ጀ/ደምሴ ወደ ኤርትራ በሄዱ በሶስተኛው ቀን ሐውዜን ተከቦ የነበረው የወያኔ ጦር የ22ኛ ብርጌድ በነበረበት መስመር ወደ ተንቤን አቅጣጫ የሞት ሽረት ተጋድሎ አድርጎ ከበባውን በጥሶ ወጣ። በወርኢ ወንዝ በኩል አድርጎ ወደ ተከዜ ገባ።

ከጥቂት ወራት በኋላ የሶስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት የሚባል ትግራይ ውስጥ ሲቋቋም የጦሩ አዛዥ ጄነራል ሙላቱ ነጋሽ የትግራይ ክ/ሀገር እና የጦሩ የበላይ አስተዳዳሪ ደግሞ የአምሳ አለቃ ለገሠ ሆኖ ተሾመ። ሃምሳ አለቃ ለገሠ ከተማ በመቆጣጠር ላይ የተመሠረተ ታክቲክ ተከትሎ የተለያዩ የትግራይ ከተሞችን "ማፅዳት" ዘመቻ ጀመረ።

ጀ/ሙላቱ ይህን ታክቲክ እንደተቃወሙ ግልጽ ነበር። ለመከላከያ ሚኒስትሩ በጻፉት ሪፖርት ከዚያ በፊት በጀ/ደምሴ የቀረበውን ወንበደውን እንቅ መሬትን ግብ ያለማድረግ እቅድ ጠቅሰው ዘመቻው በዚያ መልክ መካሄድ እንዳለበት ገልጸዋል። የጀነራሉ ፕላን በአምሳ አለቃው ተሽሮ ጦሩ በትግራይ ከተሞች ተበተነ። ከተማ የመቆጣጠር ታክቲክ ተከተሉ። ጦሩ በየትናንሹ ከተማ ከተበተነ በኋላ አንዱ ላንዱ እርዳታ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ሲገኝ ለወያኔ ጦር አመቺ ሆነለት። በተጨማሪ ከተሞችን በቦንብ ጣይ አውሮፕላን እየደበደቡ ሕዝቡን የበለጠ አስቆጡት። ሐውዜን ከተማ ላይ አውሮፕላን ድብደባ የተደረገው ያን ጊዜ ነበር።





## -6-

አዲስ አበባ ከደረስኩበት ደቂቃ ጀምሮ አስመራ የምመለስበትን ምክንያትና ቀን ማሰብ አላቋረጥኩም:: አስመራ ከሄድኩኝ ወራቶች አልፈዋል። የተቀየረ ነገር ቢኖር አባቴ ኤርትራ የሚገኘው የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ሆኖ አስመራ ሲቀር፣ አብረውት ሄደው የነበሩት ጀ/መርዕድ፣ ጀ/ኃይሉ፣ ጀ/አምሃ፣ እና ሌሎች የጦር መኮንኖች ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸው ነው። ሜ/ጀ ቁምላቸው ደጀኔ (የዘመቻ)፣ ሜ/ጀ ሁሴን አህመድ (የድርጅት)፣ እና ሜ/ጀ ወርቁ ቸርነት (የፖለቲካ) ምክትል አዛዦች ሆነው ተሹመው ነበር። አባቴ የሹመቱ ደብዳቤ ሲደርሰው ሌ/ኮ/መንግሥቱ ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ ይዞ ከቀረበ በኋላ በጦሩ ውስጥ ያለው መከፋፈል ሙቶም እንዳለበት እና አንድ ዓይነት ውጤት ለማምጣት አስፈላጊ ከሆኑት ውስጥ አንዱ በጦሩ ያለው የዕዝ ጠገግ መሻሻል መሆኑን አስረድቶ በኤርትራ እንዲሰራ ከተደረገ የአንድ ሰው ትዕዛዝ ደንብ መከበር እንዳለበት አለበለዚያ ግን የሱ እዚያ መመደብ ለውጥ እንደማያመጣ ገለፀላቸው። ሌ/ኮ/መንግሥቱም የዚህ ዓይነቱ አሰራር በሥልጣናቸው ላይ የሚያመጣውን አደጋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የዚህ ዓይነቱ አሠራር ደግሞ በሰሜን ከተጀመረ ወደ ሌሎች ክፍሎችም መዛመቱ ለስማይቀር ከብዙ ማቅማማትና ጭትጭቅ በኋላ በጊዜው ሁኔታ ተገደው ተስማሙ። በዚህ ሕግ መሠረት

የጦሩ አዛዥ የፖለቲካ ኃላፊም ይሆናል። በሌሎች ጦር ክፍሎች የፖለቲካ ኃላፊዎች ዋና ተጠሪነታቸው ለመከላከያ ፖለቲካ ሐላፊ ነበር። የዚህ ዓይነቱ አሰራር በጦር ውስጥ ከፍተኛ ብጥብጥ ሲያስነሳ የኖረ ነው። የብዙ አውነተኛ የኢትዮጵያውያን ደም በዚህ ዓይነቱ ተራ የመወነጃጀያና የጣት መጠቋቆሚያ ሥርዓት በከንቱ ፈሷል።

ጄነራል ደምሴ በመጀመሪያ ወደ ሰሜን የሄደው በ1969 ነበር። ያኔ የሁለተኛ ክፍለጦር አዛዥ ሆኖ ነበር የተሾመው። በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች አገሮች አንድ ክ/ጦር ግፋ ቢል ሰባት ሺህ ሰው ይይዛል። ታዲያ ከብዙ የድሮ ወታደሮች እንደሰማሁት ከሆነ ያን ግዜ አንድ ሻለቃ ጦር ወደ 500 ሰው ለግዳጅ ከወጣ ግዳጁን በጀግንነት ይወጣል። በጀግንነት የያዘውንም መሬት ሳይለቅ እስከመጨረሻው ይዋደቃል። ወደ ኋላው ላይ ሃያ ሺህ ጦር ተደመሰሰ፣ አስር ሺህ እጁን ሰጠ፣ ሲባል እነዚህ የድሮ ወታደሮች ግራ ይጋቡ ነበር። ነገሩ እነሱ የሚያውቁት ጦር ወይ አልቋል ወይ በአዲሱ ተውጠ መኖሩ እና አለመኖሩ ለውጥ የማያመጣበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ታዲያ በ1969 ዓ.ም ቀውጢ ጊዜ ምንም እንኳ ብዛት ባይኖረውና ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀ በይሆንም፣ በአስመራ ዙሪያ በ9 ኪ/ሜትር የተሰማራው የኢትዮጵያ ጦር መሸሽን እንደምርጫ አልቆጠረም። ተስፋ ሳይቆርጥ እስከመጨረሽ ለመዋጋት ዝግጁ ነበር። በመጨረሻ የጀበሀና የሻዕቢያ መካከል የተፈጠረው ግጭት የበለጠ ረድቶት የጦርነቱን አቅጣጫ ወደ ከረን ቀይሮታል።





አስመራ ላይ አንዣቦ የነበረው ጉም መሳሳት ሲጀምር ነበር ጀ/ደምሴ፣ ወደ ደቡብ ተቀይሮ የሄደው። ያን ጊዜ ኰሎኔል ነበር። ያኔ ተሹሞ ሲሄድ አንድ ዓላማ ብቻ ነበረው። ሲዳሞንና ባሌን አጥለቅልቆ ከአዋሳ ከተማ 60 ኪ/ሜ ላይ የሚገኘውን የሱማሌ ጦር መመከት ከዚያም ድል አድርጎ ከኢትዮጵያ መሬት ማስወጣት። ያኔ አበረውት የነበሩት የአባቴ ሹፌር እንዳጫወቱኝ ሲዳሞ ሲደርስ ግን የጦሩ ዓላማ የተለየ ሆኖ ጠበቀው። በአንድ አካባቢ ተሰብስቦ የነበረው ጦር መሣሪያውን ከባድ መኪኖች ላይ ጭኖ ሊሸሽ ሲዘጋጅ ነበር ጀ/ደምሴ እቦታው የደረሰው። በቦታው የነበሩትም መኮንኖች ግማሾቹ ግራ ገብቷቸው ቆመዋል። ግማሾቹ ደግሞ ለመሸሽ መሣሪያ ያስጭናሉ። ጀ/ደምሴ ከመኪናው ወርዶ አንዱን መኮንን ጠራውና ቀረበ።

"ምንድነው የምታደርጉት?"

"ጦሩ መሣሪያውን እየጫነ ነው ጌታዬ?"

"ለምን?"

"የተጠናከረ የሶማሌ ጦር ወደዚህ እያመራ ስለሆነ ከኋላ ካለው ወገን ጦር ጋር ለመቀላቀል ነው ጌታዬ።"

"ሁሉንም በፍጥነት ሰብስብ። ሹፌሮችንም ጭምር!" አለ በንዴት።

ጦሩም ጠላት እየመጣ ደግሞ የምን ስብሰባ ነው በሚል አኳኋን እየተገላመጠ ተሰበሰበ።

ጀ/ደምሴ ባሉበት እንዲቀመጡ አዘዛቸውና አብሮት የመጡ አንድ ሃያ የሚሆኑ አጃቢ ወታደሮች በግማሽ ቀለበት መሳሪቸውን ጦሩ ላይ ደግነው

ቦታ እንዲይዙ ትዕዛዝ ሰጣቸው። ከጦሩ ፊት በመቆም በንዴት የተሰበሰበውን ከቃኘ በኋላ "እኔ የመጣሁት በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን ጦር ለመምራት የእዙ አዛዥ ሆኜ ነው።" ብሎ ንግግሩን ጀመረ። "ጦሩን የምመራውም ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ አይደለም። ወደ ኋላ ያለው ጦርም ወደዚሁ በመምጣት ላይ ይገኛል። አሁን ረዥም ንግግር ለማድረግ ጊዜ የለኝም። ለመሆኑ የቱን መሬት ጥላችሁ ነው ወደየትኛው መሬት የምትሄዱት? ሶማሌ ገና ወደዚህ መንገድ ጀምራለች ስትሉ መሣሪያ የምትጭኑ ወታደሮች ናችሁ ወይስ ሲቪል? የዚህ ዓይነት ወራዳ ሥራ በኢትዮጵያ ጦር ውስጥ አይቼ አላውቅም። ከመሃከላችሁ አገር ወዳድ ደፋር ጀግና ኢትዮጵያዊ እንዳለ አምናለሁ። ለመዋጋት ዝግጁ የሆናችሁ መሣሪያችሁን አውርዳችሁ ከኔ ጋር ወደፊት! ከቀራችሁት ጋር ስመለስ እንነጋገራለን። ጥያቄ ያለው አለ?"

አንዱ ተነሳና "ለመሆኑ አዛዦች በየጊዜው ትቀያየራላችሁ ለመሆኑ እርስዎ ወደፊት የሚሉት ከቀድሞው አዛዥ የተለየ ምን ይዘውልን መጥተዋል?" ብሎ በማፌዝ መልክ ጠየቀ። ወቅቱ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በጦሩ ውስጥ መለያየትን የፈጠሩበትና ጦሩን ግራ ያጋቡበት ጊዜ ነበር። ንዴቱን ሲቆጣጠር የነበረው ጀ/ደምሴ ገነፈለበት።

በትረ መኮንኑን በአንድ እጁ ይዞ ወደሰውየው በቀጥታ በፍጥነት አመራ። ከፊት ተቀምጠው የነበሩትን ጥሶ አጠገቡ ሲደርስ ሰውየው እንደተቀመጠ ነበር። በትር ባልያዘ እጁ ድንገት ካንገቱ ልብሱን ጨምድዶ አነሳው። አይኑን አፍጥጦ እየተመለከተው እንደ ብራቅ በሚጮህ ድምጽ-





"መሣሪያ አለህ፣ ስንቅ አለህ። የሌለህ ነገር ቢኖር ልብ ነው። ልብ ደግሞ ልትዋጋ ትችላለህ" ... 

"መሣሪያ አለህ፣ ስንቅ አለህ። የሌለህ ነገር ቢኖር ልብ ነው። ልብ ደግሞ መጥቻለሁ። የጫናችሁትን መሣሪያ አውርዱ። የኢትዮጵያ ጠረፍ ሳንደርስ አንቆምም። ወደ ኋላ መሄድ ቀርቶ ዞር ብሎ ማየት እንኳን የለም" ብሎ የሚርበተበተውን ወታደር ለቀቀው። ከተሰበሰበው ግማሹ ማትራራት ግማሹም መቁነጥነጥ ጀመረ።

ጦሩ መሣሪያውን ከተጫነበት አውርዶ በሥርዓት ወደፊት ገሰግሶ ምቹ ቦታ ከያዘ በኋላ እየገሰገሰ ይመጣ የነበረውን የሱማሌ ጦር በድንገት ገጠመው። ከፊት የመጣውን የሱማሌ ጦር ድል አድርጎ ከኋላ የሚመጣውን የወገን ጦር ሳይጠብቅ ወደፊት የገፋው ጀ/ደምሴ ዱላ ይዞ ወደ ኋላ የቀረውን ወደፊት እንዲገፋ እያዘዘ ይጓዝ ነበር። ማምሻውን ይጠበቅ የነበረው ጦር ደርሶ ጦሩ ተጠናክሮ በነገታው ወደፊት ገሰገሰ። ለሶስት ቀናት ያለማቋረጥ የተፋፋመ ጦርነት ተደርጎ በሶስተኛው ቀን የኢትዮጵያ ጦር ከኢትዮጵያ ጠረፍ ደረሰ።

አባቴ በሲዳሞና በባሌ በእነዚያ ሶስት ቀናት በተካሄደው ፍልሚያ ከነገረኝ ሁሉ ከአንጎሌ የማይጠፋው የማላወቃቸው ሁለት ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን ነው፡፡ ..

ፊልቱ የምትባል አንድ ቁልፍ ቦታ ለመያዝ ጦሩ እየተረባረበ ነው። የጀ/ደምሴ ጂ.ኘ ታንኮችና ከባድ መኪኖች መሃል ወደፊት ትገሰግሳለች። ድንገት ከፊት ካሉት አንደኛው ከባድ መኪና ፈንጂ ላይ ወጣና ጆሮ የሚያደነቁር ድምጽ ተሰምቶ ከመኪናው አካል የወጡ ብረቶች በየቦታው ያበተናሉ። ጀ/ደምሴ ከመኪናው ወርዶ ወደ ጋየው መኪና ሄደ። አጠገቡ

ሲደርስ ወታደሮቹ ይተራመሳሉ። በፈንጂ የተመታ አንድ ወታደር አን እግሩ ክፉኛ እየደማ ይጮሀል። ቀጥሎ ስለሆነው ጀ/ደምሴ እንዲህ ብ ነበር ያጫወተን።

“ወደ ስውየው ለመጠጋት አንድ እግሬን እንዳነሳሁ የሆነ ነገር ቀፈፈኝ እ መለስኩት። ወዲያው ሁላችሁም ወደ ኋላ፤ ማንም ሰው እንዳይጠ፡ ‘የፈንጂ መሀንዲሶችን ጥራ’ ብዬ አጠገቤ ለነበረው ነገርኩት።

በአካባቢው የነበሩ ባሉበት ቀመው እንዳሉ ሁለት ወታደሮች ከየ፡ መጡ ሳይባል ሮጠው መሀል ገቡ። ተመለሱ ብዬ ካፌ ሳይወጣ አንደኛ፡ ፀረ ሰው ፈንጂው ላይ ወጥቶ ወደላይ ሲወረወር ሌላኛው እንደቆመ የፈንጂ ፍንጣሪ አንድ እግሩን ቀረጠው። ፀረ ሰው ፈንጂ ሲኖር እንደሚችል መጠራጠር አለብህ። መኪናው ሲመታ ከውስጥ የሚወጡትንና የተጎዱትን ለመርዳት የሚመጡትን ለመምታት፤ ከፀረ መኪና ፈንጂ ጎን ሁል ጊዜ ፀረ ሰው ፈንጂ ይቀበራል። ታዲያ እንደዛ ቀን ተናድጄ አላውቅም። ከየት መጡ ሳይባል ነው ዘለው የገቡት። አንደኛው ወደያው ሞተ።”

OOOO

ስለ አባቴ አስመራ መመደብ የነበረኝ ስሜት የተቀላቀለ ነበር። ባንድ በኩል የአካባቢው አደገኛነት ማንንም ልጅ እንደሚያሳስበው አሳስቦኛል። በሌላ በኩል ደግሞ በአባቴ ላይ በነበረኝ እምነትና በአባቴ ጀግንነትና ቀራጥነት የነበረኝ ኩራት ፍርሐቴን ያጠፋዋል። ጊዜው አደገኛ





ቢሆንም አስመራ ሄጄ ከአባቴ ጋር እየተዘዋወርኩ ሁኔታዎችን ለማጥናት ወሰንኩ።

ከመስሪያ ቤት ፍቃድ ጠይቄ ወደ አስመራ ለመሄድ ዝግጅት ላይ እያለሁ የአባቴ የቅርብ ጓደኛና አብሮ አደግ እንዲሁም አበልጅ የሆነው እኔም እንደ አባቴ የማየው ሜ/ጀ መርዕድ ንጉሤ ታሞ ጦር ሐይሎች ሆስፒታል መተኛቱ ተነግሮን ከእናቴ ጋር ልንጠይቀው ሄድን።

ጀ/መርዕድ የተኛው ለጀነራል መኮንኖች ተከልሎ በተዘጋጀ የህክምና ክፍል ውስጥ ነው። ደረጃውን ወጥተን ወደ ኮሪደሩ ልንታጥፍ ስንል የወታደር ፖሊስ አቀመንና የመጣንበትን ምክንያት ጠይቀን ማረፊያ ክፍል እንድንቆይ አሳየን። ክፍሉ በወንበሮችና እዲሁም በቴሌቪዥን ተሞልቷል። ወታደር ፖሊሱ ወዲያው ተመልሶ ወደ ጀ/መርዕድ ክፍል ወሰደን።

“ታዲያስ አስቴር? እንዴ ፀረ ድንቁርናም መጥተሀል እንዴ?” ፈገግ ብሎ አንድ እጁን ከብርድ ልብሱ ሥር ወደ ጎን አውጥቶ ጀርባችንን መታ መታ እያደረገ ሳመንና፣ ስለጤንነታችን መወያየት ጀመርን። ጀ/መርዕድ ባንድ ወቅት የ506ኛው ግብረኃይል አዛዥ ሆኖ ኤርትራ ሲፋለም በከባድ ሙትረየስ ተመቶ ቆስሎ ነበር። ከብዙ ሕክምና በኋላ እንደልቡ መንቀሳቀስ የጀመረ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ግን አልዳነም ነበር። ኋላም ላይ የእግር ኳስ ሲጫወት እግሩ ተጎድቶ በደንብ ሳይድን እየተነሳበት ሆስፒታል እየተኛ ታክሟል። ሌት ተቀን ከመሥራት ግን አልተቆጠበም። ያው መንቀሳቀስ ሲያቅተው ሆስፒታል እየገባ ትንሽ ሻል ሲለው ደግሞ ይወጣል። እናቴ ራሱን መጠበቅና መንከባከብ እንዳለበት

ከመከረችው በኋላ "ልፋታችሁን የሚያይላችሁ እንደሆን የለም። እንደዚ ተሩጦ ሌት ተቀን ተሠርቶ፣ ከቤተሰብ ተለይቶ አድሜን ጨርሶ መጨረሻ ደግሞ እንደ ታሪኩ በጥይት መደብደብ . . . ጉድ እኮ ነው።" አለኝ በምሬትና ጀ/ታሪኩ ላይ የተደረገው በደል እንዳሳፀየፋት በፊቷ እየታየ። "የተደረገው ያሳዝናል አድሜ ልኩን ጦር ሜዳ ኖሮ... ተይኝ አባክሽ ሰሞኑን ደግሞ ሲቪል ሆነው ለዓመታት ሲሠሩ የነበሩትን እያነሱ የጦር አዛዥ ማድረግ ሆኖአል ሥራቸው። ዘለቀ በየነ በሜ/ጀኔራልነት የደቡብ ዕዝ አዛዥ ሆኗል። ይሄ ማነው ውብሸት ደሴ በሻለቃነት ወደ ሲቪል ተቀይሮ የፖለቲካ ሥራ ሲሠራ የኖረ ነው። አሁን ከ15 እስከ 20 ዓመት ልምድ የሚጠይቀውን ቦታ ያውም ሶስት ደረጃ ዘሎ በሜ/ጀኔራልነት የምሥራቅ ዕዝ አዛዥ... ምን ትይዋለሽ ታዲያ ይሄንን፣ ቀልድ አይደለም?"

ጀ/መርዕድ የሚናገረውን ማመን እንዳቃተው የፈጠጡት ዐይኖቹና ወደ ጎንና ወደ ጎን የሚዘዋወረው ጭንቅላቱ ይገልፃሉ። በራሱ ንግግር ከመገረም አልፎ እንደመሳቅ አለና፣ ፈገግታ የማይለየውን ፊቱን ጨፍገግ አድርጎ "ለነገሩ እኛ እኮ ነው እንጂ ማዕረግ ለነሱ ምናቸውም አይደለችም። እኛ ይህን ሁሉ ዓመት ወጥተን ወርደን ያገኘነውን ማዕረግ እነሱ እያነሱ ለአንድ ሌ/ኮነሬል ለአንድ ሻለቃ ካድሬ ይሰጣሉ። ታዲያ ይሄ ፍፁም ከሚሊትሪ ሥነስርዓት ውጭ ነው።" አለ። ቀጠለናም "አሁን ዘለቀ በየነ አንድ ባትሪ እዞ እማያውቅ ከሌ/ኮለኔልነት ሜ/ጀነራል ሲሆን ምን ይባላል? ያውም ከአብዮቱ ጀምሮ በሲቪልነት ሲሠራ የነበረ ሰው! እ-ማነው ውብሸት ደሴም ቢሆን ከዘለቀ ይብሳል እንጂ እንደውም። አሁን እሱ ሻለቃ ነው። ከአብዮቱ ጀምሮ በሲቪልነት ነው የሠራው። አንስተው ሜ/ጀነራል እና





የምስራቅ ዕዝ አዛዥ አደረጉት። መሾሙን ይሾም ችግራችን እሱ አይደለም። የኛ ችግር እንዴት አድርጎ ጦር ይመራል ነው? የሱን ቀሻሻ ማነው የሚያፀዳው? ይሄን ምን ትይዋለሽ? ቀልድ አይደለም? አሁን በእነዚህ የሚመራ ጦር ይዋጋል? በሥራቸው ያሉት የበታች ሹማምንት የሚያዟቸው ሰዎች በሙሉ በሚሊተሪ እውቀትም፣ በችሎታም፣ በልምድም ይበልጧቸዋል። እና ጨርሶ ቀልድ ነው የተያዘው። መቀለድ። በሰው ነፍስ እንደሚቀልዱ.. "ብሎ አረፍ አለ።

ይሄ "እነሱ!" የሚለው ቃል ወደ እነማን እንደሚያተኩር ለመገመት ብዙም አልተቸገርኩም። ጋሽ መርዕድ ብዙ ጊዜ ቀልድ ካልሆነ የዚህ ዓይነቱን ነገር በግልጽ አያወራም። አሁን ግን ብስጭትና ቁጭት ይነበብበታል።

እኔና እናቴ ሜ/ጀ/መርዕድን እግዚአብሔር ያጥናህ ብለን ተሰነባብተን ከጦር ሐይሎች ሆስፒታል ወጣን። እቤት እንደተመለስኩ ለጉዞ የሚያስፈልጉኝን አንዳንድ ዕቃዎች ጠርቅሜ በነጋታው ወደ አስመራ ለመጓዝ ተዘጋጀሁ። ወደ አስመራ የሚጓዙ የአየር መንገድ የመንገደኛ አውሮፕላኖች ሁሉ በግዳጅ ላይ ስለነበሩ መደበኛውን በረራቸውን አቋርጠው ጦር ማመላለስ ላይ ነበሩ። አ.አበባ ከነበሩት የአባቴ ተወካይ ጋር ተነጋግሬ ከነዚሁ ወታደሮች ጋር ለመሄድ ፈቃድ እንዲያወጡልኝ ጠየቅኩ። ተወካዩም በምድር ጦር አዛዥ በጀ/ኃይሉ የተፈረመ ፈቃድ አውጥተውልኝ ጉዞዬ ቁርጥ ሆነ።

በነጋታው ጠዋት 6 ሰዓት ላይ ቦሌ አየር ማረፊያ ለወታደራዊ ነክ ጉዞ በተመደበው ክልል ስደርስ አካባቢውን የወታደሮች ትርምስ ሞልቶት

አገኘሁ። በቅርቡ የሶስት ወር ልምምድ የተሰጣቸው ቀድሞ በአብዬት ጥበቃነት ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው። በሶስት ወር ስልጠና ከልጅነት ጀምሮ ከጥይት ጩኸት ጋር ካደገ ሻዕቢያ ጋር ሊዋጉ ማለት ነው። አውሮፕላኑ ቆሞ ለበረራ ዝግጁ መሆኑን ሲያሳውቅ የየክፍሉ አዛዥ የራሱን ወታደሮች በረድፍ ማሰለፍ ጀመረ። መሣሪያቸውን ጭነው ስለነበረ ሁሉም ሌጣቸውን ነበሩ። ከያዙት ኮዳ በቀር ሌላ የወታደር ትጥቅ አልነበራቸውም። አውሮፕላኑ እስከሚችለው ድረስ ከጫነ በኋላ የተቀሩት ሌላ በረራ እንዲጠብቁ ተነግሯቸው እንደገና በረድፍ ተመለሱ። የኔ ጉዞ ጉዳይ ግራ ገብቶኝ እንደቆምኩ አንድ ሲቪል የለበሰ ወጣት ብጤ ወደኔ ጠጋ ብሎ "ትሄዳለህ የተባልከው የጀ/ደምሴ ልጅ አንተነህ?" አለኝ።
"አዎን" አልኩኝ የመሄድ ተስፋዬ እንደገና ታድሶ።

"በል እቃህ የታለ ያዝና ና እብረን ነው የምንሄደው" ብሎ የአውሮፕላኑን ደረጃ መውጣት ጀመረ። እኔም እናቴ የሰነቀችውን እብድ የሚያህል አገልግል በሁለት እጄ ይዤ ሻንጣዬንም አንግቼ እንደያዝኩ ደረጃውን እየተንገዳገድኩ ወጣሁ። የአውሮፕላኑ ውስጥ ትርኢት ተአምር ነበር። የአውሮፕላኑ መቀመጫዎች በሙሉ ወጥተው የገቡት ወታደሮች ወይ መሬት ወይ ዕቃ ላይ ነበር የተቀመጡት። በመሃል ባላችው ክፍት ቦታ እንኳን ሰው ሊተላለፍ አንድም ሰው ማቆሟን እንጃ። ታዲያ የት ልቀመጥ ነው አሁንም "ና ወዲህ!" ብሎ ያው ሰውዬ ገላገለኝ። ከፊት ያልተነቀሉ ሁለት መቀመጫዎች ነበሩ። ሰውየው ገብቶ አንዱ ላይ መቀመጡን አላየሁም ነበር።





እቃዬን እንደምንም ከፊት ለፊቱ አብቃቅቼ ተቀመጥኩ። የሰውየው ምንነት ስላልገባኝ ወደ ጎን ዞር ብዬ ቃኘሁትና "ደረጀ እባላለሁ!" ብዬ ቀኝ እጄን ዘረጋሁ። ስሙን እሁን ዘነጋሁት እንጂ እሱም ስሙን ጠቅሶ ጨበጠኝ።

አውሮፕላኑ እኮብክቦ ከተነሳ በኋላ የአውሮፕላን አስተናጋጆች ወዲያ ወዲህ ማለት ተያያዙ። ትንሽ እንደተጓዝን በላስቲክ የተጠቀለለ ለይብና ዳቦ ከብርትኳን ጭማቂ ጋር ለሁሉም እየተዘዋወሩ አደሉ። የወታደሮቹ ሁካታ ከአውሮፕላኑ ድምፅ አይሎ ይሰማል። የታዘብኩት ነገር ቢኖር አስተናጋጆቹ ለተጓዡ የሚያሳዩትን ንቀት ነበር። እልፎ እልፎ እርስ በርስ በእንግሊዝኛ ጥራዝ እየነጠቁ በወታደሮቹ ይሳለቁ ነበር። እነሱን መታዘቤን ትቼ ከጎኔ ወደ ተቀመጠው ሰውዬ ዞር አልኩና አስመራ ለስራ ነው የምትሄደው አልኩት። ስለማንነቱ ለመረዳት እችል ይሆናል በማለት።

"አዎን ጀ/ደምሴ ጠርተውኝ ነው የምሄደው። ራሽያ በትምህርት ላይ ነበርኩ። አቋርጠህ ና ተብዬ ነው የመጣሁኝ።" አለኝ ሲናገር ጭንቅላቱን ወደ ላይ ቀና ቀና እያደረገ ነው። ተጠርቶ ከራሺያ በመመለሱ የተደሰተ እንዳልሆነ ከአነጋገሩ ግልፅ ነው።
"ምን ያህል ጊዜ ቆየህ እሶሽየት ሕብረት?" ብዬ ጠየቅኩ፣ ነገሩን ለመረዳት ቸኩዬ።
"ሁለት ዓመት ቆየሁ። አንድ ዓመት ይቀረኝ ነበር..."
"የሚሊቴሪ ትምህርት ነው?" አልኩ ለማዳመጥ እየተደላደልኩ።
"አዎን ሚሊቴሪ ሳይንስ ነበር የምማረው። የጦር አዛዥነት ትምህርት" አለኝ።

“ማዕረግህ ምንድነው?” አሁንም የሚሰጠኝ አጫጭር መልሶች የማወቅ ፍላጎቴን አላረካ ስላሉኝ ትዕግስቴ እያለቀ።

“ኮሎኔል ነኝ” አለ። ሁለት ሶስት ጊዜ ተመለከትኩት። በጣም ወጣት ነው። ኮሎኔል ቀርቶ ሻለቃም አይመስል። እስከ አሁን አንተ እያልኩ ስዘረጥጠው በመቆየቴ ቅሬታ ተሰማኝ።

“ይቅርታ አላወቅኩም ነበር። ዝም ብዬ አንተ አልኩህ።” አልኩት

“አይዞህ ግድ የለም አንተ በለኝ።” አለና ቀጠለ። “ክ/ጦር ለማዘዝ ነው ተጠርቼ የመጣሁት ሌሎችም ከኔ ጋር የሄዱ ተጠርተው መጥተዋል።” አለኝ።

“መቼ መጣህ ታዲያ?”

“ከሁለት ወር በፊት ነው የመጣሁት። አዲስ አበባ አንዳንድ የምጨርሰው ጉዳይ ነበረኝ” አለ። አሁንም ጭንቅላቱን ወደ ላይ ቀና ቀና እያደረገ። ትንሽ ቆየና “የሰሜን ችግር ይኸውልህ አይለቀንም። ትምህርት እንኳን መማር አልቻልንም። ሰው የለም አሉ። ምን ይደረግ እኛም ተምረን ለመሥራት ስለሆነ የሄድነው ችግሩ ሲባባስ ደግሞ መጥተን መስራት ግዴታችን ነው።” አለኝ።

“እንዴት ነው እየተሻሻለ ነው ወይስ እየባሰ የሚሄደው?”

“አሁን እንኳን ደህና ነው። ትንሽ በከረን መስመር ነው ችግር ያለው። ሌላው ደህና ነው። ጦርነቶች ግን በየጊዜው አሉ። እኔም እዚያው ከረን መስመር ነው የምሰራው” አለና ተንጠራርቶ አይኖቹን በድካም ዓይነት እንደመከደን አለ። እኔም ትቸው ከቦርሳዬ ውስጥ መጽሐፍ አውጥቼ ማንበብ ጀመርኩ።





ከጥዋቱ ወደ ሶስት ሰዓት ገደማ ሲል አስመራ አየር ማረፊያ ደረስን። እፊት ተቀምጠን ስለነበርን ከወታደሮች በፊት ዕቃችንን ይዘን ወጣን። ከአውሮፕላናችን ትንሽ እንደራቅን “ሹፌሩ ይመጣልሃል አይደል? ” አለኝ አብሮኝ የመጣው ኮለኔል።

“መሰለኝ...” ብዬ ሳልጨርስ ባሻ ክፈተው ቶዮታ ላንድ ክሩዘሩን እያክለፈለፉ ወደ አውሮፕላኑ መጡ። ሠላምታ ተለዋውጠን ለኮለኔሉም የደንብ ሠላምታ ሰጡትና “እንኳን ደህና መጡ ጌታዬ” ብለው ጨበጡት።

“ታዲያስ ክፈተው እንዴት ናችሁ? እኔ እዚህ አየር ኃይል ጎራ ልል ነበር ግን ከናንተው ጋር ብሄድ ይሻለኛል።” አለና ቶዮታው ላይ ተሳፈረ።

“እርሶንም እንድቀበል ነው የታዘዝኩት ጌታዬ። ጀኔራል ቢሮ እንዲመጡ ብለዋል” አሉ ባሻ ክፈተው።

“እሺ. እቤት አድርሰኝና ልብሴን ለዋውጬ እመጣለሁ።” አለና አስመራ የናፈቀችው ዓይነት ዞር ዞር ብሎ እየቃኛት ተጓዘ።

ከባሻ ጋር እያወራን ቃኘው ስቴሽን ገባንና እቤት ስንደርስ እኔን አውርደውኝ በረሩ። የቤቱ ሁናቴ በፊት ካየሁት ተቀያይሯል። ባዶ ቦታ ላይ ከሌሎች መሰል ቤቶች ጋር ቀሞ የነበረው አሁን አጥር ተሰርቶለት ከፊት ለፊቱ ደግሞ በአንድ የወታደር ፖሊስ እየተጠበቀ ነው። ግቢውም አበቦች ተተክለውበታል። አባቴ በሄደበት ሁሉ እነዚህን ለውጦች ሳያደርግ አይቀርም። ጥበቃ ጽዳትና ሥነሥርዓት ተቀዳሚ ተግባሮቹ ነበሩ። በፊት ከባቴ ጋር በዚሁ ቤት ይኖሩ የነበሩት ጀነራሎች ወደ አዲስ አበባ በመመለሳቸው ሶስት መኝታ ቤቶች ባዶ ሆነዋል።

እንደ ውስጥ ገብቼ ዕቃዬን አስቀመጥኩና ወደ አባቴ ቢሮ ስልክ ደወልኩ፤ ያገኘሁት የአባቴን ፀሐፊ ሻምበል ጌታሁንን ነበር። የእንኳን ደህና መጣህ ሠላምታ ሰጥቶኝ "የዘመቻ ስብሰባ ላይ ናቸው። ለምን እዚህ መጥተህ አትጠብቃቸውም ወይስ ደክሞሃል?" አለኝ።

"እረ ድካም የለም። መጣሁ!" ብዬ ወዲያው ወጣሁ። ቢሮው እግቢው ውስጥ ቢሆንም መድረስ እንደቅርበቱ ቀላል አልነበረም። አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ሶስት ጊዜ እንድቆም ትዕዛዝ ተሰጥቶኝ ማንነቴ እየተጣራ እያለፍኩ ነው የደረስኩት።

ሻ/ጌታሁን ከጀ/ደምሴ ቢሮ ፊት ለፊት ባለ ሰፊ ክፍል ብዙ ስልኮች ከተደረደሩበት ትልቅ ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጧል። ኮስማና ሰውነቱ በተቀመጠበት ግዙፍ ወንበር ተሞልቶ የባሰውን አንሷል። በጣም ቀጭንና የልጅ ፊት ያለው ቢሆንም በራሱ የሚተማመንና ኩሩነቱ በፊቱ ላይ የሚታይ መኮንን ነው። ስለዚህ በቀላሉ የሚደፍሩት ሰው አይደለም። አባቴ እንደ ልጁ ስለሚያየው የኛም አቀራረብ የወንድማማችነት ነበር። ተቃቅፈን ስንጨርስ ስለጦርነቱ ሁኔታ ጠየቅኩት።

"አሁን ጦርነት ያለው ያው በከረን በኩል ነው። እንዲያውም ነገ ወደዛው ሳንሄድ አንቀርም።" አለኝ ነገሩን ቀለል አድርጎ።

"ኦ እውነትህን ነው በል እኔም አብሬያችሁ መሄድ አለብኝ። ዋናውም የመጣሁት ከአባዬ ጋር እየተዘዋወርኩ ሁኔታዎችን ለማየት ነው" አልኩት።

"ትችላለህ ጠይቃቸው" እንዳለኝ አባቴ በርከት ባሉ መኮንኖች ታጅቦ ወደቢሮ ሊገባ ሲል ወደሱ አመራሁ። ፈገግ ብሎ

"ኦ ልጅ ደረጀ ታዲያስ ባክህ!" ብሎ አቀፈኝ።





"ደህና ነኝ ታዲያስ!" አልኩና። ተሳሳምን።

"ልጄ ነው። ዛሬ ነው ከአዲስ አበባ የመጣው። የአስመራን መንገድ የውሃ መንገድ አድርጎታል" ብሎ ለተቀሩት አስተዋወቀኝ። አንዳንዶቹን ቀደም ብዬ አውቃቸው ስለነበረ ተገቢውን ሠላምታ እጅ እየነሳሁ ሰጠሁ። ግማሾቹ ብ/ጋዲየር ጀነራሎች ግማሾቹ ደግሞ ኮነሬሎች ነበሩ።

"በል ጠብቀኝ ትንሽ ሥራ አለን ከዚያ ምሳ እንበላለን።" ብሎኝ ወደ ቢሮው ገባ። ስብሰባው ብዙም አልቆየ ከበሩ በላይ የነበረው ቀይ መብራት ጠፍቶ አረንጓዴው በራና መኮንኖቹ አንድ በአንድ ወጡ። ወዲያው አባቴም ቆቡንና በትረ መኮንኑን ይዞ ብቅ አለና ቀሞ ወደ ሚጠብቀው መኪና አመራን።

"እሺ, በል? ምን አዲስ ነገር አለ?" አለኝ ቤት ደርሰን ሶፋ ላይ ቆቡንና በትረ መኮንኑን አኑሮ ደገፍ ካለ በኋላ።

"ያው ነው ሁላችንም ደህና ነን። አንተስ ሥራ እንዴት ነው?" አልኩና ጠየኩ። ከአባቴ ጋር በጣም ተዝናንቼ በነፃነት ነበር የምንወያየው።

"አሁን ብዙ ነገር ተስተካክሏል። ያኔ ከመጣህ ጊዜና አሁን በጣም ብዙ ለውጥ አለ። ብዙ ለውጥ። የሚያመኝም ጨርሶ ጠፍቷል። በል ተነስ ጃል! ምሳ እንብላ።" ብሎ ወደ መታጠቢያ ቤት አመራ።

"የመጣሁት አገልግል አለ። ልክፈተው ወይስ ነገ ወደ ከረን ይዘነው እንሂድ?" ስለከረን መንገድ ሳንነጋገርና መሄዴን ሳልጠይቅ ለጉዞ እንደተዘጋጀሁ በማስታወቅ ዓይነት።

"ማን ነገረህ ደግሞ? ገና ከመምጣትህ ኢንፎርሜሽን መሰብሰብ ጀመርክ? አንተ እኮ የምትቻል ሰው አይደለህም?" አለኝ ተገርሞ እያየኝ።

“እይ ጌታሁን ነገ ወደዛው እንሄዳለን ስላለኝ ነው። እና እኔም አብሬ፣ መሄድ ከቻልኩ ደስ ይለኛ ነበር።” አልኩ በመማጸን ዓይነት።
“ትችላለህ ይህን ያህል ካሳሰበህ። በጥዋት ነው የምንሄደው በጊዜ ተኛ፣ ልብስ ደግሞ ያስፈልግሃል። ይህን ለብሰህ መሄድ አትችልም። ግንባር ነው የምንሄደው።” አለኝ ወደ ጠረጴዛው እያመራ።

“ሰሞኑን ከፍተኛ ኦፕሬሽን በከረን አካባቢ እያካሄድን ስለሆነ መመለሳችን አይቀርም። ነገር ግን ጠሩን ለውጊያ ለማሰናዳት ነው የምንሄደው። እስከዚያው ከኔ ጋር መዘዋወር ትችላለህ። የምትሰማውን ግን ለራስህ ያዘው” አለኝ ምግቡን እያወጣ።
“ኧረ እኔ ፈጽሞ አላወራም። ለዚያውም የማውቀው ሰው የለ” ብዬ እናቴ ሌላ አገልግል እልካለሁ ያለችው ትዝ ብሎኝ እሱን በሰሞኑ ጉዞዎች ለመውሰድ አሰብኩና ይህኛውን ከፍቼ አቀረብኩ። ከትልቅነቱ የተነሳ አገልግሉን ለአንድ አነስተኛ ጦር የተላከ ይመስላል። እናቴ ራሷ እያንዳንዷን የእንጀራ ቅንጣቢ እጅ በሚያስቀረጥም መልክ እያራሰች አጥንቱንና እንቁላሉን የተፈጥሮ ቦታውን ይዞ እንደሚቀመጥ ዓይነት አድርጋ እየጎሰጎሰች የሰነቀችው አገልግል ነው።
“ግሩም አይደለም እንዴ ባክህ?” እያለ ደግሞ አወጣ።
“ዛሬ አንድ አብሮኝ የመጣ ወጣት መኮንን ኮሎኔል ነኝ ሲለኝ ገረመኝ። ከራሺያ ጠርተውኝ ነው የመጣሁት አለኝ።” አልኩ ወሬ ለመጀመር።
“እዎ ያ አጭበርባሪ! ቅድም ከስብሰባ ስወጣ አስጠርቼ ልክ ልኩን ነግሬ፣ እንጥሬ እንጥሬ፣ ወደ እስር ቤት ላኩት። በሌላው አዛዥ ላይ የለመደውን





በኔ በደምሴ ላይ ሊቀልድ ሞከረ” ሲለኝ ባልጠበቅኩት ድንገተኛ መልስ ቀዪንቱም ትንሽም ደንግጬ በጉጉት ማደመጥ ጀምርኩ።

"ከመጣ ሁለት ወሩ ነው አሉኝ። እስካለፈው ሳምንት ሪፖርት ሳያደርግ ዝም ብሎ ተቀምጦ ቆይቶ አሁን መጣ። ይህን አጭበርብረህ ያገኘኸውን ማዕረግ ነው የማሳጣህ አልኩት። ሹመት ሲመጣ እዚህ ተሰፋዬ ገ/ኪዳን ሥር ጉድ ጉድ ብሎ ለሌላ ሌ/ኮሎኔል የሚገባውን ነው እሱ የወሰደው። አሁን ደግሞ ጠፋ በቂ አዛዥ በሌለው ጊዜ ተጠርቶ አዲስ አበባ ሁለት ወር የሚያስቀምጠው ንቀት ካልሆነ ሌላ ነገር የለም። አሁን ትንሽ አቅምሼ እልከዋለሁ” አለ። ለኔ የሚናገር ሳይሆን ከራሱ ጋር በንዴት የሚወያይ ይመስል ነበር።
"አሁን ወደ ኤርፖርት ሄጄ የመጡትን ወታደሮች ማነጋገር እፈልጋለሁ። ከፈለግክ መምጣት ትችላለህ።” አለኝ ከትንሽ ፀጥታ በኋላ። ሲናደድ ሁላችንም እስኪበርድለት ድረስ በጸጥታ እንጠብቃለን። ቁጣው ግን ለሰከንዶች ብቻ ነው። በምንም ነገር ለረዥም ጊዜ አይናደድም። ቂምም አይዝም። ለሰኮንድ የሚቆየው ቁጣው ግን አንዳንዴ እንደ መብረቅ ያስደነግጣል።
"እዎ መሄድ እፈልጋለሁ። በተቻለኝ አብሬህ መዘዋወር ነው የምፈልገው” አልኩ። “ጥሩ የምታየውን ሁሉ በደንብ ተከታተል። ትምህርት ይሆንሃል” ብሎኝ ተነሳና ወደ ስልኩ አመራ።

እቤት መጥቶ ከአንድ ሰዓት በላይ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ሶስት ወይ አራቴ ወደ ቢሮ ይደውላል። ሥራው ውጥረት ነው። እረፍት

የለም። በአስራ ሰባት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያረፈበት ጊዜ ትዝ አይለኝም፣ ታምሞ እንኳን ለማረፍ ጊዜ የለም። ሥራውን ግን እንደኑሮ ስለሚቆጥረው ለእርሱ ውጥረት የኑሮ እውነታ እንጂ ጊዜያዊ ክስተት ሆኖ አይታየውም፤ ለዚያም ነው መሰለኝ አዲስ አበባ መጥቶ አንድ ሳምንት ሳይቆይ ነው "ወደ ግንባር ሄጄ ጠሩን ማነጋገር አለብኝ" ብሎ የሚነሳው። ኑሮ ትርጉሙን እንዳያጣ።

ወደ አየር ማረፊያው ለመጓዝ ጉዞ ስንጀምር ከኋላችን መትረየስ የተጠመደበት ግልጽ ቶዮታ ተከተለን። በፍጥነት የከተማ መብራቶችን እየጣስን ነበር የምንጓዘው። አየር ማረፊያው ስንደርስ በቅርቡ የደረሱ ተጨማሪ ወታደሮች አሁንም በረድፍ ቆመው ቁጥራቸው ሲጠራ እያዳመጡ ይመልሳሉ። ሜዳው ውስጥ ገብተን እስከ ወታደሮቹ ነዳንና ገና ከመኪናው እንደወረድን፣

"በሥላሴ? ምንድን ነው የሚሠራው? ና እስቲ ወደዚህ?" በማለት ቆሞ ቁጥር የሚጠራውን መኮንን ጀ/ደምሴ ጠራው።

"አቤት ጌታዬ" ብሎ በተጠንቀቅ ቆመ።

"ምንድን ነው? ይሄ ነው ማለት ነው ኮዳቸው?" ብሎ ጠየቀ።

"አዎ ይሄው ነው። የብረት ኮዳ የለም ተብለን ነው ጌታዬ" አለ መኮንኑ፤ እኔ የለሁበትም በማለት አኳኋን።

"ምን ማድረግ ይሻላል? አሁን ከኮዳ አቅም ማዘጋጀት ያቅተን? ይሄ ኮዳ በረሃ ውስጥ ሊያገለግል ቀርቶ አንድ ቀን አያድርም። ታዲያ ያለውሃ ልንዋጋ ነው ወይስ እኔ ኮዳ እንድሆን ነው ይህን የሚልኩት?" ብሎ በማዘን እንደ ወደ መሬት አቀረቀረና ከዚያ ወደ ሩቅ ተመለከተ።





ወታደሮች የያዙትን ኮዳ ቀደም ብዬ ያየሁት ቢሆንም ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። ኮዳው የላስቲክ ከመሆኑም በላይ በጨርቅ በተሰራ ከረጢት ገብቶ በጨርቅ ማንገቻ በአንገት የሚጠልቅ ነበር። እውነትም እንኳን የበረሃ ሙቀትና የወታደር ውጣ ውረድ ሊችል ቀርቶ ለአንድ ተማሪ የውሃ መያዣነት እንኳ የሚጠቀሙበት አይደለም።

"ለጊዜው እዚህ ተጨማሪ ሥልጠና እየሰጠን እናቆያቸዋለን። በኮዳ ምክንያት ... ኮዳ እስኪገኝ..." የፌዝ ሳቅ ሳቀና።

"ሌላስ ትጥቅ በደንብ ይዛችኋል?" አለና የመኮንኑን መልስ ሳይጠብቅ ቀጥሎ "ከድርጅት መኮንኑ ጋር ተነጋገርና የሚጎልህን ዝርዝር ስጠው። ከነገ ወዲያ ቢሮዬ መጥተህ እንድታነጋግረኝ። ይኸው ነው" ብሎ እየተናደደ ወደ መኪናው ተመለሰ።

"የሚገርም ነው። ዝግጁ ናቸው ተብለው ነበር የመጣሁት። አሁን እዚህ ባልመጣ ኖሮ በዚህ ኮዳ ሊላኩ ነበር ማለት ነው። እንግዲህ እኛ ስንቱን ጥቃቅን ነገር ተቆጣጥረን እንችላለን?" አለ መኪና ውስጥ ከገባን በኋላ። ንግግሩ ለማናችንም አልነበረም፤ ሁላችንም ዝም ብለን እናዳምጣለን።

"ጦርነት ማሸነፍ የሚቻለው ሰው በማግበስበስ ብቻ አይደለም። በቂ ስልጠናና ትጥቅ ያልተሰጠውን ጦር ማዋጋት ወደ እሳት መማገድ ነው። ወታደሩ አይፈረድበትም። የችሎታውን ነው የሚያደርገው" አለ አሁን ከኋላ ተቀምጦ በዝምታ ይጓዝ የነበረውን የዘመቻ መኮንን እየተመለከተ። መኮንኑም የዓይት ተካፋይ መሆኑን ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ገልጾ ዝም አለ። ቢሮ እንደደረስን "አዲስ አበባ መከላከያ ደውልና አገናኘኝ" አለና ጀ/ደምሴ ፀሐፊውን እያዘዘ በፍጥነት ወደቢሮው ገባ።

"እሺ ጌታዬ" ብሎ እሱም ሮጥ ሮጥ እያለ ገባ።

እኔም ትንሽ ዞር ዞር ስል ጥግ ላይ ዳማ ወደሚጫወቱ ሁለት ወታደሮች አየሁ። ወደ እነሱ ሄጀ ጨዋታውን ቆሜ መመልከት ያዝኩ። በወረቀት የተሠራች ዳማ ወጫወቻ ላይ ቆርኪዎችን እንደ ወታደርና ንጉሥ እያስመሰሉ ነበር የሚጫወቱት። "የወታደር ነገር ሥራውም ጨዋታውም ውጊያ ነው" አልኩ በሆዴ። ወዲያው ደግሞ ሐረር ወታደሮች ያለሙት እርሻ ትዝ አለኝና ሰላም ቢወርድ ከጦርነት ጋር ያልተገናኝ ብዙ ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ አሰብኩ። የወረቀቱ ዳማ ላይ ወታደሮቹ አልቀው ሶስት ንጉሦች ቀርተዋል። የተበጣጠሰ በሚመስል ጨርቅ በተሰራ፤ ጦር ሜዳ ለመመሳሰል የሚጠቀሙበት ሽፋን ስር ተቀምጠው የርቀት መገናኛ ሬደዮ ላይ ጆሮአቸውን ጥለው ጨዋታቸውን ቀጥለዋል። ትቻቸው ወደ ቤት ሄድኩ።

ማምሻዬን እስመራ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ የነበረውን አጎቴን ከበበው ቡልቶን ደውዬ መምጣቴን ካበሰርኩት በኋላ በነጋታው ከረን እንደምሄድ ነገርኩት። ከሥራ በኋላ ለመገናኘት ተስማምተን እስኪመጣ እዚያው ቃኘው ስቴሽን እየተዘዋወርኩ ለመቆየት ወጣሁ።

ወደ ምሽቱ አስር ሰዓት ገደማ አባቴ ከቢሮ መጣ። እንደወትሮው ብዙም አላወራንም። ነገር ግን ስለ ነገው ጉዞ ወሳኝነት ጠቅሶ አስረዳኝ። ዓላማው በሚቀጥሉት ሶስት ቀናት ውስጥ ከባድና አፋጣኝ የመልሶ ማጥቃት እርምጃዎችን በከረን ግንባር ከከተማው 40 ኪ/ሜትር አካባቢ ርቆ በሚገኘው የአጋሮ ተራራ ላይ ለመውሰድ ነበር። የዚህ ተራራ ገዢ





መሬትነት ለሚቀጥሉት እርምጃዎች ወሳኝ ነበር። ሻዕቢያም ይህን ስለሚያውቅ ኃይሉን አጠናክሮ በተራራው መሽጓል።

"ይህን ተራራ አጥቅተን በግድ መያዝ አለብን" አለኝና ቀጠለ። ነገሩ እነሱም ለማጥቃት እየተዘጋጀን እንደሆነ ያውቁታል። ስለዚህ ተዘጋጅተው ነው የሚጠብቁን። ነገር ግን እንድ ያላሰቡት ነገር አዘጋጅተንላቸዋል። እሱን እያውቁም። እና ይሄን ቦታ መያዝ በዚያ በኩል ለምናደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ አማራጭ የሌለው ነው። በጣም አስቸጋሪ ተራራ ነው፤ ግን መያዝ አለበት" አለ የውጥኑን ምስጢርነት በሚገልጽ ቀስ ባለ ድምጽ።

ሚስጥሩ ከበደኝ። ሚስጢር መያዝ አቅቶት መሬት ቆፍሮ እንዳወራው ወሬኛ ታሪክ ሆዴን ወጥሮ አቁነጠነጠኝ። የሚቀጥለውን ለማወቅ ያለኝም ጉጉት ልቦለድ ሳነብ የታሪኩን ምስጢር መፍቻ ላይ የደረስኩ ዓይነት ነበር። አባቴ በኔ ላይ ባለው እምነት እየተገረምኩ ወደ አልጋዬ ሄጄ ተጋደምኩ። እንቅልፍ ግን በዋዛ አልመጣልኝም። ሳወጣ ሳወርድ እና የማደርገውን /ካሞፍላጅ/ ዥጉርጉር የወታደር ልብስ ሁለት ሶስቴ ከአልጋ ተነስቼ ሳይና ስለካ ለሊቱን ኢጋመስኩ። ስለ አጋሮ ተራራ አሰባሰሁ። ከዚህ በፊት የማውቀው ዓይነት ቁልጭ ብሎ ታየኝ። የወንበዴው ምሽግና የጠመንጃ አፈሙዞች አፍጠው ታዩኝ። ፍልሚያው ባይኔ መጣ። እንቅልፍም እንዳይቀር ድንገት መጥቶ ወሰደኝ።

-7-

ከረን

ጠዋት ወደ አምስት ሰዓት ገደማ አባቴ ክፍሌ መጥቶ “ተነስተሃል?” ሲል ባነንኩ ። ደካማ እንዳልባል ወዲያው ፈጠን ብዬ ነቅቼ እንደቆየሁ ዓይነት “አዎ ነቃቻለሁ” አልኩ። ሌላ ጊዜ ሶስት ወይ አራቴ ተሰቀስቅሼ የምነሳው ሰው ከአልጋ ለመውጣት ሰከንድ አልፈጀብኝም። ተጣጥቤ ልብሴን ለበስኩና ከአገልግሉ አሙቄ አቀረብኩ።

“ሆ!ሆ! በርትተሓል...በል!” አለ አባቴ እንፋሎቱ ከላይ የለበሰውን እንጀራ እየጣሰ የሚግተለተል ፍርፍር እየተመለከተ። ወዲያው ሻ/ጌታሁን መጣ።

“ጌታሁን ቁርስ ብላ” አለው አባቴ ወደ መታጠቢያ ቤት እያመራ። ጌታሁንም “ታዲያስ ተዘጋጀህ?” አለኝና ወደ ጠረጴዛው ቀረበ።





ቶሎ ቶሎ በልተን ወዲያው ለመሄድ ተዘጋጀን። መጀመሪያ ወደ ቢሮ ነበር የሄድነው። እዚያ ትንሽ ቆይተን ጨለማው ለቀኑ መልቀቅ ሲጀምር አንድ ማእረግ የሌለው የወታደር ልብስ የለበሰ ነገር ግን ሹም የሚመስል ሰውዬ መጥቶ ከተቀላቀለን በኋላ በተለመደው ሁናቴ ወደ አየር ማረፊያው ከነፍን። እንደ አጃቢ መኪናው ሲቆም ተፈናጥሬ መውጣት ለምጄ ነበርና ተፈናጥሬ ስወጣ ሰውየው ጠጋ ብሎ “አጃቢ ኮማንዶ ነህ?” ብሎ ጠየቀኝ። በሰውየው ጥያቄ ግራ እየተጋባሁ “አይደለሁም” አልኩት። ወታደር እንዳልሆነ ገባኝ። ለትሩ ገባ ያለና ደልዳላ የከተማ ሰውነት ያለው ደርባባ ሰው ነው። በኋላ ሙሉጌታ ሉሌ የተባለ በማስታወቂያ ሚኒስቴር የመምሪያ ሃላፊ መሆኑን እና የታወቀ ጋዜጠኛም እንደነበረ ተረዳሁ። እሱም እኔም ወሬ ለመሰበሰብ ነበር የምንሄደው። በመጀመሪያ ሳየው አስተያየቱ ተጠራጣሪና ነገሮችን የሚያሰላ ይመስላል። ሰውየውና ሥራው ተጣጥመዋል ብዬ አሰብኩ።

አየር ማረፊያ ስንደርስ ውስጥ የሚጠብቁን ሁለት ሲቪሎች ነበሩ። ሰማያዊውን የሲቪል ደንብ ልብስ ለብሰው ቆመዋል። አንደኛው ቀደም ቀደም የሚል ሽበት ጣል ጣል ያለበት የመንግሥት እርሻዎች ሚ/ር ቀጠካይ ነው። ሲናገር ይፈጥናል፤ ሲሄድም እንዲሁ። "ጀኔራል መቼም እንደምንም ብለው እርሻችንን እንደሚጎበኙልን ተስፋ አለን" አለ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ፈጠን ፈጠን እያለ።
"ጥሩ ነው ጊዜ ካለ ምናለ። ብቻ የምንሰራቸው ሥራዎች አሉ። እዚያ ካሉት ከናንተም ሰዎች ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ። የነሱ አቤቱታ ወረቀት ነው ጠረጴዛዬን የሞላው።" አለ ጀ/ደምሴ ወደ ቆመችው ትንሽ አውሮፕላን እያመራ።

"አዎ ብዙ ችግር አለባቸው እዚያው መነጋገር እንችላላን። እንደምንም ብለው ትንሽ ጊዜ ቢሰጡን ጥሩ ነበር" አለ ሰውየው ከኋላ ከተል እያለ። "ጥሩ ነው እንዲያውም አሁን ትንሽ ጊዜ አለን። መጀመሪያ የናንተን እርሻ እንጎበኝና ከዚያ እንቀጥላለን። ትክክለኛውን ሰዓት ያልነገርኩህ አንዳንድ ያልጨረስናቸው ነገሮች ስለነበሩ ነው እንጂ ከፕሮግራማችን አንዱ የናንተን ልማት ማየትና የጥበቃውን ሁኔታ ለማስተካከል ነው" አለው ቆም ብሎ። ወደፊት የሚያደርጉትን ሰዎች ሲጠይቋቸው እርግጠኛ መልስ አለመስጠት የአዛዦች ልማዳቸው ነው። ከአዛዥነት ጸባያት አንዱ ሳይሆን አይቀርም።

ወደ አውሮኘላኑ አንድ በአንድ ገባን። በሁለት ረድፍ ሁለት ሁለት መቀመጫዎች ነበሩ። ወደ ኋላ ልቀመጥ ስል አባቴ ጠራኝና ከሱ ጋር ተቀምጬ አንዳንድ የቤተሰብ ጨዋታዎችን እያወራን ጉዞውን ተያያዝነው። ከረን ከአስመራ ወደ አንድ መቶ ኪ/ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ከተማ ስለነበር በረራችን ጊዜ አልወሰደም። ባለ ሁለት ሞተር አውሮኘላኑ ከረንን እንደ በመዞር ላይ እያለ አባቴ ወደኔ ዞር ብሎ "ይኸውልህ ከረን ስትራቴጂካዊነቷ ከነዚህ ተራሮች አንጻር ነው። ዙሪያዋ በተራሮች የተከበበ ስለሆነች ለመከላከል ቀላል ነው። ከተራሮች ባሻገር ደግሞ ያለው ለጥ ያለው ሜዳ አጥቂውን በጣም ያስጠቃዋል።" አለኝ በጣቶቹ ወደ የተራራው እያመለከተ። እውነትም ተራሮቹ እንደሰው ሰራሽ ግንብ ከረንን ከበው የሚጠብቁ ይመስል ዙሪያውን ቆመዋል። ከአንዱ ተራራ ጎን ለጥ ያለ ሜዳ ላይ የተሰራ አነስተኛ የአየር ማረፊያ ይታያል። ወደ መሬት እየተጠጋን ሄደን ሜዳው ላይ አረፍን። አውሮኘላኑ ሞተሮቹን አጥፍቶ ከቆመ በኋላ





አንድ የአየር ኃይል ሠራተኛ ከፓይለቶቹ ክፍል ወጥቶ ዋናውን በር ከፈተና ደረጃ ገጠመበት። ሁላችንም እየተሰናበትን ወረድን።

የከረን አየር ከአስመራው ትንሽ ቀዝቀዝ ይል ነበር። ከአውሮፕላኑ እንደወረድን ይጠብቁን የነበሩት መኮንኖች ወደኛ ቀርበው ሰላምታ ስንለዋወጥ ትንሽ ቆምንና ተዘጋጅተው ወደ ሚጠብቁን ዋዞች/ራሺያ የሚሠሩ ጂፕ መሰል መኪኖች/ ላይ ተሳፍረን በፍጥነት መጓዝ ጀመርን። በመጀመሪያዎቹ ደቂቃዎች ውስጥ በመንገዳችን ከወታደሮች ሌላ ሰላማዊ ሰው አላየሁም። ወደ ከተማዋ እየገባን ስንመጣ ከረን ሞቅ ሞቅ እያለች መጣች። በመንገድ ላይ ትናንሽ የእህል ገበያዎች ይታያሉ። ጥምጣም የጠመጠሙ ነጋዴዎች ግመሎቻቸውን እያቀሙ በእርዳታ የመጣ እህል የእርዳታ ድርጅቶች አርማ ካለበት ጆንያ እያወጡ ይሸጣሉ። ሌሎቹ ደግሞ ፍየሎችን እየነዱ ይጓዛሉ። በምስራቅ ኢትዮጵያ ካሉት የአፋር ብሔረሰብ የሚለያቸው መሣሪያ አለመያዛቸው ብቻ ነው። መንገዱ አስፋልት ባይሆንም ለጥ ያለና አቧራ የሌለው ነበር። ምናልባት በዝናብ አቧራው ታጥቦም ይሆናል። በአጠቃላይ ከረን ይህ ነው የሚባል ልዩ ነገር ባይኖራትም የብዙ ኢትዮጵያውያን ደም ፈስባታል! የታሪክና የአቀማመጥ ወሳኝነት አላት።

እየተጠማዘዝን ሄደን ወደ አንድ ጦር ሠፈር ደረስን። በቀጥታ የሄድነው ወደ ቀዳሚ መምሪያ ተብሎ የሚታወቀው የዘመቻ ማቀነባበሪያ ክፍል ነበር። ቅዳዩ የማይመለከተን ከመኪናዎቹ ወርደን ስንጠብቅ የተቀሩት ጀ/ደምሴን ተከትለው በመደዳ ወደተሰራው ቤት ገቡ። ውስጥ የነበሩት መኮንኖች እየወጡ ሲቀበሏቸው ዐይኔ አንድ የማውቀው ፊት ላይ አረፈ።

ካየሁት በርካታ ዓመታት አልፈዋል። ያን ጊዜ ሻምበል ሆኖ ሐ
የመኮንኖች ክበብ ነበር ያገኘሁት። ከዚያ በፊት እኔ በጣም ልጅ እያ
አባቴ የሐረር ጦር አካዳሚ የትምህርት ዲሬክተር በነበረበት ጊዜ እ
መኮንን የነበረ ሰው ነው። ስፖርተኛና ተጫዋች በመሆኑ ወደሱ እየሄደ
ኳስ እንጫወት ነበር። አሁን ከረን ላይ ሳየው ዓለም ይህን ያህል ሊያ
አይችልም ብዬ ተጠራጠርኩ። ስብሰባ ጨርሰው እስካነጋገረው ጨነቀ
እየተንጎራደድኩ ጠበቅኩ። በሩ ተከፍቶ ጮክ ባለ ድምጽ እየተነጋገ
ሲወጡ ወደ እሱ ጠጋ አልኩ።

“አምሳሉ?” አልኩት እሱ መሆኑን እየተጠራጠርኩ። እሱም ግራ ግብቶ አተኩሮ አየኝ።

“ደረጀ ነኝ፣ እንደምን አለህ?” አልኩና ወደሱ ቀረበኩ።

“እንዴ? አንቺ ነሽ እንዴ እንዲህ ትልቅ ሰው የሆንሽው?” ብሎ አቀፈኝ
በማስታወሱ እየተገረምኩ እጁን መለስኩ። አምሳሉ የሙሉ ኮሎኔ
ማዕረግ አድርጎ ስለነበር እዚህ በመድረሱ የተሰማኝን ደስታ ገልጬ “ሰሚ
እንዴት ይዞሃል? መቼ መጣህ?” ብዬ ጠየቅሁት።

“አለን ይኸውልህ! ደህና ነኝ። እዚህማ ቆየሁ። ያኔ ሐረር ካገኘሽኝ በኋ
ነው እኮ ወደዚህ የተዛወርኩት።” ያን ጊዜ ሳየው ደህና የነበረው ጸጉ
አሁን ሸሽቶ ወደ ኋላ ሄዷል። ሰውነቱም ጨምሮ ትንሽ ቦርጭ ብጠ
አውጥቷል። ንግግራቸውን ጨርሰው መንገድ መጀመራቸው ስለነበር
ጀ/ደምሴ ወደ አምሳሉ ጠጋ አለና “በል እንግዲህ አምሳሉ የተነጋገርናቸውን
ነገሮች ተከታትለህ በፍጥነት አስፈጽም። እና ይሄን ቦርጭህን ደግሞ ስመለስ





እንዳላየው።” ብሎ በበትረ መኮንኑ ቦርጩን በቀልድ መልክ ገፋ አደረገውና ከቆመው መኪና ላይ ተሳፈረ።

ከጦር ሰፈሩ ወጥተን ወደ ዋናው የከረን መንገድ ገባን። ጉዞአችን ኢላበረድ የሚገኘውን የመንግሥት እርሻ ለመጎብኘት ነበር። ኢላበረድ ከከረን ብዙም አይርቅም። በአረንጓዴ ልምላሜ የተሸፈነ አካባቢ ስንደርስ ወታደሮች ማየት ጀመርን። እስካሁን ያየሁት የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል በጨንጫ ድንጋይ የተሞላ ካልሆነ እንደ ምጽዋ ምድር በዳ ሐሩር ነበር። ይህኛው ግን ጨርሶ ልዩ ነው። በኤርትራ ብርቅ የሆኑ ረጃጅም ዛፎችና ተክሎች እንዲሁም ሰፋ ያለ የብርትኳንና የሌሎች ፍሬ ዛፎች እርሻ ተንጣሎ ይታያል። በዋናው በር ገብተን ግዙፍ የድንጋይ ቤት ስር ቆምን። ከአስመራ አብረውን መጥተው ከረን አውሮኘላን ማረፊያ የተለዩን ሰዎች ወዲያው ብቅ ብቅ ብለው ተቀበሉንና የእርሻውን ሥራ እስኪያጅ አስተዋወቁን። ሰውየው ትንሽ ቆም ብሎ ካወራ በኋላ ራሱ መኪና ውስጥ ገብቶ የተከተሉኝ ዓይነት ምልክት ሰጠን። እሱን እየተከተልን ቀጠልን።

ግቢው እንደ ሰፋቱ አንድ አነስተኛ ከተማ መሆን ይችላል። ዙሪያውን በሽቦ ከታጠረው.. እርሻ ሌላ የተለያዩ የልማት ዘርፎች በውስጡ አሉ። ከመኪና እየወረድንና እየተሳፈርን በግቢው ተዘዋውረን የአሳማ፣ የከብት፣ የዶሮና የመሳሰሉትን እርባታ እንዲሁም እርሻው የሚያመርተውን የወይን ጠጅ እስከ ሚዘራቸው ሰብሎች ድረስ ጎብኘተን ተመለስን። በጉብኝታችን መጨረሻ ላይ ለምሳ እንድንመለስ ተጋብዘንና ሊነጋገሩባቸው ያቀዱት ጉዳዮችም ያኔ እንዲነሱ ተስማምተው ተለያየን።

የሚቀጥለው ጉዞአችን በመሳሕሊት ግንባር የሚገኘውን 10 ኪ.ጦር ከሁለት ቀን በኋላ ከሚጠበቀው ውጊያ በፊት ለማነጋገር ነበር እሁን ወደ ዋናው ጉዳይ ልገባ ነው አልኩ በሆዴ። ከዋናው መንገድ ወጥተ አንድ በተራራ ዙሪያ የተሰራ መንገድ ተያይዘናል። በምንጓዝበት መንገ፥ በተራራው ዙሪያ ስንጠመዘዝ ከፊት የሚጠብቀን ጨርሶ ስለማይታ፥ መንገዱ ትንሽ አስፈሪ ሆኖ ተሰማኝ። ሁለት ተመሳሳይ ተራሮችን አልፈ አንድ ከፍ ብሎ በሚገኝ ተራራ ጫፍ ላይ ስንደርስ በርከት ያሉ ከፍተኛ መኮንኖች ከፊት ለፊት ቆመው ወደ ምንመጣበት አቅጣጫ ይመለከታሉ።

ከነሱ በስተጀርባ በተራራው ላይ ደግሞ በቁጥር ከ5-6 መቶ የሚሆኑ የተለያየ ማዕረግ ያላቸው ወታደሮች ከላይ ወደ ታች ተደርድረው ተቀምጠዋል። መኮንኖቹ አጠገብ ስንደርስ አቆምንና ከመኪኖቹ ወረድን። ጀ/ደምሴ እና አብረውን የመጡት የጦሩ ምክትል አዛዥ ጀ/ቁምላቸው ደጀኔ ከመኮንኖቹ ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ ትንሽ ቆሙና ተቀምጠው ወደ ሚጠብቁት ወታደሮች ሲያመሩ እኛም ተከተልን። ወታደሮቹ በአንድነት ሰላምታ ከሰጡ በኋላ የክ/ጦሩ አዛዥ አጠር ያለ ንግግር አደረጉላቸው። ንግግራቸውን ጦሩ ያለውን አስተያየትና ጥያቄ መጨረሻ ላይ እንዲያቀርብ ጠይቀው መድረኩን ለጀ/ደምሴ ለቀቁ። ጀ/ደምሴ ረጋ ብሎ ጦሩን እየቃኘ ከጎንና ጎን እየተንጎራደደ ትንሽ ካሰበ በኋላ፦

"አዎ ዛሬ ዋናው ላነጋግራችሁ የፈለግኩበት ምክንያት ሰሞኑን የተከሰቱትን ድርጊቶች በሚመለከት መታረም ያለባቸውን ነገሮች ለማሳወቅና በናንተም በኩል ያሉባችሁን ችግሮች ለመስማት ነው። ሰሞኑን በ------





ግንባር የተደረገው ጨርሶ መደረግም የሌለበት በእውነቱ እንደናንተ ካለ በብዙ ግንባር በእሳት ተፈትኖ ከወጣ ጦር የማይጠበቅ ነው። ይህን ጦር በደንብ ነው የማውቀው። ሐረር ለመጀመሪያ ጊዜ በተሰለፈበት ወቅት እኔ የምሥራቅ ዕዝ አዛዥ ነበርኩ። በጎዴ በ-------በ------እና በ--------- ያደረጋችሁት ተጋድሎና ጀግንነት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ የሚቀይ ነው። ለአገራችሁ የከፈላችሁት መስዋዕትነት እና ያሳያችሁት ጀግንነት የሚዘነጋ አይደለም። ይህ ጦር ጀግና ጦር ነው። የሶማሌ ጦር ፊታችሁ እንደማይቆም ማንም ያውቃል። ታዲያ ይህን ዓይነት የጀግንነት ገድል ያለው ጦር እንዴት ለኤርትራ ወንበዴ የያዘውን መሬት ይለቃል? እያችሁ ግልጽ ያልሆነላችሁ ሶስት የተለያዩ መሠረታዊ የጦር ስልቶች አሉ። መከላከል፣ ማፈግፈግ እና ማጥቃት። እነዚህን ሶስት የጦር ስልቶች በሚገባ መረዳት አለባችሁ። ከመከላከል እጀምራለሁ።" አለ። ሲናገር ሰውነቱ ሁሉ አብሮ ይናገራል። አንዳንድ ቃላቶችን ረገጥ አድርጎ ረጋ ባለ መንፈስ እንደ አስተማሪ ነው ይሚናገረው።

ከወታደሮቹ ውስጥ አንዳንዶቹ በተለይ መኮንኖቹ አልፎ አልፎ ማስታወሻ ቢጤ ጫር ጫር እያደረጉ ያዳምጣሉ። የቀረው ሁሉ በስሜት እፉን ከፍቶ ይሰማል። አካባቢው የስጋት ፀጥታ የሰፈነበት ዓይነት ከጀ/ደምሴ ድምጽ ሌላ የሚሰማ ኮሽታ እንኳን የለም። የጠዋት ፀሐይ ብቅ ብላ ሁላችንንም ትንሽ ሞቅ እያደረገችን ነው። ትንሽ ወደ ግራ እና ቀኝ እያሰበ በዝግታ ራመድ ራመድ ካለ በኋላ፤ ጀ/ደምሴ በዱላው የሌላኛው እጁን መዳፍ መታ መታ አደረገና ንግግሩን ቀጠለ።

“መከላከል ማለት አንድ ጦር ደህና ምሽግ ይዞ አስፈላጊውን የመሣሪያዎች አቀማመጥ ካጠናቀቀ በኋላ ወይ በቂ ኃይል እስኪደርስለት ወይ ደግሞ ትዕዛዝ እስኪሰጠው እየተከላከለ ሲቆይ ነው። በወታደራዊ ሳይንስ የአጥቂና የተከላይ ጦር ሬሾው ሶስት ለአንድ ነው። ይህም የሚከላከል ሰው ቢያንስ ሶስት ሰው መግደል ይችላል ከሚል አስተሳሰብ የመጣ ነው። አንተ ምሽግ ውስጥ ሆነህ ወዳንተ ተጋልጦ የሚመጣን ጦር ስትከላከል አንተን ከምሽጉ ለማስወጣት ወይንም ቦታህን ለማስለቀቅ አጥቂው ካንተ ብዛት ሶስት እጥፍ በላይ መሆን አለበት። ነገር ግን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የኛ ወታደሮች በቁጥር ሳያንሱ ሳይከላከሉ ቦታ የለቀቁበት ጊዜ ብዙ ነው። አየህ የያዝከውን ጠመንጃ እወቀው። መጀመሪያ ጠመንጃህ በደንብ የሚመታው እስከ አምስት መቶ ያርድ ነው። አንተ ገና ወንበዴው በአንድ ሺህ ያርድ ላይ እያለ መተኮስ ትጀምራለህ ወደ አምስት እና ሶስት መቶ ያርድ ላይ ሲደርስ መተኮስ በሚገባህ ሰዓት ሽሽት ትጀምራለህ።”

“ስለዚህ ይህን ነገር አስተውሉ። ያለ አለቃችሁ ትዕዛዝ ቦታችሁን መልቀቅ የለባችሁም። መሣሪያችሁን ደግሞ ከጭንቅላታችሁ ጋር ተጠቀሙበት።” አለና አሁንም ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ በዝግታ ዞር ዞር ካለ በኋላ “ሁለተኛው” ብሎ ጀመረ።

“ሁለተኛው ማፈግፈግ ነው። ልብ አድርጉ፣ በማፈግፈግና በመሸሽ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። መሸሽ የሚለው ቋንቋ እንዲያውም በወታደር ትምህርት ውስጥ የለም። ጥሎ ሸሸ የሚባለው ለሲቪል አምባጓሮ ነው።





አንድ ወታደር የትም ቦታ ጥሎ ሸሸ መባል የለበትም። ለዓላማ እስከተዋጋ ድረስ የሚሸሸው ነገር የለም። ለስልት ብሎ ግን ያፈገፍጋል። ማፈግፈግ ማለት አንድ ጦር በቂ ኃይል ሳይኖረው ቀርቶ ተጨማሪ ኃይል እስኪመጣለት እያንገራገረ ቦታውን ለቆ ነገር ግን ተዋረዱን ሳያጣ የሚቀጥለውን ቦታ ይዞ የሚቆይበት፣ ወይም ሆን ተብሎ ጠላትን መግደያ ወረዳ ለማስገባት ወደ ኋላ እያፈገፈገ ወጥወድ ውስጥ የሚከትበት ስልት ነው።

እና ይህ ሁሉ ሲደረግ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ መውጣት የለባቸውም። ሥነስርዓትና ዲሲኘሊን ባለው መልኩ እያንዳንዱ ወታደር ከጓድ መሪው የሚሰጠውን ትዕዛዝ እየተከተለ፣ ጓድ መሪው ደግሞ እንዲሁ ከበላዮቹ የሚመጣውን ትዕዛዝ እየተከተለ የሚከናወን ነው። እንጂ እዚህ እናንተ እንደምታደርጉት ጨርሶ በወታደር ዓለም ውስጥ የሌለ ሥርዓት አልባነት አይደለም። በእውነቱ በጣም ነው ያዘንኩት። ከናንተ የሚጠበቅ ተግባር አልነበረም የተሠራው። ገና ይሄን የገማ ጎፈሬ ስታዩ ቦታችሁን ጥላችሁ ትሄዳላችሁ። እስኪጠጋህ ድረስ ጠብቀው። ከዚያ ያለህን ሁሉ አርከፍክፍበት። አልፎ ከመጣ በቦንብ አጨማልቀው። ከዚያ ከተረፈ በሳንጃ ተሞሻለቅ። የኢትዮጵያ ድንበር መጨረሻ ይሄ አይደለም። እዚያ ሳንደርስ እንመለስም። እና ይህን ጦርነት ደግሞ እኛ ስንዋጋ የመኖር ፍላጎት የለንም። ሁላችንም ከቤተሰቦቻችን ጋር መኖር እንፈልጋለን። እና ተባብረን ጦርነቱን ጨርሰን ወደቤታችን እንመለስ። ከእንግዲህ ወዲያ መሸሽ የሚባለውን ቃሉንም መስማት አልፈልግም። ከየትኛው የኢትዮጵያ መሬት ወደ የትኛው ነው የሚሸሸው? ጀግና በአገሩ አይሸሽም። ጀግና ግንባሩን

እንኳ ጀርባውን አይመታም። ስትሸሽ የወደቀውን ወንድምህን እንኳ አታነሳም፤ በጣም የሚያስዝን ነው። ከዛሬ ጀምሮ አንድ ሰው ጀርባውን ተመቶ ማየት አልፈልግም። ከወንበዴ ጥይት በሽሽት አመልጣለሁ ብሎ የሚያስብ ጀርባውን ተመቶ ይሞጣና የኔ የደምሴ ጥይት ይጠብቀዋል። የአንድ ሰው መሸሽ ስንት ሰው እንደደሚያስጭርስ ታውቃላችሁ? የሚዋጋ ጦር ካጠገቡ ያሉት ሰዎች ሲሸሹ መዋጋቱን ያቆማል። እና ይሄ የአገር እና የወገን ክህደት ነው። እና ወይ ተዋግተን በጀግንነት እንወጣለን ወይ እየተዋጋን ግንባራችንን ተመተን በጀግንነት እንወድቃለን። ጀግና ግንባሩን ነው የሚመታው!" በማለት ቆም ብሎ ለጥቂት ሰኮንዶች በዝምታ ጠሩ ላይ ኮስተር ብሎ አይኑን ተከለ። ጥቁር ፊቱ ንዴቱን ያገነዋል። የሚመለከተውን ሁሉ ሳይወድ በግድ የፍርሐት ስሜት በውስጡ ይቀሰቅስበታል። ብዙዎቹ ባሉበት ደርቀው ነበር የሚያዳምጡት። አሁንም ጭር ካለ ፀጥታ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ።

"ሶስተኛውና አሁን በሚቀጥለው ግዳጃችሁ ላይ የምትጠቀሙበት ዋናው ስልት ማጥቃት ነው። ስታጠቁ ማድረግ ያለባችሁ ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው ይሄ እጅብ እያላችሁ የምትሄዱትን ነገር ማስወገድ አለባችሁ። የሚደርሱኝን ሪፖርቶች ጠለቅ ብዬ እንዳጠናሁት አብዛኛው ጥቃት የደረሰው እጅብ ብላችሁ በምትሄዱበት ጊዜ በጣም ጥቂት በሆኑ የመድፍ፣ የሞርታር፣ ወይም የላውንቸር ጥይቶች ነው። በያንዳንዱ ወታደር መካከል ቢያንስ ሰባት ሜትር ርቀት መኖር አለበት። ይህን እንዳትረሱ፤ ፃፉት። እንዲያውም በምንም ዓይነት ሶስት አራት ሰው ተጠጋግቶ መሄድ የለበትም።





ጀብ የሆነ እንደሆነ በአንድ ጥይት ብዙ ሰው አያልቅም። ሁለተኛ በምታጠቁበት ጊዜ የምትጓዙት በጣም በከፍተኛ ፍጥነት መሆን አለበት። ማጥቃት እጅግ በጣም በከፍተኛ ፍጥነት ይጠይቃል። መሸጎ የሚጠብቀው ጠላት ለመከላከል የማያስፈልገውን ጊዜ መስጠት የለብንም። በጣም ፈጣን በሆነ መንገድ አንድ ሰው ሳያቅማማ ወደፊት መገስገስ አለባችሁ። የጓድ መሪዎች ተነሱ!" ብሎ ንግግሩን የጓድ መሪዎች እስኪነሱ ገታ አደረገ። ከያሉበት ተነስተው ቆሙ።
"እዎ እናንተ በሥራችሁ ያሉትን ሰዎች ከኋላ ሆናችሁ እየተቆጣጠራችሁ መሄድ አለባችሁ። ለመሆኑ ስንታችሁ ናችሁ ሥራችሁ ያሉትን ሰባት ወይ ስምንት ሰዎች ስም የማታውቁት? አዎ ትኖራላችሁ። ከእንግዲህ ወዲያ የደረሱበት አልታወቀም የሚባል ሪፖርት እንዲቀርብልኝ አልፈልግም። እያንዳንዳችሁ በስራችሁ ላሉት ሰዎች ተጠያቂዎች ናችሁ። እያንዳንዳቸው ማድረግ የሚችሉትንና የሚሳናቸውን ታውቃላችሁ። እንደ ችሎታቸው የሥራ ድርሻ እየሰጣችሁ ወደፊት መጓዝ አለባችሁ። የቆሰለ ወይም የተሰዋ በአፋጣኝ እንዲነሳ የማድረግም ኃላፊነት የናንተው ነው። ለእናት አገሩ የወደቀ ሰው የማይታወቅ ወይም ለእናት አገሩ ሲዋጋ የደረሰበት በማይታወቅ ጀግና ከእንግዲህ አይኖርም። የጓድ መሪ በጣም ትልቅ ኃላፊነት አለበት። ኃላፊነታችሁን መናቅ ወይም መዘንጋት የለባችሁም። ወታደሮቻችሁን ወደፊት አስቀድማችሁ በፍጥነት ማጥቃት መቻል አለባችሁ። በስራችሁ አንድ ሰው እንኳን ለመሸሽ ቢሞክር እየመታችሁ ወደፊት መቀጠል አለባችሁ። ማጥቃት ከተጀመረ በኋላ ወደ ኋላ ማለት በምንም ዓይነት የለም። ወደፊት በፍጥነት መጓዝ! ጦር ሜዳ ላይ፡ ፍጥነት

ለአደጋ የሚያጋልጥ ሳይሆን ከአደጋ የሚያድን ነው። ይኸው ነው መቀመጥ ትችላላችሁ።" ብሎ የተሰበሰቡትን ተመለከተ። የጓድ መሪዎቹ ትዕዛዝ መቀበላቸውን ሰላምታ እየሰጡ ገልጸው ተቀመጡ። በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ። የአባቴ ንግግር ትንሽ ከበደብኝ። የወታደሮቹም ሥነስርዓት አስገረመኝ። በንግግሩ ጠንካራነት በመበሳጨት ፊንታ በወታደሮቹ ፊት ላይ ከውስጥ ፈንቅሎ ለመውጣት የተቃረበ የወኔ ሲቃ ነው የሚነበበው። አንዳንዶቹ እንዲያውም ባሉበት መርጋት አቅቷቸው በወኔ ባሉበት ይቁነጠነጣሉ።

ጀ/ደምሴ አሁንም ዞር ዞር አለና። "ሌላው ላሳሰባችሁ የምፈልጋቸው ሁለት ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ አንድ ቦታ በምትይዙበት ጊዜ የምታደርጉትን ጭፈራና ዳንኪራ ጨርሶ ማቆም አለባችሁ። ቦታ ከአስለቀቅን በኋላ ለወደቁት ጀግና ኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን ሥነሥርዓት ፈጽመን ወዲያውኑ ወደ ጥበቃና ምሽግ ማጠናከር ተግባር መስማራት አለብን። ብዙ ጊዜ ጠራችን ቦታዎችን ካስለቀቀ በኋላ ለሚመጣው መልሶ ማጥቃት ሳይዘጋጅ እየቀረ በብዙ ጀግኖች ደም እና መስዋእትነት የተገኘውን ድላችንን ጠብቀን ማቆየት ያልቻልንበት ጊዜ አለ። እና ራሳችሁን ካልጠበቃችሁ ማንም ሊጠብቃችሁ አይችልም። ድግስና ጭፈራ ወንበዴን ከኢትዮጵያ ድንበር ስናጠፋ እንደርስበታለን። እስቲ በ-----ግንባር ብርጌድ መሪ ተነስ?" ከማለቱ አንድ ሻምበል ተነስቶ ሰላምታ ሰጠና ስሙን ከነማዕረጉ ተናገረ።

"ወንበዴዎች ባንተ ግንባር አንድ ሺህ ሜትር ላይ ነው አይደለም ያሉት?" አለው። ጀ/ደምሴ በያዘው በትር መኮንን የግንባሩን አቅጣጫ እያሳየ።





"ትክክል ነው ጌታዬ" አለ ሻምበሉ በተጠንቀቅ ቆሞ።

"ታያቸዋለህ? እንደው በመነጽር እንኳ ይታያሉ?" አለው ጀ/ደምሴ አትዋሸኝ በሚል አኳኋን።

"አናያቸውም ጌታዬ። በቃፊር ነው እንቅስቃሴ ካለ የምንቆጣጠረው።" አለ ሻምበሉ ፈርጠም ብሎ።

"አያችሁ?" አሉ ጀ/ደምሴ የወንበዴዎቹ አለመታየት የተለየ ነገር እንደሆነ ሁሉ። ቀጠለና

"እነሱ አይታዩም። አታዩዋቸውም። ያንተስ ወታደሮች ይታያሉ? እሳት ያነዳሉ? ወይ በማታ ሲጋራ ያጨሳሉ? የሚያዩዋችሁ ይመስልሃል?" አለው ጀ/ደምሴ ሻምበሉን ትክ ብሎ እያየ።

"ትክክል ነው ጌታዬ! የኔ ወታደሮች ሊታዩ ይችላሉ።" አለ አሁን ፈራ ያለ ይመስላል።

"ይሄንን ነው የምለው። እናንተ የመንግሥት ወታደሮች ስለሆናችሁ እንደፈለጋችሁ መሆን የምትችሉ ይመስላችኋል። ይሄ ጦር ሜዳ ነው። ጦር ሜዳን ካላከበሩት ያዋርዳል። ስለዚህ አክብሩት። ጭስ አታጭሱ፣ አለመታየት መቻል አለባችሁ። ወታደር ካልታየ አይተኮስበትም፣ ካልታየህ አትሞትም። ብቻህን እንኳን ብትሆን አለመታየት ከቻልክ ጠብቀህ መግደል ትችላለህ። ስለዚህ አለመታየት ዋናው ነው፣ አትታዩ!! እኛ በምንችለው ሁሉ አስፈላጊውን ለሟሟላት እንሞክራለን። ለእናት አገራችን አንድነት የሚጠበቅብንን መክፈል ግዴታችን ነው። አሁን በእናንተ በኩል ያለውን አስተያየትም ሆነ ጥያቄ እቀበላለሁ። ከዚህ በኋላ እስክንገናኝ ምናልባት

ትንሽ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ ያላችሁን ጥያቄ ሁሉ ዛሬ ለመጠየቅ ብትሞክሩ ጥሩ ነው" አለ ጥያቄ በሚጋብዝ አይነት ረጋ ባለ ድምፅ። በንግግሩ መሐል ጭብጨባ ተከልክሎ የነበረ ቢሆንም አሁን ጭብጨባው ከዳር እስከዳር አስተጋባ። ወዲያው እንዲያቆሙ ምልክት ተሰጣቸው ጭብጨባው ወዲያው ቆመ።

ወደ መሬት የተወረወረ የመብረቅ ብልጭታ የሚመስለው የፀሐይዋ ጨረር ለቀኑ ቢጫ ቀለም ሰጥቶታል። ጠዋት የነበረው ብርድ በፀሐይዋ ተሟሙቆ ከቦታው የለም። ሰሜናዊ ነፋስ ከተራራው አናት ላይ ያለችውን ዛፍ ያወዛውዛታል። የጠሩም ልብ እንደዛፍዋ የሚንዥዋዥው መሰለኝ በአካባቢው ከባድ ጸጥታ በቅጽበት ሰፈነ። ጥቂት እጆች ከተሰበሰቡት መሃል ብቅብቅ ማለት ሲጀምሩ ጀ/ደምሴ መጀመሪያ እጁን ወዳወጣው ሰው በበትሩ መኮንኑ እያመለከተ "እሺ እዚያ ጋ!" አለ። ለመስማት አንድ ሁለት እርምጃ ወደፊት እየተራመደ። ወታደሩ ተነሳና ግጥም አድርጎ ሰላምታ ሰጠ።

"መ/አለቃ አገሌ መለያ ቁጥር----በ---ብርጌድ የ-------ሻለቃ አዛዥ፤ የኔ ጥያቄ መሣሪያን በሚመለከት ነው። የማዘው ጦር እንዲሁም በሌሎች ሻለቃ ጦር ውስጥ ከፍተኛ የከባድ መትረየስ እጥረት አለብን። እና ይህንን ችግር እርስዎ እንዲረዱትና ተጨማሪ ከባድ መትረየሶች እንዲሟሉልን ለመጠየቅ ነው" ብሎ እንደገና ሠላምታ ሰጥቶ ቆመ።

ጀ/ደምሴ ትንሽ ትኩር ብሎ ካየው በኋላ "ጥሩ ነው፤ ነገር ግን ስንት ከባድ መትረየሶች ነው ያለህ ከነዓይነታቸው?" ብሎ ጠየቀው። መ/አለቃው ቁጥሩን መለሰ።





"እሺ ተጨማሪ ያስፈልግሃል። ነገር ግን ባለፈው ውጊያ ምን ያህል ከባድ መትረየሶችን ጥላችሁ እንደመጣችሁ አትዘንጋ። እኛ እናንተን ስናስታጥቅ እዛንተ ደግሞ ወንበዴን የምታስታጥቁ ከሆነ ምን ትርጉም አለው? መሣሪያችሁን እንኳን ሳትይዙ ነው ቦታ ለቃችሁ የምትመጡት። እና የዚህ ዓይነት ድርጊት ከእንግዲህ ሊፈፀም አይችልም። ማንም ወታደር መሣሪያውን ሳይዝ ቦታ ለቆ መሄድ የለበትም። መንገድ ላይ እንኳን ከጠሩ ብትቀረጡ ራሳችሁን የምትከላከሉበት መሣሪያ እንኳን የላችሁም። ጥሩ ነው የመትረየሶች ዓይነት ይጣራ። አሁን----- ኤ. ፎር መትረየሶችና ------- ኤ. ሲክስ መትረየሶች፤---- መትረየሶች ለየብርጌዱ እንዲዳረሱ ይደረጋል። ሌላ ጥያቄ።"

"እሺ፣- እዚያ ጋር ቀጥል!" አለ ጀ/ደምሴ። ንግግሩ አንዴ የቁጣ አንዴ ደግሞ የአስተማሪ አይነት ነው።

ወታደሩ ተነሳና "ምክትል አስር ዓለቃ ----በ ----ብርጌድ------- ሻለቃ የ--- ሻምበል አዛዥ" ሲል የም/አስር/አለቃ የሻምበል ጦር ማዘዙ ገርሞኝ አተኩሬ ተመለከትኩት። እውነትም የጠሩ ተዋረድ ተመስቃቅሏል አልኩ። ም/አ/አለቃው ቀጠለና "የኔ ጥያቄ በመገናኛ ሬዲዮ ላይ ያተኮረ ነው። የመገናኛ ሬዲዮኖች እጥረት አሉብን። ከዚህ በፊት ከጠሩ አልፈን ሄደን የወንበዴ ጉሮሮ ለመያዝ ትንሽ ቀርቶን ሳለ መገናኛ ባለመኖሩ እቦታው ላይ መድረሳችንን ለመድፈኞቻችን ማሳወቅ ስላልቻልን፤ ጓደኞቻችን በወገን መድፍ ተደብድበዋል። እና በዚህ ረገድ ከፍተኛ ችግር ደርሶብናል ጌታዬ" አለና ባለበት ቆሞ ቀረ።

"እዎ የዚህ ዓይነት ድርጊት ሲሆን ጨርሶ የማይገባ ነው የመገናኛ ሬዲዮኖች ችግር በዚህ ጦር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ክ/ጦሮች ያለ ነው። እኔም አዲስ አበባ በየጊዜው ደጋግሜ ይህን አስታውቄለሁ። የሚያስፈልገውንም ዝርዝር አቅርቤ በየቀኑ እየተጨቃጨቅኩ ነው። ነገር ግን ይቺ በጦርነት የላሸቀች አገራችን ልትሰጠን የምትችለው የተወሰነ ነው። ለአንድ ክ/ጦር ብቻ የተለየ ትጥቅ ልንሰጥ አንችልም። ሁሉም እኩል ነው የሚያገኘው፤ እናንተም ከሌላው ያነሰ የላችሁም። እና ይህ ችግር በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈታል ብዬ የማስበው አይደለም። ነገር ግን የተቻለንን ጥረት ሁሉ እናደርጋለን። እስከዚያው ድረስ ባላችሁ መጠቀም ይኖርባችኋል።" አለ ጀ/ደምሴ በሁኔታው ከአቅም በላይ መሆን የተሰማውን ብስጭት በሆዱ አምቆ የንዴት እርጋታ ከተረጋጋ በኋላ።

ጥያቄውን የጠየቀው ወታደር ወዲያው ቀጠል አርጎ "ልክ ነው ጌታዬ አገሪቷ ያለችበት ደረጃ ሁላችንም የምናውቀው ነው። እና እኛም ሁሉን ነገር ከአገራችን መጠበቅ አንችልም። ስለዚህ የመገናኛ ሬዲዮ ለምናደርገው ትግል ወሳኝነት እንዳለው ጠንቅቀን የተረዳን ስለሆነ ከደሞዛችን ተቀርጦ ለሬዲዮ መግዣ እንዲውል እኔ በኔ በኩል ፈቃደኛ መሆኔን በዚህ ደቂቃ አረጋግጣለሁ" ሲል የተቀመጠው ሁሉ ጭብጨባውን አቀለጠው። ይህ ለውዬ ጤነኛ አይደለም እንዴ? አልኩና በሆዴ የሚቀጥለውን ለመስማት በጉጉት ጠበቅኩ።

ጀ/ደምሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የደስታ ፈገግታ አሳየ። ቀጠለናም-





"በእውነቱ ሞራልህ የሚያኮራ ነው። ነገር ግን እናንተ የኢትዮጵያን አንድነት በደማችሁ ለማስከበር የተነሳችሁ ዜጎች ከምታገኟት አነስተኛ ደሞዝ ላይ ለመገናኛ ሬድዮ መግዣ የምታዋጡበት ደረጃ ላይ ገና አልደረስንም። ችግራችሁ ይገባኛል። የኔም ችግሬ ነው። እናንተ የምትጠይቁኝን ያህል እኔም አለቆቼን እጨቀጭቃለሁ።" ወዲያው አስከተለና "ለመሆኑ የሥራ ድርሻህ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀው።

"የ------ ሻምበል መሪ ነኝ ጌታዬ!" አለ በተጠንቀቅ እንዳለ።

"መቼ ነው ም/አ/አለቃ የሆንከው?"

"በሰባ ሶስት ነው ጌታዬ" ብሎ መለሰ።

"የብርጌዱ አዛዥ ማነው? እዚህ አለ?" አለ ጀ/ደምሴ ቀጣ ብሎ። "አለሁ ጌታዬ ሻምበል ------የ------ ብርጌድ አዛዥ" አለ ቀሞ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ።

"ለምንድነው ያልተሾመው?"

ሻምበሉ መልስ እንደሌለው በዝምታ ገለጸ።

"ግዳጁን በሚገባ ያከናውናል? ምን አስተያየት አለህ?" አለው ሻምበሉን አሁንም አትኩሮ እየተመለከተው።

"አዎን ጥሩ መሪ ነው ጌታዬ። ምንም ተቃውሞ የለኝም"

"በል ከአሁን ጀምሮ የሃምሳ ዓለቃ ሆነሃል" አለ። ጀ/ደምሴ ወደ ቀድሞው ም/አ/ዓለቃ ዞር ብሎ እሱም በደስታ በቀለጠ ጭብጨባ ታጅቦ ሠላምታ ከሰጠ በኋላ ተቀመጠ።

"እንደዚህ ዓይነት ወኔ ያላቸውና አገራቸውን በቅንነት የሚያገለግሉ ወታደሮች በምንም ዓይነት ይህን ያህል ጊዜ ሹመት ሊያልፋቸው አይገባም። በሥሮቻችሁ ያሉትን ሰዎች በሙሉ የማሳደግ ኃላፊነት የናንተ

ነው። መታለፍ የሌለባቸውን ሰዎች ብዙ ጊዜ ሞራላቸው እስኪላሽቅ ድ እየታለፉ ይታያል። በዚህ ጉዳይ ላይ ብታስቡበት ጥሩ ነው። ሌላ ጥ. ያለው" አለ። አንዱ እጁን አወጣ።

"እሺ ጠይቅ"

"ወታደር እገሌ ----ብርጌድ ----ሻለቃ----ሻምበል መለያ ቁጥሬ -- ፤ ጥያቄ የጠመንጃ ቅባትን በሚመለከት ነው። የጠመንጃ ቅባት እጥረ አለብን"

"ምንድነው የምትለው? የጠመንጃ ቅባት እጥረት ሲወራ ዛሬ ገና መስማ ነው። የድርጅት ክፍልህን አትጠይቅም እንዴ። ማነው የድርጅት ኃላፊ ተነስ!" አለ በንዴት ዓይኑ የተቀመጡት ላይ አፍጥጦ። አንድ መቶ ዓለ ተነሳና ቆመ።

"የጠመንጃ ቅባት የለህም እንዴ?"

"ኧረ አለን ጌታዬ። እንዲያውም እጥረት ኖሮን አያውቅም"

"እንደዚህ ዓይነት ተልካሻ ነገር እኔን አትጠይቁኝ። እየህ ይሄ በመቶ ዓለ ደረጃ የሚያልቅ ነው። ወይ የክ/ጦር አዛዥህን መጠየቀም ትችላለህ። አለው አሁንም በንዴት።

"እሳቸው ጋር ስለማልደርስ ነው ጌታዬ" አለ ወታደሩ።

"ታደያ እኔ ጋር ነው የምትደርሰው?" አለው። የተቀመጠው ሁሉ ባንደ በሳቅ አለቀ። ጀ/ደምሴም ፈገግ ብሎ ወደ ኋላ ዞር አለና ቆመው ወደ ነበሩት የክ/ጦሩ አዛዥ እየተመለከተ "አታነጋግራቸውም እንዴ?" አለውና መልስ ሳይጠብቅ እንደገና ዞር ብሎ "አያነጋግራችሁም እንዴ?" አለ።

"ያነናጋግሩናል" በማለት ሁለም በኅርናና ድምጽ መለሱ።





"በል ቅባትሕን በኋላ እዚሁ እነጋግረህ መቀበል ትችላለህ። ሌላ ጥያቄ፤ ስለ ተራ ነገሮች ሳይሆን እኔን የሚመለከት ጥያቄ ጠይቁ። እሺ... እዚያ ጋ አንተ!"

"ሁለት የውሃ ቦቴዎች ብቻ ነው ያሉን። እና አንዳንዴ ጠሩ ወኔ ሳያንሰው መሣሪያና ጥይት ሳይጎለው ወንበዴ ሳይሆን የውሃ ጥም ሲፈታው ይታያል። በዚህ ችግር ላይ የሚቻልዎትን እንደሚያደርጉ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ" አለና ተቀመጠ።

"አዎ የውሃ ቦቴ አሁንም ችግር አለብን። ነገር ግን ወደዚህ ስመጣ አንድ ቦቴ አዝዤላችሁ ነው የመጣሁት፤ ለጊዜው እሱ ይረዳችኋል። በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ደግሞ እንዲሁ ሌላ አንድ እጨምርላችኋለሁ። ችግሩ ቦቴዎቻችን እየተመቱና በመንገድ እየተሰበሩ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ጥገና ላይ ነው የሚያሳልፉት። አዳዲስ ቦቴዎች እየመጡልን ነው። ስለዚህ በዚህ አኳያ ችግር አይኖርባችሁም"

"ሌላ ጥያቄ ያለው አለ?" አለና ትንሽ ጠበቀ፤ የሚጠይቅ አልነበረም።

"እሺ እንግዲህ እስካሁን የሰማችሁትን በተግባር እንደምታውሉት እርግጠኛ ነኝ። ከእንግዲህ የምንገናኘው አፍአበት ላይ ነው። ከእንግዲህ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ የሚባል ቋንቋ አይኖረንም፤ መልካም ዕድል!" ብሎ ጠሩን ተሰናበተ። ጠሩም አፀፋውን ሰጠ።

ጠሩን ሲሰናበት ፈገግታው አባታዊ ስሜቱን ለያንዳንዱ ወታደር የሚያስተላልፍ ይመስላል። በአካባቢው ያለው ሁሉ ሳይነካካ የተቃቀፈ መሰለኝ። ሁላችንም በስሜት ተቃቅፈን፣ በስሜት ተለያየን። እነሱ ወደ

አፋቤት ለመድረስ ወደሚገጥማቸው ፍልሚያ፤ እኔ ደግሞ የእረፍት ወ
መስብሰቢያ ሽርሽር።





OOOO

ከመሳህሊት ተነስተን 18ኛው ተራራ ክ/ጦር የሚገኝበት ግንባር ጉዞ ጀመርን። የወጣነውን ተራራ መኪኖቹ ዝግ ብለው ይወርዳሉ። አብረውን የነበሩት ጀ/ቁምላቸው ከጋዜጠኛው አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ጋር ጨዋታ ብጤ ጀዘዋል። ወደ ውጭ እየተመለከትኩ ስጓዝ አህያ እየነዱ የሚጓዙ ሁለት ሰዎች አየሁ። በአካባቢው ሰው ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። እንዴት እዚህ ዓይነት ቦታ ውስጥ የስጋት አየር እየተነፈሱ እንደሚኖሩ ግራ ገባኝ። የማይለመድ ነገር የለም። የጥይቱም ጩኸት ሲለመድ እንደ ሙዚቃ አብሮ ሙዚፈን ሊመጣ ይችላል። ኢትዮጵያዊ ብርቱ ዜጋ ነው። ለዚህም ይሆናል ጦርነቱ አላልቅ ያለው። አንደኛውን ተራራ ወርደን የሚቀጥለው ላይ ወጥተናል። ጉዞአችን በጥቂት ቀናት ውስጥ ግዳጅ የሚላከው ለ18ኛ ክ/ጦር ስለሚጠበቅበት ኃላፊነት ገለጻ ለማድረግና በተዘጋጀውም እቅድ ላይ ለመነጋገር ነበር።

ውስጥ ለውስጥ የተሰራውን አቧራማ መንገድ ለቀን ወደ ዋናው የከረን-አስመራ አስፋልት መንገድ ውስጥ ገብተናል። የመንገዱ አስፋልት ፈራርሶ ወደ ጠጠራማነት እየተሸጋገረ ነው።

አልፎ አልፎ ወታደር የጫኑ ግልጽ ከባድ መኪኖች በዝግታ ሲጓዙ ቀም ብለን አይተናቸው እናልፋለን። ወደ ሰሜን እየራቅን በሄድን ቁጥር ደግሞ ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቶ ጭራሹን በመንገድ ጥበት የተነሳ

አንድ ቦታ ቆምን። ከባድ መኪኖችና ታንኮች ቅጠሎች ባዘሉ ቅርንጫፎች እየተሸጎረጎሩ ቆመዋል። በታንኮች ጥግ ጥግ ላይ ወታደሮች በግዴለሽነት ተሳፍረው ወደ ፊት እያዩ በዝግታ ይጓዛሉ። ከፊታችን የነበረው መትረየስ የተጠመደበት ዋዝ መንገድ እያስለቀቀ መርቶን ከትርምሱ አወጣን።

ወደ ጎን መገንጠያ መንገድ ውስጥ ስንገባ ቀኑ ወደ 6 ሰዓት ደርሶ ነበር። አሁንም ተራሮችን እየቧጠጥን ነበር የምንጓዘው። የሰሜን ተራራዎች ብዙ የተወራላቸው ቢሆኑም ሄዶ ለሚያያቸው አስገራሚ ናቸው። አንድ ተራራ ከሌላው ጋር ዝምድና ያለው ይመስል አንድ አካባቢ ተኮልኩለዋል። የሜዳ ናፍቆት ከዚያ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ ስሜት ነው። ሜዳ ናፈቀኝ። እንደ አባቴ የትውልድ ሰፈር፣ የቢላቻ ሜዳ፣ ለጥ ያለ፣ ውጣ ውረድ የሌለው፣ የሰላም አየር የሚነፍስበት ሜዳ፣ ሰውነትን አጉላልቶ መንፈስን የማይወጥር ሜዳ...

ተራራው አናት ላይ ለመድረስ ትንሽ ሲቀረን ወታደሮች ማየት ጀመርን። ማንነታችንን እንዳወቁ ሁሉ ምንም ሳይጠይቁን ጨፌ ላይ ወጣን። ከመኪኖቹ ስንወርድ ምርኩዝ ብጤ የያዙ ረዥም ኮሎኔል ከሌሎች መኮንኖች ጋር ቀርበው ተቀበሉን። ኮሎኔል በኃይሉ ከንደ (በኋላ ብ/ጀነራል) ይባላሉ። ጠይም ፊታቸው በከፊል ጠቆር ባለ የፀሐይ መነጽር ተሸፍኗል። ሰውየው እዚህ በረሃ እንደከረሙ ጠቅላላ ሁኔታቸው ይመሰክራል። ራቅ ብሎ ሰብሰብ ብለው የተቀመጡ ወታደሮች የአንዱን ካድሬ ንግግር ያዳምጣሉ። ከሰላምታው በኋላ ጀ/ደምሴ ዞር ብሎ "ምንድነው እዚያ የሰበሰባችሁት?" አለ።

"ንቃት እየተሰጣቸው ነው ጌታዬ" አለ አንደኛው።





"የምን ንቃት ነው የምትሰጡት?ጥራው ካድሬውን" አለ በቁጣ። ካድሬው ተጠርቶ ቀረበ።

"ምን እየሠራህ ነው?" አለው ረጋ ብሎ።

"ንቃት እየሰጠን ነው ጌታዬ?" አለ ወታደሩ ቀስ ብሎ።

"ምን? የፖለቲካ ንቃት?" አለና በጎን ተመለከተው። መልስ አልሰጠም።

"በሉ ከዛሬ ጀምሮ እነዚህ ደክሞአቸው የሚመጡትን ወታደሮች ንቃት እንሰጣለን እያላችሁ ስትሰበስቡ እንዳላይ። እስከዛሬ በቂ ንቃት ተሰጥቷቸዋል። አሁን ከወታደራዊ ትምህርት ሌላ ምንም ዓይነት ንቃት አያስፈልጋቸውም። ይኸው ነው መሄድ ትችላለህ!" ብሎት ወደ ኮሎኔል በኃይሉ ዞር አለና "በኃይሉ ለነብር አይመትሩም፣ ለጎበዝ አይነግሩትም ይባላል። እና እዚህ ጦር ፊት ወንበዴ እንደማይቆም የታወቀ ነው። ስለዚህ ወታደሮቹን ማነጋገር አያስፈልገኝም። እኛ ብቻ ስለ እቅዱ መወያየት እንችላለን። እነሱ እረፍት ያድርጉ።" ብሎ ፈገግ እያለ መንገድ ቀጠለ። ኮ/በኃይሉ በያዙት ዱላ መሬት እየደቁ ወደ አንድ በጭራሮ የተሸፈነች ጎጆ ቤት አመሩና በሯን ከፍተው እንግዶቹ እንዲገቡ ጋበዙ። የመጡት ሁሉ ተያይዘው ጎጆ ቤቷ ከገቡ በኋላ በሯን መለስ አደረጓት።

በአካባቢው የጭራሮ ቅርንጫፍ ክምር የመሰሉኝ ሁሉ ቤቶች መሆናቸውን አጣራሁ። የሚገርም ነው። በሩቅ ለሚያያቸው ቀርቶ እዚያው አፍንጫዬ ሥር ሆነው አይለዩም። እነሱ ስራቸውን እስኪጨርሱ አካባቢዋን ለማየት ዞር ዞር ማለት ጀመርኩ። ከመጣነው ውስጥ ከስብሰባው ያልገባነው እኔ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እና አጃቢዎቹ ብቻ ነበርን። ከተራራዋ

ዙሪያ በጭራሮ የተሸፈኑ ጉድጓዳ ቤቶች ይታያሉ። መለስተኛ ዘርዘር ያለ ቅጠል የለሽ ዛፎች በየቦታው ይታያሉ። በረሃ ብትሆንም ደመቅ ያለች ነፋሻማ እና የደስ ደስ ያላት ተራራ ናት። ከአንድ ዛፍ ሥር ቁጭ እንዳልክ ፀጥታውን ስንጥቆ የሚጎዝ ለስላሳ የዘፈን ጽምጽ ሰማሁ።

"How long
Before you let me know you
Before you let me show you
All I have in my mind
Cause, you are…

ኬኒ ሮጀርስ የተባለው አሜሪካዊ የሚዘፍነው የእንግሊዘኛ ዘፈን ነበር። በጣም ገረመኝ። ዘፈኑን ከዚያ በፊት ሰምቼው የማውቅ በመሆኑና የዚህ ዓይነት ቦታ ላይ ልሰማው መቻሌ በጣም አስገረመኝ። ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ዘፈኑን እየተከተልኩ መሄድ ጀመርኩ። ትንሽ ሄጀ አንድ የጭራሮ ጎጆ ጋር ስደርስ ቆምኩኝ። የቴፕ ሪኮርደር ነበር የሚጫወተው። አምስት ወይ ስድስት የሚሆኑ ወጣት ልጆች ቴፑን ከበው ያዳምጣሉ። ከከተማ ለብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ከሄዱት ስለመሆናቸው አልተጠራጠርኩም። በማላውቀው ምክንያት አቦታው መቆየት አልቻልኩም። ወዲያው ወደመጣሁበት በዝግታ ቀይ ሸሮ የመሰለውን መሬት እየደቃሁ ተመለስኩ።

የአባቴ አጃቢ የአስር አለቃ ጌታቸው ከአንድ ዛፍ ስር ቆሞ ዙሪያውን ይቃኛል። ወደሱ ሄድ ብዬ ስለ አካባቢው ሁኔታ መጠየቅ ጀመርኩ።

"አሁን ሻዕቢያ ከዚህ ምን ያህል ርቀት ላይ ይገኛል?"





"ብዙም አይርቁም እዚያ በሩቅ የምታየው ተራራ አካባቢ ናቸው።" አለኝ።

"እዚሁ?" ብዬ በመገረም አየሁት።

"አዎ ብዙ ሩቅ አይደሉም" አለኝ።

"ሆሆ ለካስ ያለሁበት ቦታ የዋዛ አይደለም" አልኩና በሩቅ ወደሚታየው ተራራ አማተርኩ። ረሃብ ትንሽ ጀማምሮኝ ነበርና ተራራውን መመልከት ትቼ የመሰብሰቢያዋን ጎጆ መመልከት ያዝኩ። ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ከተነጋገሩ በኋላ የጎጆዋ ጭራሮ በር ተከፈተና ሁሉም መውጣት ጀመሩ።

"ያው እንግዲህ ቅድመ ዝግጅቱን ካሁኑ ጀምሩ ምንም ሊገጥማችሁ የሚችል ችግር አይታየኝም።" አለ ጀ/ደምሴ። አካባቢውን ለመቃኘት በጭራሮ የተሸፈኑትን ጎጆዎች አልፈው እየሄዱ እኛም አብረን ተከተልን። ወደ ተራራው ጥግ ጋር እንደ ደረስን እስካሁን ያላየኋቸው ታንኮችና ቢ.አር.ዲ.ኤም ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች በቅጠል ምስል በተሰራ ጨርቅ ተሸፍነው እዚም እዚያም ቆመዋል። ሮኬት የሚተኩሱ ቢ.ኤም.21 ተሽከርካሪዎችም አልፎ አልፎ እንዲሁ ቅጠል መሰል ጨርቅ ለብሰው ይታያሉ። አፋፍ ላይ ቆመው ትንሽ ከተነጋገሩ በኋላ ለሚጠበቀው ወሳኝ ውጊያ ዝግጅቱ በጥንቃቄ እንዲካሄድ ትዕዛዝ እየሰጡ ወደ መኪኖቹ አመሩ።

ኮ/በኃይሉና መኮንኖቹ ከዐይን እስኪጠፉ ድረስ በመስኮት ስመለከት የሚጠብቃቸው መራራ ትግል በአእምሮዬ መነሁለል ጀመረ። እንደሰበሰብኩት መረጃ ከሆነ ከሁለት ወይም ሶስት ቀናት በኋላ ሊደረግ የታቀደው ጦርነት ለተከታታይ እንቅስቃሴዎች ወሳኝ እንደሆነና በከፍተኛ ደረጃ ጦርነቱ የሚካሄደው አጋሮ በተባለው በተራራማ ቦታ ላይ ነው። አጋሮ ሻዕቢያ ደህና አርጎ የመሸገበት ተራራ ከመሆኑም በላይ፣ የተደራጀ ጥቃት

ቢሞክርበት ተጨማሪ ጦር አምጥቶ የሚከላከለው በምንም ዓይነት በቀ የማይለቀው ቦታም ነው። የኢትዮጵያም ጦር የከረንን ከተማ ከተደጋጋ ጥቃት ፍጹም ነጻ ለማድረግም ሆነ አፍአበትን እንደገና በቁጥጥር ለማዋል ካቀደ የአጋሮንና አካባቢውን ተራሮች ከወንበዴ ነፃ ማድረ ነበረበት። ስለዚህ በጣም በተቀናጀ መልኩ ከባድ ውጊያ በጥቂት ቀና ውስጥ ለማድረግ ታቅዷል። የጦርነቱን ጠቅላላ ዕቅድ ለማወቅ ባልችል ቢያንስ ሁለት ወይም ሶስት ክፍለ ጦሮች እንደሚሳተፉበት እስከ አሁ ካየሁት ገምቻለሁ።

ሙዚቃ ሲያዳምጡ የነበሩት ወጣቶች፣ ኮ/በኃይሉ እና መኮንኖ ባንድ ላይ በሃሳቤ መጥተው ተደረደሩ። አሳዘኑኝ። አሁን እነዚሀ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ያስታውሳቸው ይሆን? እያልኩ ስለነሱ ብዙ አሰብኩ።

ተራራውን ወርደን ስንጨርስ ከሃሳቤ ባነንኩና የሰሜኑን በረ መቃኘት ገባሁ። ፀሃይዋ አናት መብሳት ካቆመች ትንሽ ጊዜ አልፏል፤ የሆዴም ጩኸት በጊዜው ልክ እየጨመረ ነበር። ዋናው መንገድ ላይ ከወጣን በኋላ ወደ ኢላበረድ አመራን። ምሳ ኢላበረድ መንግሥት እርሻ ተቋም ውስጥ ተዘጋጅቶ ይጠብቀን ነበር። ረሃቡ ነው መሰለኝ መንገዱ ትንሽ ረዘመብኝ።

ኢላበረድ ከሚገኘው የመንግሥት እርሻ እንደ ደረስን በቀጥታ ወደ ተዘጋጀው የምሳ ግብዣ እየመሩ ወሰዱን። የቀኑ ውጥረትና ድካም በኢላበረድ ውበት እንደታጠበ ሁሉ የሁሉም ፊት በመዝናናት ስሜት ፈካ ብሏል። ሁሉም አልፎ አልፎ ብቻ እየተነጋገረ ተመገበ። ምሳ ተበልቶ እንዳለቀ፤ ጀ/ደምሴ አጠገቡ ተቀምጦ ወደ ነበረው የእርሻው ኃላፊ ዞር





ብሎ "ችግር አለብን ያልካቸውን ነገሮች አሁን ልንወያይ እንችላለን" አለው።

"አዎን እንግዲህ ተዘዋውረው እንዳዩት ከወይን ጠጅ እስከ ተለያዩ ፍራፍሬዎች እንዲሁም የከብት ሥጋ ምርት ትልቅ አሥተዋጽኦ እያደረግን ነው። አሁን የምንጠይቀው መደበኛ ወታደሮች በጥበቃ እንዲሰጡን፣ በተለይ ወታደሮች በዚህ በሚያልፉበት ጊዜ እርሻዎች ውስጥ አለአግባብ እየገቡ ምርታችንን እንዳያበላሹ የሚጠብቁ ወታደሮች እንፈልጋለን።" አለ ኃላፊው ለስለስ ባለ ድምፅ።

"ወታደሮች በብዛት እርሻ ውስጥ እየገቡ ምርት ያበላሻሉ ነው ያልከኝ" አለ ጀ/ደምሴ። የእርሻው ኃላፊ የአነጋገሩን ድምጸት ስላልወደደው የተናገረውን ለመድገም ካቅማማ በኋላ
"አዎ አ...ከስነሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ እየገቡ ብዙ ጊዜ ምርት አበላሽተውብናል" አለ።

ጀ/ደምሴ "ይሄ በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። እሸት ታይቶ አይታለፍም ሲባል አልሰማህም?" አለና ፈገግ ካለ በኋላ "ያንተ ችግር ይገባኛል። ነገር ግን እነዚህ ወታደሮች ናቸው። እናንተ እዚህ እንድትሠሩ የሚታገሉት፣ ለአገራቸው ደምተውና ተጋድለው በጥማትና ችግር በዚህ ሲያልፉ 'ይሄ እርሻ ለእናንተ ሳይሆን መሃል አገር ወይ አሥመራ የሚላክ ነው። እና መብላት አትችሉም' ማለት በእውነቱ ኃጢያት ነው። ማድረግ የምትችለው አንድ ነገር ነው። ወታደሮች ሲያልፉ በሥነሥርዓት የተወሰነ ስጧቸው። ለጥበቃ የሚሆኑ ወታደሮችም ይመደብላችኋል። ነገር ግን ከጠሩ ጋር ተስማምታችሁ መቆየት አለባችሁ። እናንተንም አይጎዳችሁም ምርቱ

ከሚጨፈጨፍ በሥነ ሥርዓት ሰጧቸው። ነገር ግን ለእንደዚህ ዓይነ ጉዳይ እኛ ህግ አናወጣም።" አለና ሰውዬውን ለማበረታታት ጀርባውን አን ሁለቴ ቸብ ቸብ አደረገው።

"እሺ እንግዲህ ሰዎች ከተመደቡልን እኛም በተቻለ እንተባበራለን። እንዳሉን እርሻውም መንቀሳቀስ የቻለው ወታደሮ በመኖራቸው ነው።" አለ ኃላፊው ቅሬታውን እንደመደበቅ ብሎ።

እንዲሁ ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮችን አንስቶ ጥያቄዎችን ካቀረበ በኋ የኢላበረድን የእርሻ ተቋም ሠራተኞችን ተሰነባብተን ጉዞ ወደ ከሬ አመራን።

ከረን እንደ ደረስን መጀመሪያ የሄድነው ወደ ቀዳሚ መምሪያው ነበር። እዚያ ስንደርስ ብ/ጀ/ወርቁ ቸርነት ከአንድ ግንባር ተመልሰው አገኘናቸው ከመደዳዎቹ ቤቶች ወጥተው ሲቀበሉን

"ታዲያስ ወርቁ እንዴት ነው?" አለ ጀ/ደምሴ።

"ባጠቃላይ ጥሩ ነበር ዝግጁ ናቸው ጌታዬ" አሉ ጀ/ወርቁ።

ከመደዳዎቹ ቤት ወደ አንዱ ተከታትለው ገቡና ብዙ ሳይቆዩ ወደ በረንዳ ተመለሱ። ወዲያው ሁለት መኮንኖች ወንበር አመጡና አስቀመጧቸው።

"እዎ ይሄ ስለምታደርጉት ንቃት ላነጋግርህ ነበር የፈለግኩህ። ጠፉ ደክሞት ከግዳጅ ሲመለስ ንቃት ከግዳጁ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነው። በሁለተኛ ደረጃ ንቃት መስጠት ያለብን ዋናው ለወንበዴው ነው። እነዚያ ቢ.አር.ዲ.ኤምችን ተጠቀሙባቸው ሶስት ኪ/ሜትር ድረስ ማስማት ትችላላችሁ፤ ለእነሱ መጠቀም አለባችሁ። ወንበዴው እንደውም በየግንባሩ ያለው ከአንድ ኪ/ሜትር በማይበልጥ እርቀት ላይ ነው። እና ወታደሮች





ደክሟቸው ሲመለሱ እንደገና ሰብስቦ ንቃት እንስጣችሁ ማለት ትርጉም የለውም። ከእንግዲህ ወዲያ የምናገኘውን ጊዜ በሙሉ ለጦርነት ዝግጅት ማዋል አለብን። ማርክሲዝም ሌኒንዝም ለእነዚህ ሰዎች እዚህ በረሃ ውስጥ የምናስተምረው ምን ለማግኘት እንደሆነ አይገባኝም። ይሄን አንተ ተከታትለህ ንቃቱ በወንበዴ ፕሮፖጋንዳ ተታለው እንዲሁም ተገደው በሚማገዱት ወጣቶች ላይ ማተኮር አለበት። በየግንባሩ ይህን ማድረግ አለባችሁ።" አለ ጀ/ደምሴ የቀረበለትን የአንቦ ውሃ እየተጎነጨ። ካድሬዎች የሚያመጡት የፖለቲካ አጓጉል ፈሊጥ ከወታደራዊ ዲስፕሊን ትምህርት እየተጋጨ ብዙ ጊዜ ጀኔራል ደምሴን ያበሳጭ ነበር። ለምሳሌ የደርግ አባል የነበረው አስር አለቃ ገዛኸኝ ወርቄ ሐረር የጦሩ የፖለቲካ ኃላፊ በነበረበት ጊዜ "ቀድሞ ያየ ሠላምታ ይስጥ፤" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ ለተወሰነ ጊዜ ወታደሮች ለአለቃቸው ሠላምታ መስጠት እንደ ግዴታ ሳይሆን እንደ አማራጭ ይዘውት ነበር። አንድ ጊዜ ደግሞ አባቴ ከሐረር ወደ አሰመራ ጀነራል መርዕድን ለማነጋገር ስልክ ሲደውል የሰማሁት ትዝ ይለኛል። በወዲያኛው በኩል ስልኩን ያነሳው የጀነራል መርዕድ ረዳት ሻምበል ሙሉጌታ ነበር።

ጀነራል ደምሴ "ደምሴ ነኝ ማን ልበል?" ሲለው ሻምበሉ "እናሸንፋለን ጌታዬ!" ብሎ መለሰ።

ጀነራል ደምሴ "ምን ታሸንፋለህ፤ ወንበዴ እናትህ ላይ እየጨፈረ። መርዕድን ጸቅርብልኝ!!" ካለው በኋላ ስልኩን ሲጨርስ ወደ ተቀመጥነው ዞር ብሎ "ይገርማልኮ ሥራ ትተው በመፈክር ማሸነፍ ይቻል ይመስል ዝም

ብለው ይለፈልፋሉ። እንደምነህ ስለው "እናሸንፋለን!" ይበለኝ እንዴ? ይ ካድሬዎች ያመጡት አዲስ ፈሊጥ ነው" አለ።

ጀኔራል ደምሴና የፖለቲካው መምሪያ ኃላፊ የነበሩት ጀ/ወርቁ ግ ተስማምተው ነበር የሚሠሩት። ከጀ/ደምሴ ጋር በሐረር የጦሩ የፖለቲ ኃላፊ ሆነው ለሰባት ዓመት አብረው ስለነበሩ የቅርብ ጓደኞች ነበሩ። ጀ/ደምሴ ባለው የወታደራዊ አቋም የካድሬ ጠላት በመባል ብዙ ጊዜ ቢወነጀልም እንደ ጀ/ወርቁ ዓይነት ብቃት ያላቸው መኮንኖች ጋር ተስማምቶ ነበር የሚሰራው። ጀ/ወርቁ እንዲያውም የጀ/ደምሴ ቀኝ እጅ ነበሩ።

ቢ.አር.ዲ.ኤም የተባሉት ደግሞ ከሌሎች መደበኛ ቢ.አር.ዲ.ኤም ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ለየት የሚሉት እስከ ሶስት ሺ.ህ ሜትር ርቀት ድረስ ሊያሰሙ የሚችሉ ድምፅ ማጉያ መሣሪያዎች የተጠመዱባቸው መሆናቸውና ለቅስቀሳ ብቻ እንዲያገለግሉ የተመደቡ መሆናቸው ነው።

"አዎ ጌታዬ እኔም በዚህ በጣም ነው የምስማማው፤ የሚያመጣውን ንትርክ ብዬ ነው እንጂ እሱማ ጨርሶ ከሥርዓት ውጪ የሆነ አሰራር ነው። ጦሩ እንደሆነ አስፈላጊው ንቃት ተሰጥቶት ነው የሚመጣው፤ ብቻ የኛ ሰዎች ነገር በማዞር የሚችላቸው ስለሌለ ወደያው ይጠመዝዙታል ብዬ ነው" አሉ ጀ/ወርቁ ንግግራቸውን ሲጨርሱ በቀጭን ድምፅ እየሳቁ። አብዛኛውን ጊዜ ንግግራቸውን ሲጨርሱ በመሳቅ ነው የሚዘጉት። ወፍራም ድምፅ ተከትላ የምትወጣ ቀጭን ሳቅ አለቻቸው። ቁመታቸው አጭር የሚያስብላቸው ቢሆንም ወፈር ያለው ሰውነታቸው ግርማቸውን አላሳጣቸውም። ሲስቁ ቀይ





ፊታቸው በሳቅ ይሞላል። እና የሚያስቃቸው ነገር ባይገባውም ጀ/ወርቁ በሳቁ ቁጥር ተመልካችም አብሮ ይስቃል።

"እንደፈለጉ ሊተረጉሙት ይችላሉ። እኛ ገና ለገና እነሱ ምን ይላሉ? እያልን ሥራ መሥራት አናቆምም። በዚህ ዓይነት መቀጠል አንችልም። ጠርነቱን ወይ መጥተው ይምሩ ወይ ለኛ ይተውልን። እዚህ ሲያጨመላልቁ ከርመው አሁን ማድቤት ተቀምጠው ለሚለፈልፉ አትጨነቅ። እኛ ሥራችንን ብቻ እንሥራ።" አለ ጀ/ደምሴ ፊቱን ፊታ አድርጎ የእንቦ ውሃው ጋዝ ወደ ላይ ሲነጥር እየተመለከተ።

ከመደዳ ቤቶቹ ውስጥ ኮ/አምሳሉ ወጣና ወደ ጀ/ደምሴ ተጠግቶ "ሄሊኮፕተሮቹ መጥተዋል ጌታዬ" አለ።

"ኦ መጡ? ጥሩ ነዋ እንግዲህ፤ አምሳሉ---- በርቱ ኧ? ከሁለት ቀን በኋላ እንገናኛለን" ካለ በኋላ ወደ ጀ/ወርቁ ዞር አለና "እንግዲህ አንተ ነገ እንደተነጋገርነው ነው። በየቦታው ድረስና ሁኔታዎችን አስተካክል። ያልተሟላ ነገር በፍጹም መኖር የለበትም። እኔ ነገ አስፈልጌ አነጋግርሃለሁ።" እያለ ወደ መኪኖቹ ተራመደ። እንደተለመደው እኛም ተከትለን ወደ ከረን አየር ማረፊያ ጉዞአችንን ቀጠልን።

ወደ አየር ማረፊያው ጉዞአችን ላይ ጀ/ወርቁ "የኛ ሰዎች ነገር ማዞር የሚችላቸው ስለሌለ ወደ ሌላ እንዳይጠመዝዙት ነው።" ብለው የተናገሩትን እያሰላሰልኩ ከረንን ከጥቂት ቀናት በኋላ እስክንገናኝ ድረስ ደህና ቀዪኝ በሚል ስሜት አቃኘት ነበር። ጀ/ወርቁ የተናገሩትን ባሰብኩት ቁጥር ሊያመጣ የሚችለው ጠንቅ ወደ ጭንቅላቴ ተመላልሶ መምጣት ጀመረ። በተለይ በኮሎኔል በለጠ እና በኮሎኔል አስማማው ላይ ከጥቂት

ዓመታት በፊት የደረሰው---ጀ/ወርቁ ካነሱት ጋር ምንም ልዩነት የለውም ኮ/በለጠ ተፈራ ስመ ጥሩ መኮንን ከመሆናቸውም በላይ ወታደራዊ ጥበብ ከተካኑ የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች ውስጥ አንዱ ነበሩ። ኮሎኔል በለ በአንድ ጦርነት ወቅት---ጦራቸውን "እስቲ አሁን የት እንደምትገባ አያለሁ መጣልህ እንግዲህ። ትዋጋ እንደሆን ተዋጋ። እስኪያ ታገኘዋለህ" ብለ በመናገራቸው በእወደድ ባይና ካለኛ ላገር ተቆርቋሪ የለም ባዮች እን አስር አለቃ ግርማ አየለ (በኋላ ብ/ጄኔራል የተባለ) ባሉ ካድሬዎች ተከሰ በግፍ ተገድለዋል። የክሱ መነሻ "የወገንን ጦር ዝቅ ዝቅ በማድረ የጠላትን ጦር ከፍ ከፍ አድርጓል" የሚል ሕጻን ልጅ የሚያቀርበው አይነ ክስ ነበር። ኮ/አሰማማው ይመርም እንዲሁ በካድሬ ውንጀላ በግፍ ከተገደለ በኋላ እርምጃው የተወሰደው በስህተት እንደሆነ መንግስት አስታውቋል። ይ ግፍ በሻምበል ፍቅረሥላሴና ወግደረስ እና በአስር ዓለቃ ግርማ አየለ የተቀነባበረና እነዚሁ ሰዎች ቀመው ያስፈጸሙት አረመኔያዊ ድርጊት ነበር። እና ከዚህ አንጻር የጀ/ወርቁን ነጥብ በቀላሉ የማልፈው አልነበረም።

ከረን አየር ማረፊያ ስንደርስ አንድ ሄሊኮፐተር ቆማ ትጠብቀን ስለነበር ብዙ ጊዜ ሳናጠፋ ተሳፍረን ቦታ ቦታችንን ያዝን። አብረውን ከመጡት ውስጥ አብዛኛዎቹ ከረን ቀርተው ስለነበር መንገደኞች ጥቂት ነበርን። ከሄሊኮፐተሯ አደንቋሪ ጩኸት ጋር የቀኑ ድካም ተደምሮ ፋዞ ሆኜ ነበር አስመራ የደረስኩት።

አስመራ ስንደርስ ለዓይን ያዝ ማድረግ ጀምሮ ነበር። ደብዛዛዋ ጨረቃ እንደ ዓይን አፋር ሴት ወይዘሮ ከተራራው ጀርባ በግማሽ ወጥታ ትታያለች። የአስመራ አየር ማረፊያም የቀኑን ትርምስ በፀጥታ ለውጦ





የድካም እንቅልፍ ላይ እንዳለ ሁሉ ትንሿን ድምፅ እያጎላ እትረብሹኝ በሚል መልክ ያስተጋባል። ወደ መኪኖቹ ስናመራ የአየር ኃይሉ እንቅስቃሴ ሙሪ የነበሩት ኮሌኔል መንገሻ ሁንዴ ስለ አንዳንድ ሁኔታዎች ከጀ/ደምሴ ጋር ይወያዩ ስለነበር ቆመን ስንጠብቅ አንድ የራሺያ አስተርጓሚ መልእክት ለማቅረብ ቀረበ። ንግግራቸውን ሲጨርሱ ጀነራል ደምሴ ወደመኪናው እያመራ አስተርጓሚውን "እ ምን ነበር?" አለው።

"ጀኔራል--- ዛሬ ማታ እኛ ግቢ ውስጥ ሳውና.. እና ግብዣ እንዲመጡ በማክበር ተርተዎታል" አለ የራሺያው አስተርጓሚ ወጣት እየተኮላተፈ። ጀኔራሉ የጦሩ አዛዥ አማካሪ ሲሆን አስመራ የሚሠራ ነው። የራሺያ አስተርጓሚዎች አማርኛ አቀላጥፈው የሚናገሩና እንዲያውም አንዳንዶቹ ቅኔ ለመቀኘትም የሚሞክሩ ናቸው። የተባለው ሁሉ እንዳያመልጣቸው የተዘጋጁ እነዚህ አስተርጓሚዎች ኢትዮጵያዊ የአነጋገር ዘይቤን ለመያዝ ሁሉ ይጥራሉ። ጀ/ደምሴ መልስ ሳይሰጥ መኪና ላይ ተሳፈረና "አመሰግናለሁ ግን ብዙ ሥራ አለብኝ እና አልችልም" አለ በመስታውቱ ወደ ውጭ ተመልክቶ።

"መልክቱን ለጸሃፊዎ ነግሬያለሁ። ትናንት እና አዲስ አበባ የመጡ እንግዶች ስላሉ ይጠብቆታል።" አለ አሁንም በኢትዮጵያዊ ባሕል የሚግደረደርን ሰው እንደሚገፋፋ ዓይነት።

"እዎ ሰምቻለሁ አሁን አፋጣኝ ሥራዎች አሉኝ እና መምጣት አልችልም። ለግብዣው አመሰግናለሁ።" ካለ በኋላ ወደ ሾፌሩ ዞር ብሎ "እንሂድ!"

አለው። አስተርጓሚው ተጨማሪ ግፊት ለማድረግ ንግግር ሲጀምር ሲ መኪናዋ ተነስታ ስለሄደች በቆመበት ቀረ።

"እኛ ውጥረት ላይ ነን እነሱ 'ሳውና ፤ ሳውና' ይላሉ እንደነዚህ ሰዎ እንፋሎት የሚወድ ሰው በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም።" አለና በራ እነጋገር እየሳቀ "በሄዱበት እኮ ነው! በሄዱበት ሁሉ የመጀመሪያ ሥራቸ ሳውና ማዘጋጀት ነው" አለ ጀ/ደምሴ አሁንም ወደ ፊት ብቻ እየተመለከተ።

እኔን ቤት ጥለውኝ እነሱ ወደ ቢሮ ሲሄዱ ቀኑ ጨልሞ ጨረቃም ፍንትው ብላ ወጥታ ነበር። አባቴ ከሥራ እስኪመለስ ድረስ ቢያንስ እምስቴ በስልክ ሁለት ጊዜ ደግሞ በአካል መጥተው የሳውናውን ግብዣ መልዕክት ሲሰጡኝ አመሹ።

ጀ/ደምሴ ካድሬን ብቻ ሳይሆን ራሺያኖችንም እንዲሁ "ይጠላሉ" እየተባለ ይታማል። ባንድ ወቅት፤ ሐረር ካለው የጀነራል ደምሴ ቢሮ አንድ የራሺያዊ ጀነራል አለቀጠሮ ቢሮውን ከፍቶ በመግባቱ በወታደር ፖሊስ እንዲወጣና ለወደፊቱም ቀጠሮ ሳይዝ ቢሮው እንዳይገባ በማድረጉ በከፍተኛ ደረጃ አስወቅሶታል። በሌላ ጊዜ ደግሞ፤ አንድ ሲቪል የነዳጅ ማውጫ ፕሮጀክት ሠራተኛ የሆነ ራሺያዊ፤ ያለክፍለ ጦሩ አዛዥ ፈቃድ፣ ወታደሮችን ይዞ ከሸላቦ ርቆ ወደሚገኝ አንድ ቦታ መሄዱን ሲሰማ ሰውየውን አስጠርቶ ለምን የክ.ጦሩን አዛዥን ፈቃድ እንዳልጠየቀ





ይጠይቀዋል። ራሺያዊው በመኩራራት "ወታደሮቹን ስጠራ ቶሞ ያዳምጥ ነበር" የሚል መልስ ይሰጣል።
"በየመንገዱ ነው እንዴ የምትናግረው። ለምን ቢሮው ሄደህ በስነ ስርዓት አላስፈቀድከውም?" ብሎ ደግሞ ይጠይቀዋል። በዚህ ጊዜ ራሺያዊው በትዕቢት እየተወጣጠረ "የአንተ ኮሌኔል የመንገድ ሰው ስለሆነ እዚያው መንገድ ነው ላይ የማነጋግረው" በማለት ይመልሳል። በዚህ ድፍረት ጀ/ደምሴ በንዴት ይገነፍላል።
"ይሄ ጥጋበኛ የኢትዮጵያን ኮሌኔል ነው የመንገድ ሰው የሚለው? ባገራችን ይህን ያህል ስንሰደብ የውርደት ውርደት ነው።" ይልና ወደ እጃቢው ዞር ብሎ "ቀጥታ ውሰድና ትጥቁን አስፈትተህ እስር ቤት አስገባው" ይለዋል። ሰውየውም ወደ ድሬዳዋ ታስሮ ከተወሰደ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተላከ። ይህ እርምጃ ወደ ኋላ ብዙ መዘዝ አስከትሏል። ከፍተኛ ካድሬ የተባሉት ሁሉ ድርጊቱ "ከፊውዳላዊ አስተሳሰብ የመነጨ ነው" ብለው ባቀረቡት ክስ መሠረት ጀ/ደምሴም ስለሁኔታው እንዲያስረዳ አ.አበባ ድረስ ተጠርቶ ሄዷል። ነገር ግን ሰውየው ወደ ሥራው በምንም ዓይነት መመለስ እንደሌለበትና አገራችንንም ማዋረዱን ከእሱ ጋርም ከእንግዲህ ሊሠራ እንደማይችል ጸንቶ ስለተከራከረ በመጨረሻ ራሺያዊው ወደ አገሩ እንዲባረር ተደረገ።

ሰውየው ይቅርታ ጠይቆ አማላጆችን እስከመላክ የደረሰበትም ጊዜ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ክብራቸውን የማያስነኩ ኩሩ ህዝቦች መሆናቸውን ለመረዳት ረዘም ያለ ጊዜ ስለወሰደበት ከሚወደው

የኮንትሮባንድና ምዕራባዊያን ሽቀጥ መለየት ግድ ሆኖበታል። እናም ሰ አገሩ እንዲመለስ ተደረገ።

ጀኔራል ደምሴ ለነጮች የተለየ ክበሬታም ሆነ ንቀት የለውም ስለተለያዩ ግለሰቦች ሲያነሳ በግለሰብ ደረጃ በእውቀታቸውና በብቃታቸ መሠረት ነበር የሚመዝናቸው። በአጠቃላይ ነጮች ለኛ ኢትዮጵያውያ የነበራቸውን አመለካከት ግን በግልጽ ነበር የሚናገረው። ይኸም አመለካከ በተለያዩ ጊዜያት በደረሰበት ሁኔታና አጋጣሚዎች ላይ የተመሠረተ ነበር ለምሳሌ በ1951 ዓም ጆርጂያ በተለባለችው የአሜሪካ ግዛት ውስግ በሚገኘውና ፎርት ቤኒንግ በተብሎ በሚታወቀው የእግረኛ ጦር መ መኮንኖች ማሰልጠኛ ተቋም በትምህርት ላይ እያለ፣ የደረሰበት ለዚህ አመለካከቱ ምክንያት ከሆኑት አንዱ ነው። በትምህርት ላይ እያለ አብሮት ለትምህርት ከሄደው ከመ/አ አሰራት ብሩ (በኋላ ሜጀር ጀነራል) ጋር ሆነው በአውቶብስ ከሌሎች የአሜሪካ መኮንኖች ጋር ከአንድ ከተማ ወደሌላ ከተማ እየተጓዙ ነበር። መንገዱ ረዘም ያለና ከጧቱ እስከ ከሰዓት በኋላ የሚፈጅ ስለነበር ፣አውቶብሱ ለምሳ አንድ ሆቴል ፊት ለፊት አቁሞ ተሳፋሪው ለምሳ መውረድ ጀመረ። በወቅቱ ወጣት መ/አ መኮንንን የነበሩት ደምሴ ቡልቶ እና አሰራት ብሩ ከአውቶብሰ ወርደው ሌሎችን መኮንኖች ተከትለው ወደሆቴሉ እንደገቡ፣ ተስተናጋጁ በሙሉ መብላቱን ትቶ ወደነሱ ዞሮ ሲያፈጥባቸው ግራ ገባቸው። የለበሱት የመኮንኖች የደንብ ልብስ ከአሜሪካዊያኑ መኮንኖች የተለየ አልነበረም። ወዲያው አንዱ አስተናጋጅ በፍጥነት መጥቶ ሆቴሉ ጥቁር ሰው እንደማያስተናግድና ወደ ውስጥ





መግባታቸው ራሱ የግዛቱን ህግ የጣሰ መሆኑን ገልጾ፣ በአስቸኳይ ቤቱን ለቀው እንዲወጡ አዘዛቸው። አብሯቸው የነበሩት መኮንኖች ምግባቸውን ለማዘዝ ሲቀመጡ እነሱ አንገታቸውን አቀርቅረው ወደ ውጭ ወጡ። አብረዋቸው ከሚማሩትና ውስጥ ከነበሩት ነጮች አንዳቸውም እንኳ ቀመው ሊከራከሩላቸው ቀርቶ ሊያጽናኗቸው እንኳ አልሞከሩም። በደረሰባቸው የዘረኝነት አድልዎ ተገርመውና ግራ ተጋብተው ወደ አውቶብሱ ሲገቡ፣ ለሚታቸው በሀዘን ተሞላ። በአውቶብሰ ውስጥ የነበሩት ጥቁር መኮንኖች የመቀመጫ ቦታቸውን ሳይለቁ ቀደም ብለው የሰንቁትን ምግብ ከየምሳ እቃቸው እያወጡ በመብላት ላይ ነበሩ። እነርሱም አስከፊው የዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተው ሥርዓት የመደበላቸውን ቦታ ቀደም ብለው ያውቁ ነበር። ከዚያም በኋላ አውቶብሱ ጉዞውን ቀጥሎ እስከ መድረሻው ድረስ ይዟቸው ቢጓዝም ለምሳ ሁለተኛ አልቆመም። ምሳቸውን ሳይበሉ የታሰበበት ቦታ ደረሱ።

ስለዚህ አንድ የራሽያ መኮንን በየኢትዮጵያ መሬት ላይ ቆሞ የኢትዮጵያን መኮንን አንቋሾ ሲናገር ጀነራል ደምሴ እንደተራ ነገር ቀጥሮ ሊያልፈው አልቻለም።

ከከረን ከተመለስን ሁለተኛ ቀናችን ነው። ዝግጅች ሲደረግለትና ሲጠበቅ የነበረው ጦርነት በነገው እለት እንደሚደረግ ከምሳ በኋላ አባቴ ለጉዞ እንድዘጋጅ ሲነግረኝ ጠረጠርኩ። ለጦርነቱ ምን ያህል መቅረብ እንደምንችል ግን እርግጠኛ አልነበርኩም። ብዙም መቅረብ ባልፈልግም ምንም ማየት እስኪሳነኝ ድረስ ደግሞ መራቅ አልፈልግም። አንድ ምሽግ ውስጥ ተዘግቶ መቆየት ሊኖር ይችላል። ሌሊቱን ሙሉ ይህንኑና ሊሆን

የሚችለውን ሁሉ ሳወጣና ሳወርድ አገባደድኩት። አባቴ የዚህ ዓይነቱ እ
ቦታ ለምን ይዞኝ ለመሄድ እንደተስማማም ግራ ገባኝ። ከዚህ በ
በየምረቃ ዝግጅትና ትርኢቶች እየያዘን በመሄድ ስለ ወታደር ህይወትI
አገራችንም ሁኔታ አስረድቶናል። ወደ እውነተኛ ፍልሚያ ሜዳ
ማናችንንም ይዞን ሄዶ አያውቅም። በተለይ የዚህ ጦርነት ክብደት ኩ
ወደ ቀን እየገባኝ ሲመጣ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ሁሉ በአንጎሌ
ጥልቅ እያለ ይጎበኘኝ ጀመር። ከመድፍና ሞርታር ጥይት አንስቶ እስከ
ተሽከርካሪ ፈንጂ፤ ከታንክ ጥይት እስከ ቢ.ኤም ሃያ አንድ ሮኬት አልፎ
ጦሩ ከሸሸ ብዙ ነገሮች ያስጉናል። ብዙ ጀነራሎችም በነዚሁ ምክንያቶ
ለአገራቸው ሲዋጉ አልፈዋል። ነገር ግን አባቴ የደረሰበት ቦታ ከመድረ
የገባበት እሳት ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ ቢቻ ሳልሆን ቻኩዬም ነበር
ከዚያ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ፤ ለትልቅ ዓላማ የተዘጋጀሁ ዓይነት ስሜ
ተሰማኝ። ለማየት የምሄደው ይህን ያህል ከኮራሁ ተዋግቶ ድል የመታ
ምን ይሰማው? 'በል አሁን አርፈህ ተኛ ነገ ጠዋት ጉዞ አለብህ!' ለራ
ትዕዛዝ ስጠሁኝና አንቅልፍ ፍለጋ አይኖቼን ጨፈንኩ።





# -8-

## አጋር

ሄሊኮፕተሩዋ ከረን ስታርፍ አብዛኛው የከረን ህዝብ ገና እንቅልፍ ላይ ነበር። የጠዋቱ ቀዝቃዛ አየር ዓለምንም ከልካይ በአየር ማረፊያው ሜዳ ላይ በማን አለብኝነት ይነፍሳል። ከሄሊኮፕተሩዋ በየተራ ጃኬታችንን እየቀለፍን ወጣን። እውጭ የተቀበለን አንድ በሐረር አካዳሚ ጀ/ደምሴ ያስተማረው ኮለኔል ነበር። የሞቀ ሰላምታ ሰጥቶን ወደ መኪኖቹ መራን። መትረየስ የተጠመዱባቸው ሁለት ግልፅ ዋዞች ከፊትና ከሁዋላ አጅበውን ከረንን ከበው ከሚታዩት ተራራዎች በስተሰሜን ካለው አንድ ተራራ እትጣጫ ከነፍን። ተራራው ስር ስንደርስ በተራራው ዙሪያ የተሰራ ጥርጊያ መንገድ ላይ ወጣንና ዋዞች አቀበቱን በከባድ ማርሽ ተያያዙት። በተራራው ዙሪያ በጥበቃ ላይ የተሰማሩ ወታደሮች መትረየሶቻቸውን አንግተው ቆመዋል። ተራራው ጫፍ ላይ ስንደርስ መኪኖቹ ቆሙና ወረድን። የሬድዮ መልዕክት ማስተላለፊያና መቀበያ ሽቦዎች በተራራው አናት ላይ ከሁሉም አቅጣጫ ተወጥረው ይታያሉ። አብረውን የመጡ ሽምግል ያሉ የራሺያ ጀነራልና አስተርጓሚያቸው ወደ ኋላ ቀረት ሲሉ እኔ ሌሎቹን በግዴለሽነት ተከትዬ ባንድ ቀጭን ቀዳዳ የተራራው ምሽግ ውስጥ ገባሁ ምሽጉ

ከላይኛው መሬት ቢያንስ አንድ ሜትር ወደ ውስጥ የተቆፈረና ውስጡ ብዙ ክፍሎች ያሉት ነው። እንዲሁ ሻ/ቤታሁንን እየተከተልኩ ብዙ መኝታ ቤቶችንና የሬድዮ መገናኛ ክፍሎችን አልፌ አንድ ጠረጴዛና ወንበር ከብዙ ስልኮች ጋር ከተደረደሩበት ክፍል ስደርስ ሁሉም እዚያው ስለገቡ እኔ ውጪ ቀረሁ።

ውስጥ ውስጡን የተሰራው መተላለፊያ ከአንድ ሰው በላይ ስለማይዝ ችግር ላለመፍጠር ወደ ውጪ መውጣት ፈለግኩና ወደ ኋላ መመለስ ጀመርኩ ። እግረመንገዴን ክፍሎቹን እያጤንኩ ነበር። አሸዋ የተሞሉ ጆንያዎች በብዛት ተደርድረው እንደ ግርግዳ እንደ ጣሪያም ተሰርተዋል። የዚህ ዓይነት ምሽግ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። ምሽጉ የመድፍ ጥይት እንኳን ብዙ አደጋ ሊያደርስበት የሚችል አይመስለኝም። ምሽጉ ውስጥ ስዘዋወር የመጣሁበት መንገድ አቅጣጫ ስለጠፋኝ አንድ የሬድዮ ማዳመጫ ጆሮው ላይ ሰክቶ የተቀመጠ አስር አለቃ እየሁኝ መውጫውን ስጠይቀው በግራ መጋባት "አንተ ደግሞ ከየት የመጣህ ነህ?" በሚል ዓይነት ስሜት "በዚህ ታጠፍና ከዚያ ወደ ግራ ዙር አለኝ" የነገረኝ አቅጣጫ ያስወጣኝ በመጣሁበት ሳይሆን በጀርባው በኩል ነበር። ከፊት ለፊት አንድ መገናኛ ሬድዮ ብቻ የተጠመደበት ከባድ መኪና ውስጥ ሁለት መኮንኖች ተቀምጠው በሚስጥር መልእክት ያስተላልፋሉ። እነሱን አልፌ ዞርኩና መጀመሪያ ወደገባሁበት ቀዳዳ አመራሁ። ከገባንበት ቀዳዳ በስተቀኝ በቅጠል መሰል ጨርቅ ድንኳን ውስጥ ጂ/ደምሴ እና የመጡት ራሺያኖች ተቀምጠዋል። እዚያው አካባቢ ቆም እንዳልኩ ብ/ጂ/ታደሰ ከቀዳዳው ብቅ





ብለው ወጡ። ሲያዩኝ በመገረም "አንተ ደግሞ እዚህ ምን ትሰራለህ?" አሉኝ።

እኔም "እንዲሁ ለማየት ነው።" ብዬ ሰላምታ አቀረብኩ። ሐረር አካዳሚ ከለውጡ በፊት ከአባቴ ጋር ያስተምሩ ስለነበር አንድ ካምፕ ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ስንጫወት ነው ያደግነው። ጀ/ታደሰ የጦሩ የዘመቻ መምሪያ ሐላፊ ነበሩ። በኤርትራ ከአስር ዓመት በላይ ሌት ተቀን ያለ እረፍት ሲሰሩ ከኖሩ መሪዎች ውስጥ አንዱ ስለነበሩ ሰውነታቸው አልቆ አጥንትም ደፍሯቸው ነበር። በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም በጣም ያጨሱ ነበር። ስንመጣም አባቴ ከአስመራ ሁለት ስቴካ ሲጋራ ስንቀላቸው ነው የመጣው። ከጀ/ደምሴም ጋር አንዱ ጭቅጭቃቸው የዚሁ ሲጋራ በብዛት ማጨሳቸው ነበር። ይዞ መምጣቱን ግን አላቆመም። ለስራቸው ያላቸው አክብሮትና ትጋት ብዙ ጊዜ በብዙዎች ሲነገር የምሰማው ከመሆኑም ሌላ አስመራ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ ዋና ቢሮአቸው አስመራ ሆኖ ሳለ እዚህ ጉድጓድ ውስጥ ከቤተሰባቸው ተለይተው ነበር የሚኖሩት። ጀ/ደምሴ "ታደሰ ምርጥ መኮንን ነው" ብሎ ያደንቃቸው ነበር።

ድንኳኑ ውስጥ ተቀምጠው የሚያወሩትን መስማት እንድችል ብዙም ሳልርቅ ፈንጠር ብዬ ተቀመጥኩ።

"እስቲ የሬዲዮ ጠላፊዎች መኮንኑን አስጠራው እስከ አሁን ያገኙት ነገር መኖር አለበት" አለ ጀ/ደምሴ ጀ/ታደሰን እየተመለከተ።

ብዙም ሳይቆይ ቅድም የሬዲዮ መገናኛ የጫነ ከባድ መኪና ላይ ካየኋቸው ውስጥ አንዱ መ/አለቃ መጣና ሰላምታ ገጥሞ በተጠንቀቅ ቆመ።

"ማን ትባላለህ?" አለው ጀ/ደምሴ እየተመለከተው።

“መ/አ ---- “

ከወንበደው በኩል የታየ ምን ለውጥ አለ? ያገኛችሁትን ሁሉ ዘርዝርልኝ አለው ጀ/ደምሴ።

“እዎ በግዝግዛ ግንባር ያሉት ያልጠበቁት ነገር እንደገጠማቸውና ከ---- ግንባር ተጨማሪ ጦር ሲጠይቁ የተሰጣቸው መልስ በተለያዩ ቦታ ላይ ድንገተኛ ጦርነቶች የተከፈቱ ስለሆነና የትኛውን ላይ እንደምናተኩር እስኪረዱ ድረስ ጦር ከየትም እንደማያንቀሳቅሱ ነው። ባጠቃላይ ካገኘናቸው መረጃዎች በወንበዴው በኩል ከፍተኛ መደናገር የተፈጠረ መሆኑንና ጦር ከኋላ በኩል አንስተው ለማምጣት አለመቻላቸውን ነው።” አለና የያዘውን ወረቀት ወደ ጎን አድርጎ በተጠንቀቅ ተመልሶ ቆመ።

“ሌላስ ምን ያገኛችሁት አለ?”

“በአጠቃላይ ይኸው ነው ጌታዬ”

“በአጠቃላይ አትበለኝ። እኔ አጠቃልልኝ አላልኩህም። እያንዳንዷን ነጥብ ነው የምፈልገው። አሁን ተመለስና ነጥብ ከያዛችሁበት ወረቀት እያንዳንዱን ገልብጠህ አምጣልኝ። ይጠቅማል አይጠቅምም ሳትል ሁሉንም ነው የምፈልገው። ዛሬ በቂ ሰው ከሌለህ ይጨመርልሃል። እያንዳንዱን የወንበዴ ግንኙነት እየመዘገባችሁ ወዲያው ለመገናኛው አስተላልፉልን። ይኸው ነው ለጊዜው” ሲል መ/አለቃውም ሰላምታ ሰጥቶ በቀዳዳው ገብቶ ተሰወረ።

“ጥሩ ነው። እንዲያውም የባሰውን ግራ እንዲጋቡ በግዝግዛ በኩል የመድፍ ድብደባ እስከ ሰባት ሰዓት እንዳይቆም መልእክት አስተላልፍ። በሌሎችም





ግንባሮች እንዲሁ ትዕዛዝ እስኪደርሳቸው ተኩስ እንዳያቆሙ።” አሉ ወደ ጀ/.ታደሰ እየተመለከቱ።

“እሺ, ጌታዬ ቀደም ብየም ነግሬያቸዋለሁ በድጋሚ እንዲነገሯቸው አደርጋለሁ” አሉ ጀ/ታደሰ ያቀጣጠሉትን ሲጋራ በኃይል ስበው ጭሱን ከንግግራቸው ጋር እያወጡት።

“እሺ, እንግዲህ ታደሰ እኛ ወደዛው እንገስግስ። እንግዲህ አንተ እዚህ የተነጋገርነውን አስፈፅም።” አለና ጀ/ደምሴ ተነሳ ። ከጀ/ታደሰ ጋር በወንድማዊ ስሜት ከተጨባበጡ በኋላ ወደ መኪኖቹ አመራ።

“ጌታሁን፣ አጃቢዎቹ ተዘጋጅተዋል?” አለ ጀ/ደምሴ መኪናው ላይ እየተሳፈረ።

“አዎ ጌታዬ፣ ታች እየጠበቁን ነው።” አለና እሱም ተሳፈረ።

ወደ ጦር ሜዳ ጉዞ ጀመርን። በዛሬው እለት የብዙ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ለአገራቸው ይሰዋሉ። ብዙዎች ደግሞ ይቆስላሉ። ለብዙዎች የሞትና ሽረት ቀን፤ ለኔ ደግሞ በሕይወት የማልረሳውን ተጋድሎ የማይበት ወይም----? የሚሆነው ምን ይታወቃል? ዝም ብዬ መጓዜን ቀጠልኩ። ይጠብቁን የነበሩት አጃቢዎች ተራራውን ወርደን ስንጨርስ አንድ ጣራው ብቻ ጨርቅ የለበሰ አይፋ ከባድ መኪና ላይ እየዘለሉ ወጡና መኪናው ከኋላ መትረየስ ተጠምዶበት ከሚከተለን ዋዝ ኋላ ሆኖ ተከተለን። የከረንን ከተማ አልፈን ወደ ሰሜን ገሰገስን። የምንሄደው ወደ አጋሮ ተራራ ነበር። የሞት ሽረት ውጊያ ወደሚደረግበት ሰሜናዊ ተራራ።

ከመንገዱ ዳርና ዳር ያሉት አጫጭር አረንጓዴ ተክሎች የለበሱትን አ፬ እንደሚያረግፉ ሁሉ እርስ በርሳቸው እየተጋጩ ይንዠዋዠዋሉ። ከተክሎቹ ጋር ነፍሴም አብራ በሙዚቃ ስትደንስ ዐይኔ ከአንድ አስደንጋጭ ነገር ፣ አረፈ። መንገዱ ላይ እየተሳበ ለመውጣት ሲጥር እንደተገደለ ዓይነት አን ጎፈሬያም ጎልማሳ እጁን ወደ ፊት ዘርግቶ ወድቋል። ድንገት ሳላስበው ጮ ብዬ "የሞተ ሰው" ብዬ ተናገርኩ።

"ለምንድነው እነዚህ ሰዎች ሬሳ የማያነሱት? ይሄ ሰውዬ ባለፈው ከረን ለመያዝ ሲያጠቁ ተሰቦ እዚህ ድረስ ደርሶ በላውንቸር ታንክ ሊያቃጥ ሲል ነው የተገደለው። እስከ አሁን እንዴት ሳይቀበር ይቀራል?" አ ጀ/ደምሴ በመገደሉ ሳይሆን ባለመቀበሩ ተናደ። ከማንም መልስ ሳይጠብ ሰውየው የወደቀበትን ቦታ ካለፍን በኋላ ትንሽ ተጓዝንና ዋናውን መንገደ ለቀን ከወደ በስተግራ በኩል ከአንድ ጥርጊያ መንገድ ላይ ወጣን።

መኪኖቹ አቧራውን እያቦነኑ ፍጥነት ሳይቀንሱ ከመቀመጫችን ላይ እያነጠሩን ይበራሉ። ራቅ ካለ ስፍራ የመድፍ ተኩስ ድንገት ጆሮዬ ሲገባ ልቤ ከተመልካችነት ወደ ተሳታፊነት በቅፅበት ተለውጦ ያለሁበትን ቦታ ጠባይ በየሰኮንዱ ያስታውሰኝ ጀመረ። የመድፍ ጩኸት እየቀረበ መጣ። የማያቋርጥ የመድፍ ተኩስ ነበር። የአንበሳው 3ኛ ክ.ጦር መምሪያ የሚል ጽሑፍ ከተተከለበት አንድ ቅጥር ግቢ ስንደርስ ከመድፉ ድምፅ ሌላ የሮኬት ድብደባ ድምፅ ይሰማ ጀመር።





ተራሮችን እየቧጠጥን እንወጣና ደሞ እንወርዳቸዋለን። አንዱን ተራራ ስንጨርስ ሌላው ጥርሱን አግጦ ይጠብቀናል። እንዲህ እያልን ተጉዘን አንዱን ተራራ ስንጨርስ አንድ አነስተኛ ወንዝ ዳር ደረስን። ዙሪያዋን በዛፎችና ሳሮች የተከበበች በዛፎች ጥላ ሥር የሕይወትን ጣዕመ ዜማ የምታሰማ የምትመስል! ሙሉ የሕይወት እንቅስቃሴ የሚታይባት ለምለም ቦታ። ምን ያደርጋል ተፈጥሮን ለማድነቅ ጊዜ የለኝም። ለምለምነቷን ያጤንኩት ምናልባት እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም። የወታደሮች ትርምስ ይታይባታል። ወንዙን ለማቋረጥ አልቻልንም ብለው ወታደሮች ሁለት ዋዝ መኪኖችን ከበው ቆመዋል።
"ምንድን ነው ችግራችሁ?" አለ ጀ/ደምሴ ወታደሮቹን በመስኮት እየተመለከተ።
"ወንዙን መሻገር ስላልቻልን ከባድ መኪና እየጠበቅን ነው ጌታዬ።" አለ አንድ መቶ አለቃ።
"በሉ ተከተሉን ያሳልፉችኋል። ይሄ እስከዚህ የሚያሰጋ አይደለም።" አለና ወደ ነጂው ዞር ብሎ
"ድንጋዩን እየተከተልክ ሂድ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ አልፌበታለሁ" አለው።

ወንዙን ስንሻገር በዚያች ለምለም ቦታ ተደንቄ ዞር ዞር እያልኩ ስመለከት ዓይኔ አሁንም ሁለት ግማሽ ሰውነታቸው በውሃ የታጠበ ወጣቶች ፊት ጋር ተጋፈጠ። ዘገነነኝ። ከሳሩ መሃከል ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ጎን ለጎን ተኝተዋል። ቦታዋ የውበት ደሴት መሆኗ ቀርቶ ጣእረ ሞት የሚዘዋወርባት ጽልመታዊ የሞት ጎራ መሰለችኝ። ከአካባቢው ቶሎ መራቅ ፈለግኩ።

ወንዙን ቶሎ ተሻገርንና ሌላ ተራራ መውጣት ጀመርን። አሁን የመድ ተኩስ ድምፅ ጆሮን በሚያደነቁር ጩኸት ከተራራው ጫፍ ላይ ሲነጉ ይሰማል። ድም-ድም- ድም-----መድፍ! ሽሽሽ---ሰሰሰ--ፍፍ--ው! ሽሽሽ-- ሰሰሰ--ፍፍ--ው ቢ.ኤም.ሃያ አንድ ሮኬት። ያለማቋረጥ የሞት መልክታቸው ለማድረስ በዓየሩ ላይ ይጣደፋሉ። ተራራው ጫፍ ላይ ስንወጣ አራት ቢ.ኤም ሃያ አንድ ሮኬት የተሸከሙ ዚል ከባድ መኪናዎች ሮኬታቸውን ተራ በተራ እያወናጨፉ ይሰዳሉ። ሮኬቱ ሲተኮስ ወደ ኋላ ከሁለት ሜትር በላይ የሆነ እሳት ይተፋና ተንደርድሮ የተነሳ ዓይነት ተፈትልኮ በአፈሙዙ ይወጣል። ወታደሮች የጥይት ሳጥኖችን እየከፈቱ የሮኬት ጥይት በባዶ የሮኬት አፈሙዝ ላይ ይሞላሉ። እነሱን አለፍንና በተራራው ጠርዝ ላይ በተሰራ መንገድ ላይ ወጣን።

ብዙም ሳንሄድ መድፈኞቹ ጋር ደረስን። ወደ ስድስት የሚሆኑ መድፎች ራቅ ራቅ ብለው አፈሙዛቸውን ማዶ ወደሚታየው ተራራ ቀስረው ተራ በተራ እሳት ይተፋሉ። የመድፉ ድምፅ አይጣል ነው። የጆሮ ታምቡር ይበጥሳል። እነዚህኞቹን መድፎች እንዳለፍን ሁለተኛውን የመድፍ ረድፍ አገኘን። እነዚህኞቹም ከበፊቶቹ ባልተለየ ሁኔታ ተኩሱን ተያይዘውታል። ትንሽ በተጓዝን ቁጥር እንዲሁ ሌላ መድፈኛ ቡድን እያገኘን ነበር የምናልፈው። "ዛሬ እንኳን ሰው ተክልና ትናንሽ ነፍሳት እንኳን የሚተርፍ አይመስለኝም" ብዬ አሰብኩ።





ጠርነቱን ምን ያህል እንደምንቀርበው ልጠይቅ ሲቃጣኝ ከአንድ ተራራ ጫፍ ላይ ስንደርስ ከፊት ያለው መትረየስ ወደ ጎን ብሎ ሲቆም የኛ ዋዝ ወደፊት አለፈና ቆመ።

ከመኪናው ስንወርድ ጀ/ቁምላቸው የጦር ሜዳ መነጽራቸውን አንግተው ወደኛ መጡ። ወደፊት ይዘውን ሄዱ። አካባቢው በመድፍ ሮኬት ጥይት ድምፅ ድብልቅልቁ ወጥቷል። ጥይቱ ሲተኮስ ጆሮን በሚያደነቁር ድምፅ ይፈተለክና ሄዶ ሲመታ ደግሞ የተላከበት እንደደረሰ ሌላ ድምፅ ያሰማል።

ደ...አ...አ ሲተኮስ! ግ...አ...አ...ም...ም ሲመታ?

ተራራው ጫፍ ላይ የተቆፈረ ጎድጓዳ ቦታ ውስጥ እንደ መተኛትም እንደ መቀመጥም ካሉት ውስጥ ኮ/አምሳሉን ስላየሁ ሌሎቹን ትቼ እዚያ በፍጥነት ገባሁና ተቀመጥኩ።

"ታዲያስ? ደሞ እዚህ ምን ልታደርግ መጣህ?"

"ያው ዝም ብዬ ለማየት ነው። የናንተን ኑሮ" አልኩና፣ "አሁን እነሱ ያሉት እዚያ መድፍ የሚመታበት ቦታ ላይ ነው ማለት ነው?" ብዬ ጠየቅኩ፣ ከፊት ለፊት ያለውን ተራራ በእጇ እያሳየሁ።

"አዎ እንካ በዚህ ተመልከት" ብሎ የጦር ሜዳ መነፅሩን ሰጠኝ። መነፅሩ ከፊት ያለውን ተራራ ቁልጭ አድርጎ ባያሳይም እንቅስቃሴዎችን ለማየት ይረዳል፡ ከተራራው ሥር የተሰለፉ ወታደሮች አንድ በአንድ ወደፊት እንዲሄዱ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው ጉዞ ጀመሩ።

“እነዚህ ናቸው ማለት ነው የሚዋጉት?”
“አዎ እነዚህም ይዋጋሉ 10ኛ ክፍለ ጦሮች ናቸው። ተራራው ዶ የደረሱም አሉ። እነዚያ ተኩስ ይከፍቱና ወደ ላይ ከቀረቡ በኋላ እነዚህኞ በነሱ ላይ አልፈው እንዲሄዱ ነው ፕላኑ። ከዚያ በኋላ እነዚህ ችግ ከገጠማቸው እነዚያ እንደገና ይረዷቸዋል።” አለኝ ኮ/አምሳሉ።

ወታደሮቹ ከታች ይነጉዳሉ። ወታደሮቹ ከሻዕቢያ ወንበዴዎች የሚለዩበ የለበሱት ልብስ አረንጓዴ መሆኑ ብቻ ነው እንጂ ጠቅላላ ሁኔታቸው ከዚ በፊት ተይዘው ያየኋቸውን የሻዕቢያ ወንበዴዎች ነው የሚመስሉት አብዛኞቹ ሱሪያቸውንና ጫማቸውን ለሙቀት ብለው ስለሚቆርጡ ጎፈሬያቸውን ስለማያሳጥሩት የመንግሥት ወታደሮች መስለው አልታዩ አሉኝ። በአንድ ረድፍ የጀመረው መጀመሪያው ከዓይን ጠፍቶ መጨረሻው መንቀሳቀስ ሳይጀምር ብዙ ጊዜ አለፈ። ከአምሳ ሺህ በላይ ወታደሮች በአንድ ረድፍ ራቅ ራቅ ብለው ይተማሉ።

ጀ/ደምሴ ከጀ/ቁምላቸዉና ከሌሎች መኮንኖች ጋር ሆኖ ከተራራው ወረድ ብላ ካለች አንድ ዛፍ ስር ቆሞ በመነፅር ከተመለከተ በኃላ "ለበኃይሉ በፕላኑ መሰረት እንዲቀጥል አስታውቁት" የሚል ትዕዛዝ ሰጡ።

ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ በመድፍና በሮኬት ድምፅ ሌላ የነፍስ ወከፍና የከባድ መትረየስ ድምፅ ቦታዉን ወደ ገሃነመ እሳትነት ቀየረው። እሩምታው አንዴ ይወርድና ለሰኮንድ ቆሞ ከዚያ ይቀጥላል። ድብልቅልቁ ወጣ።





የጦር ሜዳ መነፅሩን ሰክቼ የሚሆነዉን ለማየት ተስገበገብኩ። ተራራዉ ወገብ ላይ ወታደሮች ከግራ ወደ ቀኝ እየተኮሱ ይሮጣሉ። የሻዕቢያም ወንበዴዎች ከምሽግ ሆነዉ ሳይታዩ የጥይቱን ናዳ ያወርዱታል። እልፎ አልፎም የሞርታርና የላዉንቸር ጥይቶች ከተራራዉ ወገብ ላይ ወደ ላይ ጉነዉ እየተመዘገዘጉ ይወርዳሉ።
ወዲያዉ ደግሞ ሁለት ሄሊኮፕተሮች ከበስተቀኝ በኩል አፋቸዉን ወደ መሬት አሹለዉ በፍጥነት ተጓዙና እጋሮ ተራራ ጋር ሲደርሱ ከጎናቸዉ የቆምንበትን መሬት አንቀጥቅጠ በተፈናጠረ ሮኬት የተራራዉን ጫፍ አረሱት። ሁለቱም ሄሊኮፕተሮች በተራራዉ አናት ላይ ቆም ብለዉ ያላቸዉን ጥይት ማርከፍከፍ ያዙ። መትረየሳቸዉ በሚፈጥረዉ ድምፅ ወከዉ የሚል ድምፅ ተሰጥቶታል። ወከዉ ከዉ ከዉ.... ጥይታቸዉን አርከፈከፉት። ወታደሩ ወደ አናት አካባቢ ለመድረስ ትንሽ ነው የቀረው። ሄሊኮፕተሮች የማሳረግያ ዓይነት ደባልቁ ሮኬታቸዉን አወናጭፈዉ ተጨማሪ ጥይትና ሮኬት ለመሙላት ወደ ከረን ተመለሱ።

በዚያን ጊዜ የተሰማኝን ለመግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነዉ። ግን እንዲሁ ተቅበዘበዝኩ። ሜነፅሩን ሰክቼ ተራራዉን አስሳለሁ። ሁለት ወታደሮች ወደ ጎን ተገንጥለዉ ሲሮጡ እየሁና በመነፅሩ ተከተልኳቸው። ከአንድ ምሽግ ዉስጥ አንድ ሰዉ ብቅ ብሎ የእጅ ቦንብ ሲወረውርባቸው መሬት ላይ ተደፉ። ጥይቱ የፈነዳው መሬት ከያዙ በኋላ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን በመነፅሩ ብከታተላቸዉም ላገኛቸዉ አልቻልኩም። ፈልጌ ስላጣኋቸዉ ተናድጀ መነፅሩን አስቀመጥኩና ተወራጨሁ። የማዉቃቸዉ ሰዎች የሆኑ

ዓይነት ስሜት ተሰማኝ። ተነስቼ አባቴ ወደነበረበት ዛፍ ሥር ሄድኩና አንድ ድንጋይ ላይ ከጎኑ ተቀመጥኩ።

"አብርን የመጣዉን የሬድዮ ሠራተኛ ጥራው" አለኝ እንደ ማሰብ ካለ በኋላ። ትዕዛዙ ለኔ መሆኑን ተጠራጥሬ ዞር ብል ከኋላዬ ወይ ከጎኔ ሰው ስላልነበረ ተገርሜ ሄድኩና አብርን የመጣውን መገናኛ ሠራተኛ ጠራሁት። ይህችም ሥራ ሆና ድርሻ የተሰጠኝ ዓይነት ደስ አለኝ። ቁጥር ውስጥ የገባሁ መስሎ ተሰማኝ።

"በኃይሉን አገናኝኝ" አለ ጀ/ደምሴ። ሌሎች መኮንኖችም መጡ።

"ዘርዘር ብላችሁ ተቀመጡ። አትታዩ! እዚያ ጋር የተሰበሰቡትንም ቦታ እንዲይዙ ንገራቸው። በጣም የተዝናኑ ይመስላሉ።" አለ በዱላው የነበረኩበትን ቦታ እያመለከተ።

"9-50 ትሰማለህ? 9-50?"

"አስርት ክልተ፤ ክልተ አህደ፤ አሙሽተ ክልተ፤ ሽድሽተ አሙሽተ..."

የሬድዮኑን ሞገድ ሲቀይረው የመጣ የሻዕቢያ ሬድዮ መልእክት ነበር።

"እባክህ 9-50 መሥመሩን ይዘናል" የሻዕቢያው ሬድዮ ሠራተኛ ነበር። ለማመን በጣም አስቸጋሪ የሆነብኝ በኢትዮጵያ ጦር ሬድዮ ሠራተኛና የሻዕቢያ ሬዲዮ ሠራተኛ መካከል የነበረው መከባበርና ከዚያም አልፎ መረዳዳት ነበር። በሞገድ ግጭቶች ምክንያት ሁለቱም በአንድ ጊዜ መልእክት ሲያስተላልፉ ከተጋጩ፣ በስምምነት አንዱ ለአንዱ ይለቃል። ዋናው የሬድዮ ሠራተኛውን በኋላ በሁኔታው ተገርሜ ስጠይቀው የሰጠኝ መልስ "ምን ይህ ብቻ አንዳንዴ እኔ የምፈልገውን ጦርቼ ሳጣ በነሱ በኩል የማስፈልግበት ጊዜ አለ። እነሱም እንደዚሁ ያደርጋሉ" አለኝ። ይህን





ለማመን አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። ነገር ግን እቦታው ተገኝቼ ስላየሁት ለማመን ተገድጃለሁ።

ጀ/ደምሴ በመስመሩ መያዝ ተናዶ "መልዕክት እንኳን ማስተላለፊያ ደህና መሣሪያ እንጣ?" አለና "አሁን እነሱ የምናስተላልፈውን ለመጥለፍ ደቂቃ አይፈጅባቸውም።" ብሎ የተሰበሰቡትን አየ።

"9-50 ይሰማሃል? 9-50?"

"ይሰማኛል ማነህ? ቀጥል"

"ጎፈር ነኝ። እስቲ --- ን አገናኝኝ ጎፈር ይፈልገዋል። ውጪ!"

"--- ነኝ ቀጥል" አሉ ኮ/በኃይሉ የ18ኛ ተራራ ክ.ጦር አዛዥ።

ጀ/ደምሴ በኦርምኛ መልእክት ማስተላለፍ ሲጀምሩ በአካባቢው ያለው ሁሉ ተገርሞ ማየት ጀመረ።

ተነጋግረው ሲጨርሱ "ሻዕቢያ ይህን እስኪያስተረጉም ትንሽ ጊዜ እናገኛለን። አሁን የሚዋጉት ባሉበት እንዲመሽጉ እናድርግና እነዚህ በእነሱ ላይ ተራምደው ይለፉ። ይህን ያህል ኃይል እንዳልጠበቁ እርግጠኛ ነኝ። ይቺ በየቦታው በቀሰቀስናት ጦርነት ኃይላቸውን ለማጠናከር እንዳይችሉ ስላደረግናቸው ነው. እንጂ ይህን ቦታ እንደዚህ አልነበረም የሚከላከሉት።" አለ ጀ/ደምሴ ፈገግ ብሎ። ከዚህ በፊት የአጋርን ተራራ እንደምናጠቃ ያውቃሉ፤ አንድ ግን የማያውቁት ነገር አለ" ያለው በየትኛው አቅጣጫ እንደሚጠቁ አለማወቃቸውን ነበር። በየግንባሩ ጦሩ የማጥቃት ዓይነት እንቅስቃሴ አድርጎ ኃይላቸውን ለማሰባሰብ እንዳይችሉ ተደርጓል። እናም "ጦርነት የሚካሄደው በሁለት አዛዦች ጭንቅላት ነው። ተቃራኒው

የሚያስበውን ያወቀ ድል አይሆንም" ብሎ ያለውን እሁን በተግባር እየተመለከትኩት ነው።

ጦርነቱ ተፋፍሟል። የመድፍና የሮኬትም ተኩስ ባለማቋረጥ የተራራውን አናት ይቀጠቅጣል። ሄሊኮፕተሮቹ ከሄዱ ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ ሁለት ሚግ ተዋጊ አውሮፕላኖች ነጎድጓዳቸውን እያሰሙ በአናታችን ላይ አለፉ። አንደኛው ዝቅ ብሎ በተራራው ላይ ሲያልፍ ሌላኛው ወደ ጎን ተገነጠለና ዞሮ ተመለሰ። ወደ ጎን የተገነጠለውን በጦር ሜዳ መነፅር ተከተልኩት። ለዓይን ርቆ ከሄደ በኋላ ድንገት ተመለሰና ከተራራው አናት ጋር ሲደርስ በቀይ ጃንጥላ የተንጠለጠለ ቦንብ ጥሎ አለፈ። ቦንቡ በጃንጥላው የዓየሩን ግፊት እየተቆጣጠረና አቅጣጫውን ሳይቀይር በቀጥታ የተራራው አናት ላይ ወደቀ። ለጥቂት ሰኮንዶች የተፈጠረውን ሁኔታ ለማስረዳት በቂ ቃላት ማግኘት የምችል አይመስለኝም። ነፍስና ሥጋን ለደቂቃ ለይቶ ሕይወትን በተለየ ነባራዊነት የሚያስቀምጥ ከሰማይ የወረደ ቁጣ ነፍሴን ለአፍታ በብራቅ አጅቦ ከሲኦል ነበልባል ያወረዳት መሰለኝ። በአካባቢው የተረፈ የጆሮ ታምቡር ካለ ተአምር ነው። ሁለተኛው ተዋጊ አይሮፕላንም የተሸከመውን ሮኬትና ጥይት አርከፍክፎ ባለ ጃንጥላውን ቦንብ ጥሎ ተፈተለከ። አውሮፕላኖቹ ላይ ከመሬት የሚተኮሱት ጥይቶች ወደ ሰማይ ነጥረው የተወሰነ ከፍታ ላይ ሲደርሱ ጭስ ያወጣሉ።

የተኩሱ ኳኳታና የመድፉ ድምፅ በአውሮፕላኑ ቦንብ ድምጽ ትንሽ ተውጦ ቆየና ወዲያው ደግሞ ቀጠለ። ሻዕቢያም በተኩስ በኩል አልቦዘነም።





የመድፍ፣ የሞርታርና የላውንቸር ድብደባ የተራራው ተረተር ላይ ከአናቱ እየተወረወረ ሲያርፍ ይታያል።

ካለንበት ተራራና ጦርነቱ ከሚካሄድበት የአጋሮ ተራራ መካከል በስተግራ በኩል 18ኛው ተራራ ክ.ጦር ቀዳሚ መምሪያ ምሽግ እና ኮ/በኃይሉ ትዕዛዝ የሚሰጡበት ተራራ ይገኛል። ይህንኑ ደርሰውበት ኖሮ ወንበዴው በከባድ መሣሪያ ተራራውን ያርሰው ገባ።

ዘገው! ዘገው! ዘገው! ዘገው የሚባለውን ላውንቸር ይተኩሳሉ። መሣሪያው በሚያወጣው ድምፅ ነው የሚጠራው።

"የእነ በኃይሉ ቀዳሚ መምሪያ እዚያ መሆኑን ደርሰውበታል።"

"እሱን ለመምታት ነው የሚሞክሩት።" አለ ጄ/ደምሴ የዘገው ጥይቶች ተከታትለው ቦታውን ሲደበድቡ። ተኩሱ የሚተኮስበትን ቦታ በመነፅር ፈለገና አጠገቡ የነበሩትን የራሺያ ጀነራል፣ "እርስዎ የታንክ ኤክስፐርት ነኝ ብለውኝ ነበር፤ አይደለም?" አላቸው።

ጀነራሉም አስተርጓሚያቸውን አዳመጡና። "አዎን ትክክል ነዎት" በማለት ተስማሙ።

"ተኩሱ የሚመጣው ከዚያች ቦታ ነው። እና በአንድ ታንክ ከዚህ ስር ሆነው ቢተኩሱ ሊመቱት የሚችሉ ይመስለኛል። ምን ይመስሎዎታል?" አለ ጄ/ደምሴ።

"በጣም ደስ ይለኛል። ጥሩ ሐሳብ ነው።" ብለው ጀነራሉ ወደታች ወረድ አሉና አንድ ታንክ ውስጥ ገብተው ከነጂው ጋር ወደፊት ሄዱ። ከተራራዋ

ወገብ ወደ ፊት ወጣ ካለች ቦታ ላይ ሲደርሱ ታንኩ ቀመና የመድፉን አፈሙዝ አቅጣጫ አስተካከለ።

የዘገው ጥይት አሁንም እነ ኮ/በኃይሉ የሚገኙበትን ተራራ ይደቃዋል። ታንኩ የሚያደርገው የተኩስ ዝግጅት ረዘመብኝ። የዘገው አፈሙዞች ቶሎ አፋቸውን መዝጋት ነበረባቸው። ሶስት የዘገው ጥይቶች ተከታትለው ከተባለችው ቦታ ሲመነጠቁ! ታንኩ የቆምንበትን መሬት በሚያንቀጠቅጥ ድምፅ የታጀበ እሳቱን ተፋ። ጥይቱ እንደ እቶን እየተንቀለቀለ ተምዘግዝጎ ዘገው ከሚተኮስበት ቦታ ላይ ሲያርፍ ዘገው አፉን እንደተያዘ ሁሉ ድምፁን አጠፋ። ታንኩ ተኩሱን ባለማቋረጥ አካባቢውን ሁሉ ደብድቦ ሲያበቃ አፈሙዙን ወደ ሰሜን እንደደገነ የሰረኛ አካሉን ብቻ አዞረና ከነበረበት ተመለሰ።

የራሺያው ጀነራልም እንደ ብረት ምጣድ ሰፋ ያለ ክብ ቅርፅ ያለውን ሆዳቸውን እያሹ ወደኛ መጥተው ተቀላቀሉ። “በጣም ጥሩ ነው። ትክክለኛ ቦታውን ነው ያገኙት” አሉቸው ጂ/ደምሴ።
“አመሰግናለሁ” አለ አስተርጓሚው እሳቸው በአገራቸው ቋንቋ የተናገሩትን ተርጉሞ።

የመትረየስና ጥይት እና የእጅ ቦንብ ናዳ ከተራራው አናት ላይ ወደ ታች መጉረፉን ቀጥሏል። ሻዕቢያ ያለ የሌለ ሐይሉን ተጠቅሞ ተራራዋን ሳይለቅ ለመቆየት ያቀደ ይመስላል። አሁንም በጦር ሜዳ መነፅር የሚሆነውን መከታተል ገባሁ። ከተራራው አናት ላይ የተደበቁት ወንበዴዎች አንዳንዴ ብቅ ይሉና በሳጠራ ብጤ የእጅ ቦንብ ወደ ታች እንደ ቡና ቁርስ





ይበትኑና ዘለው እምሽጋቸው ይገባሉ። የተወረወሩት የእጅ ቦንቦችም ወደ ታች ይንከባለሉና እዚህም እዚያም ይፈነዳሉ።

አዲስ የደረሰው ጦር የነበረውን ኃይል አጠናክሮ ማጥቃት ሲጀምር የሻዕቢያ ጦር ሁለት የላውንቸር ጥይቶችን ወደ ሰማይ ተኮሰ።
“ምንድን ናቸው እነዚህ ወደ ሰማይ የተተኮሱት?” አልኩና ጠየኩ አጠገቤ የነበረውን መኮንን።
“ሻዕቢያ የምትጠቀምበት ምልክቶች ናቸው። ወንበዴ እንዲያፈገፍግ ወይ እንዲያጠቃ ወይ ደግሞ አንድ እነሱ ቀደም ብለው የተነጋገሩበትን ፕላን እንዲፈፅም ወደ ሰማይ ላውንቸር ይተኩሳሉ። የሚተኩሱት የላውንቸር ቁጥር አለቆቹ የሚያውቁት ኮድ ነው።” አለኝ።
“አሁን እንግዲህ አፈግፍጉ ነው ማለት ነው ኮዱ” የሆዴን ነበር የተናገርኩት።
“አይ አይታወቅም። እኛ የእነሱን ኮድ አይተን የመሰለንን እንዳንወስን ትዕዛዝ ተላልፎልናል። ምናልባት እኛንም ለማደናገር ይሆናል አንዳንዴ የሚተኩሱት።” አለኝ መኮንኑ ወደ ፊት እየተመለከተ።

ቀጥሎ የሚሆነውን መነፅሬን ሰክቼ መጠባበቅ ጀመርኩ። ላውንቸሮቹ ወደ ሰማይ ከተተኮሱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተራራው አናት ላይ ደርሰው ወንበዴዎቹ የነበሩበት ምሽግ ውስጥ እየዘለሉ መግባት ጀመሩ። ከምሽጎቹ አንዳንዴ የመትረየስ እሩምታ ይሰማና ከዚያ ፀጥ ይላል።
“ሻዕቢያ መጨረሻ ላይ ወደ ኋላ ትታ የምትሄዳቸው ሰዎች አሉዋት። በጦርነት አካለ ስንኩላን የሆኑትን በየምሽጉ ከባድ መትረየስ ተኳሽ

ያደረጓቸውና በጣም ሲጠቁ እዚያው ጥለዋቸው ይሄዳሉ። ታዲያ እነዚህ እስከ መጨረሻው ጥይት ድረስ ይታኮሳሉ። አለቃቸው ሳይናገር ደግሞ ምሽግ ጥለው አይሄዱም። እንዲያውም ከኋላ መትረየስ ጠምደው ድንገት የሚሸሽ ሰው የሚጠብቁ ሰዎች አሉዋቸው።" አለኝ መኮንኑ።

"ይህ በምን ይታወቃል?" ብዬ ጠየቅሁ በየዋህነት

"በምናየው እንዲሁም ከእነሱ ጋር የነበሩ ወደ ገቦች በሚሰጡት መረጃ፤ ሌላም ብዙ መንገድ አለ።" አለኝና ሳቅ አለ።

ወታደሮቹ በየምሽጉ የቀሩትን መትረየስ ተኳሾች ዝም ካሰኙ በኋላ የተኩስ ድምፅ እልፎ እልፎ ካልሆነ መሰማት አቆመ።

"አሁን ምሽጉን እንዲያጠናክሩና ሻዕቢያ ለሚያደርገው የመልሶ ማጥቃት እንዲዘጋጁ ትዕዛዝ አስተላልፋላቸው። ምንም ዓይነት ፈንጠዚያ አያስፈልግም አሁኑኑ ወደ ምሽግ ሥራ መሰማራት አለባቸው። ከታች ያሉትም በሁለት በኩል በጎንና ጎን በኩል ወደ ላይ እንዲጠጉ ትዕዛዝ ይተላለፍ።" አለና ጂ/ደምሴ በጦር ሜዳው መነፅር የአጋሮን ተራራ ቃኘው።

የጥይት ድምፅ እልፎ እልፎ ከሚሰማው የኤ.ኬ.14 ነፍስ ወከፍ መሣሪያ ድምፅ በስተቀር ቆሟል። በመነፅሩ ተራራዋን እንደገና ስቃኛት ከጫፏ ላይ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ባንዲራ ሲውለበለብ አየሁ።

አሁን እልፎ እልፎ ይሰማ የነበረውም የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ድምፅ ቆሞ አጋሮ በፍፁም ፀጥታ ተውጣለች።

ከግማሽ ሰአት በኋላ "እሺ ያመጣነውን ምሳ እንጋብዛቸዋ?" አለ ጂ/ደምሴ ወደ እኔ ዞር ብሎ።





"እሺ ላምጣው" አልኩና ወደ መጣንበት መኪና ሄድኩና እብድ የሚያክለውን አገልግል ከኃላ አውርጄ እየተንገዳገድኩ በአባቴ እጃቢ እርዳታ አመጣሁ።

አገልግሉን አንድ ረዘም ያለ ሙሉ ሰው የሚባል እንኳን ዙሪያውን አቅፎ እጆቹን ሊያነካካ አይችልም። ከተጠቀጠቀ ትልቅ ሻንጣ አይተናነስም። እናቴ አገልግሉን ያዘጋጀችው በቀላሉ አይደለም። ሲሰራ ቆሜ አይቻለሁ። አራት ድስት ሙሉ ዶሮ ወጥ አገልግሉ ዙሪያ ደርድራ ከላይ ከላዩ እየጨለፈች አገልግሉ ውስጥ ተደራርቦ የተነጠፈው እንጀራ ላይ አፈሰሰች። ከዚያም ገምደል ገምደል እያደረገች የምትቆርጠውን እንጀራ ከላዩ አድርጋ እንደገና በዶሮው ወጥ አራሰችው። የራሰው ፍትፍት ላይ ደግሞ እንደገና አንድ ሁለት ሙሉ እንጀራ፤ እሱ ላይ ደግሞ ከወጡ ፈሰስ፣ እጥንቱን ሻጥ ሻጥ፣ እንቁላል ዘርዘር እያደረገች ካስቀመጠች በኋላ ያደረገችውን ሁሉ እንደገና ትደግማለች። አገልግሉ ጢም ብሎ ሲሞላ በተደራራቢ እንጀራ ተሸፍኖ በጠፍሩ ድብን ተደርጎ ታሰረ። ያንን ነበር ከአዲስ አበባ አስመራ ከአስመራ ከረን፣ ከከረን እዚህ ቀውጢ ሜዳ ይዤ የመጣሁት።

አባቴ በየሄደበት የናቴ አገልግል በየጊዜው የሚላክ ስለነበረ በተቻለው "እቴቴር የላከችው" እያለ በባለሙያ የተሰራ ምግብ ከበሉ ዘመናት ያለፉቸው መኮንኖችና ወታደሮችን መመገብ ያስደስተው ነበር።

አገልግሉን በትላልቅ ትሪ ቀነስንና ሁለት ቦታ አቀረብን። በአካባቢዉ የነበሩት መኮንኖች ተጠርተው መብላት ጀመሩ። አንዳንዶቹ መኮንኖች የቤት ምግብ ከበሉ ምናልባት ከአስር ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። እኔ ከሰሞኑ ተመልሼ የምደርስበት ስለሆነ አንድ ሁለት ጎረስኩና የወታደር ጋሌጃ (ጣዕም የሌለው ወታደሮች የሚበሉት ብስኩት) በበውኃ እያማግሁ በላሁ።

ምሳ በልተን እንደጨረስን የሻዕቢያ ጦር መልሶ አጠቃ። ለሰላሳ ደቂቃ ያህል የተፋፋመ የመትረየስና የእጅ ቦንብ ውጊያ ተደረገ። ጠሩ ግን ቦታውን አልለቀቀም። የመልሶ ማጥቃቱ ውጊያ ከበፊቱ በተፋጠነ ሁኔታ የተኩስ እሩምታ ይሰማበት ነበር።

"አሁን ከጎንና ጎን ተራራው ወገብ ላይ የተጠጉት ዙሪያውን በቀኝና በግራ እንዲዞሩና ከበባ እንዲያደርጉ ለበኃይሉ ትዕዛዝ እንዲያስተላልፍ ንገሩት።" አለ ጀ/ደምሴ በተቀመጠበት ድንጋይ ላይ ተዝናንቶ እንደተቀመጠ ነው። ምንም ጭንቀት አይታበትም። ፊቱ ብቻ ቋጠር ፈታ ሲል ነው የሚታየው።

"አሁን ድብልቅልቁ ሊወጣ ነው" አልኩ በሆዴ። ሁሉ ነገር እንደ ታቀደው መከናወኑ ገባኝ። ሻዕቢያ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ እንደሚወስድ እንዴት እንደታወቀ ባይገባኝም በእቅዱ መሰረት መልሶ ማጥቃት እንደሚያደርጉ ቀድሞ የታወቀ ይመስላል።





ከተራራው ወገብ በመጠባበቅ ላይ የሚገኘው ጦር ትዕዛዙ እንደ ደረሰው በሁለት አቅጣጫ ተራራውን ዞሮ የሻዕቢያን ወንበዴ ከበስተጀርባው ለመክበብ እንቅስቃሴውን ጀመረ። ሻዕቢያ ቦታውን የያዘው ጦር ተጨማሪ እርዳታ እስኪመጣለት ላለመቆየት ይመስላል ያለ የሌለ ኃይሏን በተራራው እናት ላይ በመልሶ ማጥቃት ውጊያ አሰማርታለች።
ጀ/ደምሴ "ወንበዴ ከፊታችሁ እንደማይቆም ማንም ያውቀዋል" ብሎ ያሞገሳቸው የ18ኛው ተራራ ክ.ጦር ከኋላ በመዞር የሻዕቢያን ወንበዴ ከጀርባው ማጥቃት መጀመሩን ለማየት ባንችልም ተራራው እያስተጋባ የሚልከው የገደል ማሚቶ የጥይቱን ድምፅ በአናታችን ላይ እያፏጨ ሲያስተጋባ የሞት ሽረት ተጋድሎው መጀመሩን ደረስንበት።

በዳመናው እምቢተኝነት ጨረሯን ማስተላለፍ የተሳናት ፀሐይ ጭራሹኑ ጠፍታ አካባቢው እንደመጨለም አለና እንዲያውም ካፊያ ቢጤ ብን ብን እያለ መውረድ ጀምሯል። በሶስት ማዕዘን የመጣበትን ጦር፤ ሻዕቢያ እንደ ምንም ለመከላከልና ሰብሮ ለመውጣት ሙከራ እያደረገ ነበር። ጦርነቱ አሁንም ለትንሽ ጊዜ ቀጠለና እየቀዘቀዘ እየቀዘቀዘ ሄዶ በአካባቢው የመቃብር ቦታ አይነት ፀጥታ ሰፈነ።

"አጋሮ በቁጥጥር ስር ውሏል የሚል መልእክት ደርሶናል ጌታዬ" አለ የሬዲዮ ሠራተኛው።
"ጥበቃውንና ምሽግ እንዲያጠናክሩ ትዕዛዝ እንዲተላለፍ፤ ለሁሉም ብርጌድ!" አለና ጀ/ደምሴ ከተቀመጠበት ድንጋይ ተነስቶ ወደ መኪኖቹ አመራ።

“በሉ እንግዲህ በጣም ጥሩ ነው። ጠርነቱ ገና አላበቃም ተደጋጋሚ መል ማጥቃት ያደርጋሉ፤ መዘናጋት የለብንም። ነቅቶ መጠበቅ ነው።” አለ መኮንኖቹን ተሰነባባተ። ወደ መኪኖቹ ሲያመራ ሁላችንም ተከተልነው። ወነ ኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ዞር ብዬ የአጋሮን ተራራ ተመለከትኳት፤ በመነፅሩ አናቷን ቃኘኋት። ባንዲራዋ አሁንም ካፊያ በፈጠረው ንፋስ ያለ እረፍት ትውለበለባለች። እረፍት ያጣች ባንዲራ፤ እረፍት ያጣች አገር።

መኪናችን ላይ ተሳፈርንና ወደ ከረን ለመመለስ ጉዞ ጀመርን። የአጋሮን ተራራ አካባቢ ለቀን መሄድ ስንጀምር እንግዳ ስሜት ተሰማኝ። ከአጋሮ ጋር ያቀራኘኝ አንድ ነገር እንዳለ ሁሉ ብዙ ዓመት ከኖርኩበት ቦታ ተለይቼ ስሄድ የሚሰማኝ ዓይነት ስሜት ወረረኝ።

ተራራውን ወርደን ከሚቀጥለው ተራራ ጋር ከሚያገናኘው መስቀለኛ መንገድ ስንደርስ ሁለት ቁስለኞች የጫኑ ከባድ መኪኖች ወደ እኛ አቅጣጫ ሲመጡ አየን። በጥይትና በቦንብ ፍንጣሪ የተመቱበት ቦታ በፋሻ ተጠቅልሎ ግማሾቹ ተቀምጠው ግማሾቹ ደግሞ ተኝተው አይኖቻቸውን ቡዝዝ እንዳደረጉ ሁሉም ከመኪናው ጋር እየተወዛወዙ ይጓዛሉ። በሩቅ የተመለከትኩት አሁን ስቀርበው አስፈሪነቱና ዘግናኝነቱ ጎልቶ ታየኝ።

ጀ/ደምሴ በሩን ከፊት አደረገና “እስጊ ሁኔታ ላይ ያሉትን በሔሊኮፕተር ወደ ከረን ልካችሁ ነው ወይስ ዝም ብላችሁ ነው ሁሉንም በመኪና የምትወስዷቸው?” አለው ከፊት የተቀመጠውን መኮንን።





“በሔሊኮፕተር የሄዱ እሉ ጌታዬ እነዚህ ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው።” አለ መኮንኑ።
“እሺ መልካም እንሂድ” አለና በሩን ዘጋ።

ካፊያው ባያይልም አላቋረጠም ነበር። ከዚያች ለምለም የሞት ጎራ ሰፍራ ስንደርስ ግን ወንዙ ከበፊቱ በበለጠ ሞልቶ ለመሻገር አስቸጋሪ ሆኖ አገኘነው። ሁላችንም ከመኪኖቹ ስንወርድ ባካባቢው የነበረው ትርምስ ጋብ አለ።

“ና እስቲ ወዲህ? ወዴት ነው የምትሄዱት?” አለ ጀ/ደምሴ ከኛ በፊት ወንዙ ዳር ቆሞ የነበረውን የአይፋ መኪና ሾፌር።
“ወደ ከረን ነው የምንሄደው ጌታዬ።” ብሎ መለሰ።
“ጥሩ ነው። ግማሾቻችን ከአጃቢዎች ጋር ግማሾቻችን ደግሞ ከእነሱ ጋር እንቀጥላለን። እናንተ ድልድይ ጥሩና ተሻገራችሁ ኑ። እዚያው ከረን እንገናኛለን።” አለ።

ከአይፋው ላይ የነበሩት ወታደሮች እየዘለሉ ሲወጡ፣ እኔም ከአባቴ አጃቢ ጋር ከኋላ ወጣሁ። አይፋው ከጎንና ጎን ክፍት ሆኖ ከላይ ብቻ መከላከያ ሸራ የነበረው ስለሆነ ጥሩ ንፋስና የካፊያ ብናኞችን እያመጣ ነፍስን ያድሳል። የነፍሴ ተጎድሶ ግን ከዙሪያዬ የተቀመጡትን ዞር ብዬ እስካጤን ድረስ ነበር የቆየው። ወንዙ ውስጥ ገብተን መንቀሳቀስ እንደ ጀመርን አይኔን ከወንዙ መለስ ሳደርግ እጥጉ ላይ ሁለት ጎፈሬአቸው ያለ ቅጥ ያደገ፣ ጥቁር መሳይ ቁምጣ ና ሸሚዝ፣ ክፍት ክፍት ካለው ላስቲክ

ጫማ ጋር ያደረጉ ጎረምሶች አፍጥጠው ይመለከቱኛል። ቀልቤን ገፈፉት። እኔም ለተወሰኑ ደቂቃዎች አፍጥጬ ተመለከትኳቸውና "እነዚህ የተማረኩ ናቸው?" ብዬ ጠየኩ አጠገቤ የነበረውን ያባቴን አጃቢ። "አይደሉም ወደ ገቦች ናቸው።" አለኝ።

አንደኛው በጣም ልጅ ከመሆኑም ሌላ አለመጠን ቀጭን ነበር። "አሁን ይቺ ምን ትዋጋለች?" አልኩና ወደ ሁለተኛው ደግሞ ዞርኩ። ይሄኛው ትንሽ ይሻላል። በዕድሜም ቢሆን አንድ ሃያ ዓመት አያጣም። ሁለቱም ምስኪን ብጤ ናቸው።

"ይች ትንሿ ሁለት ዓመት ትልቁ ደግሞ አራት ዓመት የተዋጉ ናቸው።" አለኝ የአባቴ አጃቢ።

"በምን አወቅህ? ከዚህ በፊት አግኝተሀቸዋል?" አልኩት ተገርሜ።

"አዎ እሳቸው ሊያነጋግሩዋቸው ጠርተዋቸው ነበር። አሁን ከአስመራ ነው የመጡት መንገድ እንዲጠቁሙ። ከቃፊሮች ጋር ይሠራሉ።" አለኝ።

"እኔም ባነጋግራቸው ደስ ይለኝ ነበር።"

"አማርኛ አይችሉም"

"ባንተ አስተርጎሚነት"

"እሱን ትችላለህ።" አለኝ። ሁለተኛው አጃቢ ነበር። የኤርትራ ክፍለ ሐገር ተወላጅ ነው። ሁለቱን ወደ ገቦች ከረን ስንደርስ እንዴት ሻዕቢያ ሊገቡ እንደቻሉ ስጠይቃቸው ከቤታቸው ተገደው መወሰዳቸውን ገለፁልኝ። "ሁሉም ተገዶ የተወሰደ ከሆነ ታዲያ እንዴት ጦርነቱን ሳያምንበት ይዋጋል?" ብዬ ስጠይቅ ከልጅነታቸው የሰለጠኑ እና በሻዕቢያም ዓላማ የሚያምኑ በየጠሩ





እንዳሉና፣ ሌሎችም ደግሞ ወደው ከሻዕቢያ እንደሚቀላቀሉ፤ ነገር ግን ተገደውም የሚወሰዱ እንዳሉ አስረዱኝ። እነሱ የመጡት በ.ቢ.አር.ዲ.ኤም ብረት ለበስ ላይ በተጠመደው የድምፅ ማጉያ የተላለፈውን የመንግሥት መልዕክት ሰምተው መሆኑን ገለፁልኝ። ብዙም አልጨቀጨጭቃቸውም ብዬ በዚሁ ጥያቄዬን አበቃሁ።

መንገዳችንን ቀጥለን የሶስተኛው አንበሣ ክፍለ ጦር መምሪያ አካባቢ ስንደርስ ተጨማሪ ጦር ወደ ነበርንበት አቅጣጫ ይንቀሳቀስ ነበር። ዙ 23 የተባለ ፀረ አውሮፕላን መሣሪያ አራት ሰዎች እላዩ ላይ ተቀምጠው እየተጓዘ ይሄዳል። ሻዕቢያ አውሮፕላን ስለሌለው ጠሩ የሚጠቀምበት ለሰው መሆን አለበት። ከአንዱ ዙ 23 መሣሪያ ከሚጎትት መኪና ላይ ተጭኖ የሚሄድ አንድ እዚህ ግባ የማይባል ህፃን አይቼ ዐይኔን ማመን አቃተኝ። ቀይ ድንቡሽቡሽ ያለ ቢበዛ የ15 ወይም የ16 ዓመት ልጅ፣ እሱኑ የሚያክል ክላሽንኮቭ ይዞ በጉራ አካባቢውን ይቃኛል። የዚህ አይነቱን ህፃን ልጅ ወደ ጦርነት ቀርቶ የመንደር ሱቅ እንኳን ሲልኩ ከብዙ ማስጠንቀቂያ ጋር መሆን አለበት። ወዴት እየሄድን እንደሆን ገራ ገባኝ። ወጣቱ አልቆ ህፃናት እየተመለመሉ ነው ማለት ነው? በጣም አሳዘነኝ። አብሮኝ ከሚጓዙት ወደ ገቦች ጋር አስተያየኋቸው። ምንም ልዩነት የላቸውም! አንድ ናቸው። ሕይወትን ሳይጀምሯት ጣዕሟን ሳይቀምሷት ጥለዋት ለመሄድ የተሰናዱ ጨቅሎች...